# የመምህሩ መምሪያ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ደረጃ 3 እና 4

ሥርዓተ ትምህርት ለ
ለ7 - ለ12

www.besweb.com

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታዊ አገልግሎቶች

በእንግሊዝ የበጎ አድራጎት ምዝገባ (ቁጥር 1186004)

### የተልዕኮ መልእክት

የአሁኑንና መጪውን ትውልድ በእግዚአብሔር ቃል ለመድረስ ለዓለም አቀፋዊ ግልጋሎት የሚውሉ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለእርስዎ በማዘጋጀት እርስዎም ሌሎችንም እንዲያገለግሉ ለማድረግ ነው።

### የራእይ መልእክት

የዓለም ቋንቋዎችን በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች በመጠቀም በእኛ ማዕከላዊ እሴቶች መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታዊ መረጃዎችን ከእኛ ጋር ለሚሠሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

## ጠቅላላ መረጃ

### የመጽሐፍ ቅዱስ የትምህርት አገልግሎት ምን እንደሚያከናውን:-

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትምህርት አገልግሎት (ቢኢኤስ) በኢንግሊዚኛ የተዘጋጁ። የአዲስ ህይወትን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ሰብስቦ በማሣተም፤ በፖስታ ቤት በኩል የሚሠጡ ትምህርቶችንና ሌሎች ተመሣሣይ በእንግሊዝ እንዲሁም በሌሎች አገሮች የሚሠሩ ድርጅቶችን በቢኢኤስ በኩል በመጎብኘት፤ በማስተሣሠር፤ በማስተዋወቅና በማሠልጠን ይረዳል። ከዚህ በተጨማሪም ቢኢኤስ በአሁኑ ወቅት በሌሎች አገሮች ውስጥ ትምህርቶችን በመተርጎም፤ በመንደፍ፤ በማሣተምና በማሠራጨት ሥራ ላይ ከተሠማሩ ቡድኖች ጋር አብሮ ይሠራል። ትምህርቶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች በነፃ የሚሠጡ ሲሆን ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ በደቡብ አየርላንድ ከ50 ዓመታት በፊት ተጀመረ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አገልግሎት አዘጋጆች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት በኢንግሊዚኛና በሌሎች ቋንቋዎች ለሚዘጋጁ ትምህርቶች ኃላፊነት አለባቸው። ብዙውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት

የሚዘጋጁ ትምህርቶች የሚታተሙት በA4 ፎርማት (አቀራረብ) ሲሆን ይህም በሌሎች አከባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች በየአራት ሣምንቱ ፈተናው ወደ ሚታረምበት የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል ለመላክ እንዲያመች ነው። በአሁኑ ጊዜም ለእያንዳንዱ ቤት የወንጌል ሥርጭት መነቃቂያዎች ምስጋና ይግባውና በቤል ፋስት ውስጥ ለስድስት ወራት የሚያገለግል ትምህርት በA5 ፎርማት (አቀራረብ) ስለሚታተም በተላይም የፖስታ አገልግሎት በማይገኝባቸው አብያተ ቤተ ክርስቲያናትና ትምህርት ቤቶች ጉዳዩን በጣም እንዲቀላጠፍ አድርጎታል። ቢኢኤስ በባህሪይው የሚለየው የሚዘጋጁት ትምህርቶች የቤት ወይም የቡድን ጥናትን ያማከሉና ተማሪዎቹም ሥርዓተ ትምህርቱን እስከ 20 ዓመታት ድረስ በቤተ ክርስቲያን/ትምህርት ቤት ያለማቋረጥ እንዲከታተሉ ስለሚያደረግ ነው። ለተወሠኑ የዕድሜ ደረጃ ቡድኖች የሚያገለግሉ አምስት የትምህርት ደረጃዎች ያሉ ሲሆን እነርሱም የቅድመ-ትምህርት ቤት፤ ከ5-7፤ ከ8-10፤ ከ11-13ና ከ14-16 ናቸው። ለእያንዳንዱ ቡድን የሶስት ዓመታት ሥርዓተ ትምህርት ይዘጋጃል። በተመሣሣይ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የቡድን አባላት የተለያዩ ችሎታዎች ሊኖራቸው ይችላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መረጃዎች ለልጆች የእግዚአብሔርን ቃል፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና በህይወታቸው የወንጌልን ጠቃሚነት ተግዳሮቶችን እንዲጋፈጡ እድል ይሠጣቸዋል።

በኢንግሊዚኛ ለትምህርት ተዘጋጅተው የታተሙ ቅጂዎች ከቢኢኤስ ድህረ ገጽ - www.besweb.com ወይም ከዓለም አቀፍ ጽህፈት ቤቱ ይገኛሉ። በድህረ ገጹ ላይ በሌሎች ቋንቋዎችም ይገኛሉ። ጽህፈት ቤቱ የቢኢኤስ ማዕከል ለማቋቋም የሚረዱ መረጃዎችን አለው።

## የቢኢኤስ መገኛ አድራሻዎች

**ዓለም አቀፋዊና የሠሜን አየርላንድ ጸሐፊ (ለትምህርት የተዘጋጁ ጽሁፎች በሙሉ)**
37a Belmore Street, Enniskillen, Northern Ireland BT74 6AA
ስልክ: 00 44 286 632 2462

**የዩናይትድ ኪንግደም ፀሐፊ**
Mr Stephen Gillham
ኢሜል: Email: Stephen.gillham@besweb.com

ድህረ ገጽ: www.besweb.com
ኢሜል: info@besweb.com

## ለመምህራን መምሪያዎች

የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች በመጀመሪያ ሲዘጋጁ በፖስታ በመላላክ ለማስተማር ታስበው ነበር። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የፖስታ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ማዕከላት ተቋቁመው ነበር። ነገር ግን የፖስታ አገልግሎት አስተማማኝ ባልሆነባቸው እስከጭራሹንም እየቀረ በሚሄድባቸው ስፍራዎች በተለይም ደግሞ በአፍሪካና በሕንድ እንዲሁም በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለሚጠቀሙ የማስተማሪያ መምሪያዎችም ተዘጋጅተዋል። በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተዘጋጁት የመምህሩ መምሪያዎች ታሳቢ ያደረጉት ደረጃ 3 እና 4ን በግምት እድሜያቸው ከ11-14+ ዓመት የሆኑ ልጆችን ነው።

እያንዳንዱ የመምህሩ መምሪያ ልክ በዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውስጥ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና መምሪያዎቻቸው በየሳምንቱ እንዲጠኑ ተደርገው ተዘጋጅተዋል። የሚያዚያ ትምህርቶች በተለይ ከፋሲካ ጋር የተገናኙ ትምህርቶች ሲሆኑ የታህሳስ ትምህርቶች ደግሞ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር የተገናኙ ናቸው።

በአንዳንድ ቦታዎች በኤ 4 የወረቀት መጠን የሚዘጋጀውን ሳምንታዊ ሕትመት ሲጠቀሙ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ 24 ትምህርቶችን የያዘውንና በኤ 5 የወረቀት መጠን የተዘጋጀውን ጥራዝ ይጠቀማሉ። መምህሩ ወይንም ደግሞ የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ በኤ 4 የወረቀት መጠን ትምህርት ያድላል። ትምህርቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይንም ደግሞ በት/ቤት ይሞላል ወይንም ደግሞ ወደ ቤት ይወሰዳል። ከዚያም በተከታዩ ሳምንት ይመለሳል። በወሩ መጨረሻ መምህሩ ወይንም የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ ትምህርቶችን ይሰበስብና ያርማቸዋል። ነጥብም ይሰጣቸዋል። በተቻለ መጠንም ከእርማት በኋላ ለተማሪዎች መመለስ አለበት።

የተዘጋጁት ጥራዞች ጥቅም ላይ ከዋሉ በየሳምንቱ መጨረሻ እየተሰበሰቡ ይታረማሉ። በብዙ ምክንያቶች ይህ አስቸጋሪ እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህም በክፍል ውስጥ ጥራዞቹ ለተማሪዎች ይከፋፈላሉ። በዚህ ጊዜ መምህሩ/መሪው ከተማሪዎች ጋር አብሮ ይሰራል። ተማሪዎችም የጓደኞቻቸውን ስራዎች ያርማሉ፣ ነጥብም ይሰጣሉ። ከጥራዞቹ በስተጀርባ ለእያንዳንዱ ነጥብ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ እንዲሁም ተማሪው ስላሳየው እድገት አስተያየት መስጫ ቦታ አለ። እንዲሁም ከጥራዙ በስተመጨረሻ ሰርተፊኬት ተያይዟል። ይህ ሰርተፊኬት በቀላሉ ከጥራዙ ላይ ሊገነጠል የሚችል ሲሆን ተማሪው ባለፉት 6 ወራት ከመቶ ያገኛቸውን ውጤቶች ይይዛል።

## ለመምህራን የተደረገ ዝግጅት

መምህራን በራሳቸው ዘዴ ወይንም መንገድ፣ ተነሳሽነትና ሀሳብ ላይ የተመሠረተ አንዳችም ነገር እንዲያደርጉ አንጠብቅም። ለእንደዚህ አይነት ጉዳይ ምንም ቦታ አንሰጥም። የሚከተሉት ሀሳቦች የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ሀሳቦች ናቸው።

- **ከታሪኩ ጋር በሚገባ ራስን ማስተዋወቅ -** ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና በተጓዳኝ አብረውት ከሚሄዱት የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር በተቻለ መጠን ራሳቸውን ማስተዋወቅ አለባቸው። መምህሩ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከማስተማሩ በፊት ራሱ አጥንቶ ቢያጠናቅቅ ተመራጭ ነው። ለእያንዳንዱ ትምህርት የተዘጋጁት መምሪያዎችም በእቅድ ወቅት ስለ ሚረዱ በጥንቃቄ ሊታዩ ይገባል።
- **ትምህርቶችን በሚገባ መረዳት -** ከእያንዳንዱ የትምህርት እቅድ በላይ ***"በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።"*** የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። እነኝህም መምህሩ ገለፃውን ካጠናቀቀ በኋላና ተማሪዎችም ያንን የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የሚጨብጧቸውን ሁለት አላማዎች የያዙ ናቸው። የመጀመሪያው አላማ ከታሪኩ ስለ ቀሰሙት እውቀት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ስላገኙት እውቀት እንዲያሰላስሉና በተቻለ መጠንም ምላሽ እንዲሰጡና ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት ያበረታታል። እነኝህ የመማር አላማዎች በተሰጠው ትምህርት ውስጥ ያለውን ዋና ፅነሰ ሀሳብ/እውነት የያዙ ናቸው። መምህራንም ራሳቸውን እንዲሁም የመማር የማስተማር ሂደቱን ለመገምገም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።
- **አስተዋውቁት/መግቢያ -** ሁሉንም ትምህርቶች የምንጀምረው ከራሳቸው ከተማሪዎች ልምምድና ካሉበት ሁኔታ በመነሳት ነው። ታሪኮችን በመግቢያው ውስጥ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ዘዴዎችን አቅርበናል። በዚህም ልጆች በትምህርቱ ማስጀመሪያ ነጥብ ላይ በመስተጋብር የተሞላ ውይይት እንዲያካሂዱ እናስችላቸዋለን።
- **የማስተማር ጊዜ -** የታሪኩን ቁልፍ ነጥቦች አቅርበናል። መምህራን ታሪኮቹን በሚያስተምሩበት ወቅት እነኝህን ቁልፍ ነጥቦች እንደማያነሷቸው ተስፋ እናደርጋለን። ሆኖም በሚያስምሩበት ወቅት ራሳቸውን ከታሪኩ ጋር በሚገባ አስተዋውቀው ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተማር ይጠቀሙባቸዋል። መምህሩ በትምህርቱ ውስጥ ያለውን ታሪክ ተማሪዎቹ በሚገባ እንዲረዱ ማድረግ አለበት። እንዲሁም ልጆቹ ታሪኩን ከተገነዘቡት በኋላ መስጠት ስላለባቸው ምላሽ አቅጣጫ ይጠቁማቸዋል። ከእያንዳንዱ ትረካ ጋር አብሮ የሚሄዱ ማብራሪያዎችንም አብረን ማቅረቡ ተገቢ ስለሆነ ይህንኑ አድርገናል። እነኝህም በኢታሊክስ *(ITALICS)* ተፅፈው ቀርበዋል።
- **የመማር ጊዜ -** ከእያንዳንዱ ታሪክ ጋር አብሮ የተያያዘ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለ። አንዳንድ ጊዜም ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተያይዘዋል። ምክንያቱም ተጨማሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተማሪዎች በቀላሉ መማር እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ልጆች እነኝህን ቁልፍ ጥቅሶች እንዲማሩ እንዲሁም በተደጋጋሚ እንዲያስታውሱት እንደሚደረግ ተስፋ እናደርጋለን። ይህም ልጆች የቁልፍ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እውቀት ግንባታ ማድረግ እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል።
- **ማጠናቀቅ -** በት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች ሰርቶ ማሳያ/የመለማመጃ ጥያቄዎችን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋቸውን የችሎታ ልክና መምህሩ በዚህ ረገድ ለተማሪዎቹ ሊያደርግላቸው የሚችለውን የእገዛ መጠን በተመለከተ ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል። አንዳንዶች መምህሩ ታሪኩን ካነበበላቸውና ከታሪኩ ጋር በሚገባ ከተዋወቁ በኋላ ወደ ስራ ይገባሉ። ሌሎች ልጆች ደግሞ ታሪኩን ራሳቸው ማንበብ ይችላሉ። በሁለቱም መንገዶች ዋናው ሀሳብ ጥያቄዎቹን ለመስራት በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የልጆቹ አትኩሮት እንዲያርፍ

ማድረግ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከት/ቤት ውጪ በሌሎች ቦታዎች የምትጠቀሙ ከሆነ ተማሪዎቻችሁን ባሉበት ቦታ በአካል ተገኝታችሁ መርዳት መቻል አለባችሁ። አለበለዚያ ተማሪዎቻችሁ ትምህርቱን እንደፈተና ወይንም ደግሞ የግድ መጠናቀቅ እንደላበት ስራ አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ። አስደሳች መሆን አለበት። ለዚህም ተማሪዎች እየሰሩ ባለበት ወቅት ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

- **የክለሳ ጊዜ -** በተቻለ መጠን ተማሪዎች በምን ያህል መጠን ትምህርቱን አውቀውታል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዱንን አጫጭር ሙከራዎችን መስጠት ወይንም አስፈላጊ መሆኑን እንመክራለን። ይህም ትምህርቱን ለመከለስና የተማሪዎችን የመማር ፍጥነት ለማገዝ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።
- **ማሳየት -** በአንዳንድ ሁኔታዎች የቪዡዋል (የእይታ) ትምህርት መርጃዎች በቀላሉ ላይገኙ ቢችሉም በተቻለ መጠን ለሚታዩ ስዕሎች ወይንም ደግሞ ለሌሎች ቁሳቁሶች ትኩረት መስጠትና በተግባር ማዋል ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል። በትረካ ወቅት የእይታ ትምህርት መርጃዎች ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ። አስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችን በተመለከተ መረጃ ከተፈለገ ከሚከተለው ዌብ ሳይት ማግኘትና ስዕሎችንም ማውረድ ይቻላል። [www.freebibleimages.org (FBI)] ሌላው የእይታ መርጃዎችን የምናገኝበት ምንጭም Eikon Bible Art [info@eikonbibleart.com] ዌብ ሳይት ነው። ሆኖም ከዚህ ዌብ ሳይት የምናገኛቸው ምንጮች በሽያጭ የሚገኙ ናቸው። የፎቶ ኮፒ ማሽን ባለበት አንዳንድ ስእሎች ሊተልቁ ቀለም ሊቀቡና በትምህርት ወቅት ጥቅም ላይ ማዋል ሊውሉ ይችላሉ።

**ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የማስተማር ጊዜ**

1) ጥቅሱ በወረቀት ወይንም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሊፃፍ ይችላል። ይህም የተለያዩ ቃላትን በማጉደል የሚደረግ ነው። ይህም ሁሉም የጥቅሱ ቃላት በሙሉ እስኪነሱና ተማሪዎችም ጥቅሱን በቃላቸው መድገም እስኪችሉ ድረስ ነው።
2) ቁልፍ ጥቅሱን ለማስተዋወቅ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ።
   ሀ) በሁለት ቡድኖች መስራት (በገመድ የመስቀል ዘዴ) - የቁልፍ ጥቅሱ የተለያዩ ፊደላት ተቀንሰው በምትካቸው ክፍት ቦታዎች አሉ። ልጆችም የትኞቹን ቃላት ቢጠቀሙ ጥቅሱን ማሟላት እስከሚችሉ ድረስ ይሰራሉ። ይህም ከመካከላቸው አንደኛው ልጅ ጥቅሱን እስከሚለየው ድረስ ይቀጥላል።
   ለ) ጥቅሱን ቀድሞ መፈለግ። መጽሐፍ ቅዱስ በቀላሉ የሚገኝ ከሆነ ተማሪዎች ቁልፍ ጥቅሱን ይፈልጋሉ። መጀመሪያ ጥቅሱን ያገኘው ልጅ አሸናፊ ይሆናል።

**ጊዜን ማቀድ**

- **ቅደም ተከተል.** ለሁሉም የማስተማሪያ መምሪያዎች ተመሳሳይ ቅደም ተከተል እንጠቀማለን። ሆኖም ይህን ቅደም ተከተል መምህራን እንደአስፈላጊነቱ ሊቀያይሩት ይችላሉ።
    1. መግቢያና ትረካ - በግምት 15 ደቂቃ
    2. ቁልፍ ጥቅሱን የማስተማር ጊዜ - ከ5 እስከ10 ደቂቃ
    3. ስርቶ ማሳያውን ማጠናቀቅ - 20 ደቂቃ
    4. መልመጃና ሌሎች ስራዎች 5-10 ደቂቃ

ይህን አባባል ሁሌም አስታውሱት።

“የነገራችሁኝን እረሳለሁ።
የምታሳዩኝን አስታውሳለሁ።
አብሬያችሁ ስሰራ በሚገባ እረዳለሁ።”

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ሥርዓተ ትምህርት

| | ደረጃ 0 (ቅድመ-ት/ት)<br>ደረጃ 1 (እድሜ 5-7)<br>ደረጃ 2 (እድሜ 8-10) | ደረጃ 3 (እድሜ 11-13) | ደረጃ 4 (እድሜ 14+) |
|---|---|---|---|
| የጀማሪዎች ስርዓተ ት/ት | የማሟሟቂያ ትምህርት-መግቢያ | የማሟሟቂያ ትምህርት-መግቢያ | የማሟሟቂያ ትምህርት-መግቢያ |
| ስርዓተ ት/ት ሀ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. የጴጥሮስ - መስቀል<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የጥንት ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. የጴጥሮስ - መስቀል<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የጥንት ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. የጴጥሮስ - መስቀል<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የጥንት ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የገና ታሪክ |
| ስርዓተ ት/ት ለ | 1. የመጀመሪያው የክርስቶስ ኑሮ<br>2. ተዓምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. ምሣዎች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. ኢየሱስ ያገኛቸው ሰዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ምሣሌዎች<br>2. ተዓምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የጥንት ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ጸሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ምሣሌዎች<br>2. ተዓምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የጥንት ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ጸሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የገና ታሪክ |
| ስርዓተ ት/ት ሐ | 1. ዳንኤል<br>2. ብዙ ተዓምራት<br>3. ብዙ ተዓምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሣሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. እያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሣ<br>11. ዮናታን<br>12. የገና ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ብዙ ተዓምራት<br>3. ብዙ ተዓምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሣሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. እያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሣ<br>11. ዮናታን<br>12. የገና ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ብዙ ተዓምራት<br>3. ብዙ ተዓምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሣሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. እያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሣ<br>11. ዮናታን<br>12. የገና ታሪክ |

| | ለ7 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 - የዮሴፍ ሕይወት<br>ርዕስ - ሰላዮች በግብፅ | ለ7 - ደረጃ 4<br>ጥናት 1 - የዮሴፍ ህይወተ<br>ርዕስ - የወጣትነቱ ፈተና |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘፍጥረት 41፡ 46-57 እና 42፡ 1-26***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘኍልቁ 32፡ 23***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ኃጢአት ሰርተን ማምለጥ አንችልም።<br>2. ጌታ ኢየሱስ ብቻ መስጠት የሚችለውን ይቅርታ ከማድነቃችን በፊት ሀጢያታችንን አምነን መቀበል አለብን። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘፍጥረት 39፡ 1-23 እና 40፡ 1-23***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት 39፡ 21***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ዮሴፍ ለፈተናው እጅ አልሰጠም ነበር።<br>2. በባርነት፣ በፈተና እና በእስር ቤት ውስጥ ጌታ ከዮሴፍ ጋር ነበር። ዮሴፍ ጌታን ያምንና ይታዘዝ ነበር። |
| መግቢያ | ግብፃውያን ለምግብነት በራሳቸው ሰብሎች ላይ ነበር የሚደገፉት እና ሰባት የድርቅ አመታት ለሕዝቡ በጣም አሳሳቢ ሁኔታ እንደነበር ለተማሪዎች አስረዱ። በዚያን ጊዜ በቆሎን በሁሉም ነገር ውስጥ ለምግብነት ስለሚጠቀሙት እና ለረዥም ጊዜ መቀመጥ ስለሚችል ጠቃሚ ነበር። እንደ ገንዘብም ይጠቅም ነበር። ከአባይ ወንዝ የተነሳ በድርቅ ጊዜያት ግብፅ ብዙ ጊዜ ከሌሎች ጎረቤት ሀገሮች በጣም እንደምትሻል አስረዱ። | ጴጢፋራ የፈርኦን የዘበኞች አለቃ ነበር እና ዮሴፍ ከምድያም የባሪያ ነጋዴዎች የተገዛው እሱ ቤት ውስጥ እንዲሰራ ነበር። ዮሴፍ ስራው የተከናወነለት ወጣት ስለነበር ጴጢፋራ ካደረጋቸው ውሳኔዎች ሁሉ የሚበልጥ ውሳኔ ነበር የወሰነው። የጴጢፋራ ሚስት ዮሴፍን በሀሰት ከሰሰችውና እስር ቤት እንዲገባ አደረገችው። በእስር ቤት እያለ የሕልሞች ጉዳይ መጣ፤ ዮሴፍ የሁሉንም ትኩረት በእግዚአብሄር ላይ አደረገ: *'ሕልምን የሚተረጉም እግዚአብሄር የሰጠው አይደለምን'* ***(ዘፍጥረት 40፡ 8)***፣ እናም እራሱን ጥሩ አድርጎ ከማሳየት ይልቅ አጋጣሚውን ለጌታ ታላቅ ምስክርነት እዲሆን አደረገ። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ረሀቡ ለሰባት አመታት ይቆያል ***(ቁጥር 54)*** እና ከተትረፈረፈው የፈርኦን ጎተራ ውስጥ ካለው የበቆሎ አቅርቦት ወስዶ የሚያስፈልገውን መስጠት የሚችለው ***(ቁጥር 55)*** ዮሴፍ ብቻ ነው።<br>2. በድርቁ ምክንያት የዮሴፍ ወንድሞች በቆሎ ፍለጋ ወደ ግብፅ መውረድ ነበረባቸው። ***(42፡ 1-3)***<br>3. ዮሴፍ ወንድሞቹን አወቃቸው እነሱ ግን አላወቁትም ነበር። (42፡ 7) ለሶስት ቀን እስር ቤት አቆያቸው።<br>4. እሱን እንዴት እንደበደሉት እንዲያውቁ በሚያደርጋቸው መንገድ ነበር ዮሴፍ ወንድሞቹን ያደረጋቸው። ***(42፡ 21)*** ይህ ከሆነ ብቻ ነው ይቅር የሚላቸው።<br>5. ሀሳባቸውና ሕሊናቸው ጥፋታቸውን አስታወሳቸው እና እየደረሰባቸው ላለው ጭንቀት ምክንያት እደሆነ ተረዱ።<br>6. ሀጢያተኞች ቢሆኑም ዮሴፍ አለቀሰላቸውና ***(ቁጥር 24)*** ወደ አባታቸው ያዕቆብ ለመመለስ ለሚያደርጉት ጉዞ ምግብ ሰጣቸው፣ ነገር ግን ስምኦንን እስር ቤት አቆየውና ቢኒያም፣ የሁሉም ታናሽ የሆነው ልጅ ወደ ግብፅ መምጣት እንዳለበት ነገራቸው።<br>7. የተፈጠረውን ነገር ሁሉ ሲነግሩት ያእቆብ በጣም አዘነ እና ቢኒያምን መቼም ወደ ግብፅ እዲሄድ እንደማይለቀው ተናገረ። ***(42፡ 38)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:** ***ስዕል - የዮሴፍ ወንድሞች ግብፅን ጎበኙ።*** **(P)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ዮሴፍ በግብፅ ውስጥ ባሪያ የሆነበትን አጋጣሚ ምርጥ ነገር አደረገበት እና ብዙም ሳይቆይ የፈርኦንን እምነት አገኘ። ***(39፡ 2)***<br>2. የጴጢፋራ ሚስት ዮሴፍ በእሷ ላይ ጥቃት እንደፈፀመ በመግለፅ በሀሰት ወንጀላ እስር ቤት አስገባችው። ***(39፡ 11-20)*** ቢሆንም ግን ዮሴፍ ሁኔታው ምንም ቢሆን በእግዚአብሄር መደገፉንና መታመኑን የቀጠለ ታማኝ ወጣት ነበር እና እግዚአብሄር ይህንን ሁኔታ በመቀየርና ዮሴፍን የእስር ቤቱ አዛዥ በማድረግ ባረከው። ***(39፡ 21-23)***<br>3. በእስር ቤት ውስጥ ያሉ ሁለት እስረኞች ሕልም አለሙ እና ዮሴፍ መተርጎም ቻለ። ***(40፡ 8)***<br>4. የጠጅ አሳላፊው ሕልም ትርጉም ከእስር ቤት በመፈታቱ መልዕክቱ የሕይወት ነበር ነገር ግን የእንጀራ ጋጋሪው ሕልም እንጀራ ጋጋሪው በመገደሉ የሞት መልዕክት ነበር።<br>5. ዮሴፍ ጠጅ አሳላፊው እዲየስታውሰውና የፈርኦንን እርዳታ እንዲሻ ጠየቀው ነገር ግን ሲለቀቅ ዮሴፍን እስከነጭራሹ ረሳው። ***(40፡ 14 እና 23)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:** ***ስዕል - ዮሴፍ እና የጴጢፋራ ሚስት እና ዮሴፍ- እንጀራ ጋጋሪውና ጠጅ አሳላፊው።*** **(P)** |
| ክለሳ | ቁልፍ ጥቅሱ እንዴት ትምህርቱን እደሚያጠቃልል ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ። | ቁልፍ ጥቅሱ ከእነዚህ ነጥቦች አንፃር እንዴት ትምህርቱን እደሚያጠቃልል ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ:<br>1. የዮሴፍ ሕይወት በጴጢፋራ ቤት ውስጥ፤ እና<br>2. የዮሴፍ ሕይወት በእስር ቤት ውስጥ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ለኃጢአት ጀርባችንን የመስጠት እና ይቅርታውን ለማግኘት ወደ ጌታ ኢየሱስ የመዞር አስፈላጊነት።<br>2. ***1 ዮሀንስ 1፡ 9ን*** የመረዳት አስፈላጊነት: *'በሀጢያታችን ብንናዘዝ ሀጢያታችንን ይቅር ሊለን ከአመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ፃድቅ ነው።'*<br>3. በትምህርቱ ውስጥ የመዳንን ደረጃዎች አስተውሉ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ለፈተና መሸነፍ የለብንም ነገር ግን እንድናሸንፍ ጌታ እንዲረዳን በየቀኑ መጠየቅ ነው።<br>2. ለጌታ ውጤታማ ምስክር የመሆን ሚስጥር እሷን/እሱን ለአዳኙ በማስገዛት ጥሪት ጌታ ኢየሱስን ከሌላው ሰው ገጠመኝ ጋር የምናገናኝበትን አጋጣሚዎች ማስተዋል ነው።<br>3. የቀረቡትን ተጨማሪ ንባቦች አንብቡ፣ ***ኤፌሶን 6፡ 13-17*** እና ***ያዕቆብ 1:12-18***፣ እና በሕይወታችን ውስጥ ፈተናን እንዴት ማለፍ እንዳለብን ተመልከቱ። |

| | ለ7 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 - የዮሴፍ ሕይወት<br>ርዕስ - ቢኒያምና መጥፎ ዜና! | ለ7 - ደረጃ 4<br>ጥናት 2 - የዮሴፍ ሕይወት<br>ርዕስ - የቤተመንግስት ትውውቁ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘፍጥረት 42፡ 35-38፤ 43፡ 11-14፣ 24-31፤ 44፡ 1-17***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ኤፌሶን 4፡ 32***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ይሁዳ፣ ዮሴፍን ለባርነት ለመሸጥ ከወንድሞቹ ጋር የተባበረው፣ አሁን ቢኒያምን ለማዳን እርሱ ራሱ ባሪያ ለመሆን ሀሳብ አቀረበ። ***(44፡ 33)***<br>2. እግዚአብሄር ደንዳና ልብ ባላቸው ሰዎች ላይ መስራት ይችላል እናም ፍፁም የሆነ ለውጥ በህይወታቸው ውስጥ ያመጣል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘፍጥረት 41፡ 1-45***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት 41፡ 38***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ፈርኦን ዮሴፍ የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበት ሰው መሆኑን እንዳወቀ ሁሉ ***(41፡ 38)*** እናንተንም የሚያውቋችሁ በደግ ስራችሁና እግዚአብሄርን በሚመስል ሕይወታችሁ እግዚአብሄርን በእናንተ ውስጥ ማየት መቻል አለባቸው።<br>2. ዮሴፍ በአንዴ ወደላይ ወጣ - ባሪያ ከመሆን የግብፅ ጠቅላይ ሚኒስቴር ወደመሆን። ራሳችንን የምናገኝበትን ማንኛውምን ሁኔታ እግዚአብሄር ለሕይወታችን እንዳዘጋጀው የስልጠና ፕግራም አካል ማየት አለብን። |
| መግቢያ | የዮሴፍ ወንድሞች ኃጢአት ራሳቸው ላይ ጭንቀት ማምጣት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ለአባታቸው ያዕቆብም ትልቅ የልብ ስብራት ማምጣቱን ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ። ኃጢአት ቤተሰቦቻችንና ጓደኞቻችን፣ እኛ ላይም ጭምር ከባድ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል አስረዱ። | በፈርኦን ፊት እንዲቆም ዮሴፍ ከእስር ቤት ውስጥ ተጠራ። ዮሴፍ ስለሕልሙ ለፈርኦን እንዲናገር ከእግዚአብሄር የተሰጠው ብቃት ፈርኦንን በጣም ስላስደነቀው ለዮሴፍ ትልቁን ስልጣን 'ጠቅላይ ሚኒስቴርነት'ን ሰጠው። ***(ዘፍጥረት 41፡ 41)*** ዮሴፍ በከባድ ሁኔታ ውስጥ ለእግዚአብር ታማኝ ነበር (ጥናት 1) እናም እግዚአብሄር ለእሱ ታማኝ ነበር። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ድርቁ ቀጠለ እና ወንድሞቹም ምግብ ፍለጋ በድጋሚ ወደ ግብፅ ተመለሱ። ያዕቆብ ቢኒያም ወደ ግብፅ እንዲሄድ ለመልቀቅ ፍቃደኛ አልነበረም። ***(43፡ 11)*** ዮሴፍ ብቻ ነበር ፍላጎታቸውን ሊያሟላና ጭንቀታቸውን ሊወስድ የሚችለው።<br>2. ሁሉም ወንድሞቹ ወደ ዮሴፍ ቤት ለምግብ ተጋበዙ እና አሁንም አላወቁትም ነበር። ***(43፡ 16)***<br>3. ፈርተው የነበሩት ወንድሞቹ በቤተመንግስቱ ውስጥ በዮሴፍ የተዘጋጀውን ግብዣ አጣጣሙ። ታናሽ ወንድሙን ቢኒያምን ሲያይ ዮሴፍ አለቀሰ። ***(43፡ 30)***<br>4. የብር ዋንጫው በቢኒያም ከረጢት ውስጥ እንዲከተት ያደርግና ቢኒያም እንደሰረቀውና መቀጣት እንዳለበት ይናገራል። ***(44፡ 17)***<br>5. ይሄን ሁሉ ጊዜ ዮሴፍ ሊሰጣቸው ላለው ይቅርታ ዝግጁ መሆናቸውን እየፈተነና እየገመገመ ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - *የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብፅ ተመለሱ።* (P)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. አስማተኞቹና ጥበበኞቹ የፈርኦንን ሕልም መተርጎም አልቻሉም ነገር ግን እግዚአብሄር ለዮሴፍ ገልጦለት ነበር። ***(41፡ 8)***<br>2. የዮሴፍ እግዚአብሄርን ማወቅ ሕልሙን እንዲተረጉም ረድቶት ነበር እና በድጋሚ ክብሩን ለእግዚአብሄር ሰጠ። ***(41፡ 16)***<br>3. ዮሴፍ ለፈርኦን ለሰባት አመቱ ረሀብ በግብፅ ውስጥ ብዙ ነፍስንና በጣም ሩቅ ያሉትንም የራሱን ቤተሰቦች ያዳነ በሕይወት የማቆየትን እቅድ ነበር የሰጠው። ***(41፡ 33-36)***<br>4. ዮሴፍ ከፍ ከፍ ተደረገና በግብፅ ምድር ላይ ገዢ ሆኖ ተሾመ። አዲስ ስም ተሰጠውና በተጨማሪም ምን ያሕል እንደ ተከበረ ለማሳየት የአንድ ታዋቂ የግብፅ ባለስልጣን ሴት ልጅ ለሚስትነት ተሰጠችው። ***(41፡ 41-45)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - *ዮሴፍ የፈርኦንን ሕልሞች ተረጎመ።* (P)** |
| ክለሳ | ለተማሪዎቹ አስረዱ:<br>1. ሀጢያታችንን እስክንናዘዝና ወደ 'መንፈሳዊው ዮሴፍ'፣ ጌታ ኢየሱስ ለይቅርታ እስክንመጣ ድረስ በሕይወታችን ውስጥ ባዶነት አለ።<br>2. ይቅር ለተባሉት የበረከት ድግስ ይጠብቃቸዋል፣ በተለይም ወደፊታቸው በገነት። | ተማሪዎቹ ስለ (ሀ) ሕልሙ፣ (ለ) ትርጉሙ፣ እና (ሐ) የዮሴፍ ትውውቅ በጥናት 2 ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ የሚረዳቸውን ጥያቄዎችን ጠይቋቸው። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ኃጢአት ጭንቀትን እንደሚፈጥር አስቡ።<br>2. ንስሀ ስንገባና ሀጢያታችንን ስንናዘዝ ጌታ ኢየሱስ ምሕረት ሊያደርግ እና ይቅር ሊለን ዝግጁ ነው።<br>3. ጌታ ኢየሱስ ይቅር ሲለን እኛም የበደሉንን ይቅር ማለት አለብን። ***(ኤፌሶን 4፡ 32)*** | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ዮሴፍ ከእግዚአብሄር ጋር ከነበረው ትክክለኛ ግንኙነት የተነሳ ለሁሉም ነገር ዝግጁ እንደነበረው ሁሉ እኛም ከእሱ ምሳሌ መማር አለብን። ክርስቲያኖች ከሆንን ፀሎት እና ቃሉን ማጥናት በሕይወታችን የእግዚአብሄርን ፈቃድና አቅጣጫ ለማግኘት ጠቃሚ ናቸው።<br>2. ዮሴፍ ሁሌ ለእግዚአብሄር ክብሩን በመስጠት ጠንቃቃ ነበር እና እኛም ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ መጠንቀቅ አለብን። ክብርን ለራሳችን መውሰድ የእግዚአብሄርን ክብር መስረቅ ነው።<br>3. የቀረቡትን ተጨማሪ ንባቦች አንብቡ እና መዝሙረኛው ዳዊትና ሀዋሪያው ጳውሎስ ከሞተ ከብዙ አመታት በኋላ ስለ ዮሴፍ ምን እንዳሉ ተመልከቱ እና እነዚህን ንባቦች በራሳችሁ ሕይወት ላይ ተግብሩ። ***መዝሙር 105፡ 16-22*** እና ***ሐዋ. ሥራ 7፡ 9-10*** |

| | ለ7 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 - የዮሴፍ ሕይወት<br>ርዕስ - ይቅርታ እና መልካም ዜና! | ለ7 - ደረጃ 4<br>ጥናት 3 - የዮሴፍ ሕይወት<br>ርዕስ - የእርሱ አሳቢነት |
|---|---|---|
| | ***የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:*** ***ዘፍጥረት 44፡ 18-34፤ 45፡ 1-14፣ 25-28***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት 45፡ 9***<br><br>***እየተማርን ያለነው:***<br>1. የዮሴፍ ወንድሞች ሊያስወግዱት ቢፈልጉም እንኳን እግዚአብሄር ክፉ ስራቸውን ሕይወታቸውን ለማቆየት፣ ግብፅን ለማዳን እና ለእስራኤል ሕዝብ ጅማሬ መንገድ ለማዘጋጀት ተጠቀመው።<br>2. ዮሴፍ እንደተገፋ እና በኋላም ወንድሞቹን ይቅር እዳላቸው፣ ይህ እኛ እግዚአብሄርን ብንገፋውም እንኳን እርሱ ግን እንዴት ይቅር እንደሚለንና እደሚባርከን ከዚህ እናያለን። | ***የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:*** ***ዘፍጥረት 42 እና 43***<br>**ቁልፍ ጥቅሶች:** ***ሮሜ 14፡ 11-12***<br><br>***እየተማርን ያለነው:***<br>1. የዮሴፍ ወንድሞች ይቅር ከመባላቸው በፊት ሀጢያታቸውን እንዲያዩና እንዲያምኑ መደረግ ነበረባቸው።<br>2. የዮሴፍ ወንድሞች ለእሱ በመሰጠት ሰገዱለት ስለዚህ አንድ ቀን ሁላችንም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እንሰግዳለን እና እንደ ጌትነቱ እናከብረዋለን። |
| *መግቢያ* | ዮሴፍ ወንድሞቹ ከልባቸው እንደተፀፀቱ ሲያይ ማን እንደነበረ ገለጠላቸውና ***"እኔ ዮሴፍ ነኝ።" (ዘፍጥረት 45፡ 4)*** አላቸው። 'የሰማዩ ዮሴፍ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም' ቀጥሎ ባሉት ክፍሎች ውስጥ እንዴት እራሱን 'እኔ ነኝ' ብሎ እንደጠራ ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ: ***ዮሀንስ 6፡ 35 - የሕይወት እንጀራ፤ ዮሀንስ 8፡ 12 - የአለም ብርሀን፤ ዮሀንስ 10፡ 7 - በር፤ ዮሀንስ 10፡ 11 - መልካም እረኛ፤ ዮሀንስ 11፡ 25 - ትንሳኤና ሕይወት፤ ዮሀንስ 14፡ 6 - መንገድ፤ ዮሀንስ 15፡ 1 - የወይን ግንድ።*** | ለመጨረሻ ጊዜ ዮሴፍ ወንድሞቹን ያየው፣ ከሀያ አመት በፊት ለምድያም የባሪያ ነጋዴዎች በሀያ ብር የሸጡት ጊዜ ነበር። ዮሴፍ፣ አሁንም ክፉና አስመሳይ ናቸው ወይስ በእነዚህ አመታት ተቀይረዋል ብሎ ሳያስብ አልቀረም። ይህን ለማወቅ ጥቂት ፈተናዎችን ሊፈትናቸው ወሰነ! |
| *ማጠናቀቅ* | ***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ***<br><br>***ተወያዩና አስረዱ:***<br>1. የብሩ ዋንጫው የዮሴፍ ስልጣን ምልክት ነበር እና እሱን መስረቅ ከባድ ወንጀል ነው። አሁን ቢኒያም ጉዳት ይደርስበታል ብለው ወንድሞቹ ተጨንቀው ነበር ስለዚህ ወደ ዮሴፍ ቤመንግስት ሲመለሱ ይሁዳ የቢኒያምን ቅጣት ለመቀጣት እርምጃ ወሰደ። ***(44፡ 33)***<br>2. ወንድሞቹ ከመቀጣት ይልቅ ይቅርታን ተቀበሉ ***(45፡ 5)*** እና ምንም ቢያደርጉም እንኳን እግዚአብሄር እንዴት በሕይወቱ ፍቃዱን እየፈፀመ እንደነበር ዮሴፍ አስረዳቸው።<br>3. ወንድሞቹ የዮሴፍ በሕይወት የመኖሩን መልካም ዜና ይዘው ወደ ያዕቆብ ተመለሱ እና በዮሴፍ የተላኩትን ስጦታዎች አሳዩት። ***(45፡ 26-27)***<br><br>***ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።***<br>***ትምህርት 3ን አጠናቁ።***<br>***አሳዩ: ስዕል - የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብፅ ተመለሱ። (P)*** | ***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ***<br><br>***ተወያዩና አስረዱ:***<br>1. የዮሴፍ ወንድሞች በቆሎ ለመግዛት ሲሉ ወደ ግብፅ መጡ። ዮሴፍ 'በቁጣ' አናገራቸው፣ ይቅር ከመባላቸው በፊት ሀጢያታቸውን ወደማወቅ ሊያመጣቸው እደሆነ ያሳያል። ***(42፡ 6-7)***<br>2. ዮሴፍ ለሶስት ቀን እስር ቤት አስገባቸው።በሕሊናቸው ዮሴፍ ላይ ኃጢአት እንደሰሩ ያውቁ ነበር ስለዚህም ጥፋታቸውን አመኑ። ***(42፡ 21)***<br>3. ዮሴፍ ወንድሞቹን ለማስተካከል ቢሞክርም፣ ***በዘፍጥረት 42፡ 24*** ላይ ማልቀሱ ስለተነገረን ያደረገው ግን በፍቅር ነበር። እዚህ ጋር ዮሴፍ ለወንድሞቹ የማይገባቸውን ፍቅርን ማሳየት በመቀጠሉ እውነተኛ ጸጋን በተግባር እናያለን።<br>4. ለሁለተኛ ጊዜ ቢኒያምን ይዘው ወደ ዮሴፍ ሲመጡ በአክብሮት ሰገዱለት እና ለስልጣኑ እውቅና ሰጡ። ***(43፡ 26-28)*** እዚህ ጋር ***በዘፍጥረት 37፡7*** ላይ ያለው የዮሴፍ ሕልም ወደ እውነታ ሲቀየር እናያለን። ይህ የእግዚአብሄር ቃል በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መፃፉን እናያለን!<br>5. ዮሴፍ በመጨረሻ ወንድሙን ቢኒያምን ሲያይ ተሰማውና ወደሌላ ክፍል ሄዶ አለቀሰ። ***(43፡ 30)***<br><br>***ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።***<br>***ጥናት 3ን አጠናቁ።***<br>***አሳዩ: ስዕል - የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብፅ ተመለሱ። (P)*** |
| *ክለሳ* | ይህንን ትምህርት ከቁልፍ ጥቅሱ ጋር አገናኙ:<br>***"እግዚአብሄር በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ጌታ አድርጎኛል!"*** እና ***"ወደ እኔ ና፣ አትዘግይም።"*** ለሁለቱ አረፍተ ነገሮች የያዕቆብን የደስታ ምላሽ ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ። | ሁለቱን ቁልፍ ጥቅሶች እወቁ እና እንዴት የዚህ ትምህርት ማጠቃለያ እንደሆኑ ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ። |
| *ከሕይወት ጋር ማዛመድ* | ***ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:***<br>1. ዮሴፍ በግብፅ ውስጥ በሕይወት እንደነበረና የሁሉም ገገር እንደነበር ሁሉ ጌታ ኢየሱስ በገነት ሕያው ሆኖ እንዳለና የሁሉም ጌታ እደሆነ የማወቅን አስፈላጊነት።<br>2. ጌታ ኢየሱስ ይቅርታ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ስናምነው የተትረፈረፈ በረከትንም እንደሚሰጠን የመረዳትን አስፈላጊነት።<br>3. ጌታ ኢየሱስ በፀሎቱ ውስጥ ለደቀመዛሙርቱ እንዳስተማረው፣ ሌሎችን ይቅር በማለት የእግዚአብሄርን የይቅርታ ምሳሌ የመከተላችንን አስፈላጊነት በድጋሚ ተማሪዎችን ማስታወስ። ***(ማቴዎስ 6፡ 12)*** | ***ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:***<br>1. ጌታ ኢየሱስ ***በሮሜ 5፡ 21*** ስለሚሰጠው ጸጋ ምን እንማራለን?<br>2. ለበደሉት ወንድሞቹ ዮሴፍ ፍቅር እንዳሳየው ሁሉ እንደኛ ላሉ ሀጢያተኞች በቀራንዮ ላይ ሲሞት ከዚህ በጣም የላቀ ፍቅር በጌታ ኢየሱስ ተገልጦ እናያለን። ***ሉቃስ 23፡ 34ን*** አንብቡና አሰላስሉት።<br>3. ***በዘፍጥረት 37፡ 7-8*** ላይ የሚገኘው የዮሴፍ ሕልም ***በዘፍጥረት 43፡ 26*** ላይ ተፈፀመ። የቀረቡትን ተጨማሪ ንባቦች አንብቡ፣ ***መዝሙር 51*** እና ***ፊልጵስዩስ 2፡ 9-11*** እና እነዚህ ክፍሎች ኃጢአትን የመናዘዝና 'ኢየሱስ ጌታ ስለመሆኑ' እውቅና ስለመስጠታችን አስፈላጊነት እንዴት አፅንኦት እንደሚሰጡ አስቡ። |

| | ለ7 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 - የዮሴፍ ሕይወት<br>ርዕስ - በአንድነት በግብፅ | ለ7 - ደረጃ 4<br>ጥናት 4 - የዮሴፍ ሕይወት<br>ርዕስ - ሙሉ ይቅርታ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ዘፍጥረት 46፡ 1-7፤ 26-34***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ዘፍጥረት 50፡ 20***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. የዮሴፍ ታማኝነት መላው ቤተሰቡ ላይ ተፅዕኖ አሳደረ እናም ወደ ብዙ በረከቶች አስገባቸው።<br>2. ዮሴፍ በ ***1ሳሙኤል 2፡ 30 "ያከበሩኝን አከብራለው።"*** ለሚለው የጌታ ቃልኪዳን ትክክለኛ ምሳሌ ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ዘፍጥረት 44 እና 45***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሮሜ 5፡ 10***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. የዮሴፍ ወንድሞች ሀጢያታቸውን ሲናዘዙ ከዮሴፍ ጋር የነበራቸው ወዳጅነት ተመለሰ እናም ሀጢያታችንን ስንናዘዝና ንስሀ ስንገባ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ወደ እውነተኛና ትርጉም ወዳለው ወዳጅነት መግባት እንችላለን።<br>2. ዮሴፍ በግብፅ ለወንድሞቹ አብዝቶ እንደሰጠ ጌታ ኢየሱስም የእርሱ ለሆኑት አብዝቶ ሰጥቷል እና ዘላለማዊ ሀሴትና ደስታ ወዳለበት ወደ ገነት ይወስዳቸዋል። |
| መግቢያ | እግዚአብሄር በዮሴፍ ሕይወት ውስጥ እንዴት እቅዱን እየፈፀመ እንደሆነ ለተማሪዎች አብራሩ። መላው ቤተሰቡ ከእሱ ጋር በጌሴም፣ በግብፅ ለመኖር ከከነአን መጡ። ቢሆንም ግን ከነአን ለአብርሀምና ለዘሩ ቃል ተገብቶለት ነበር ነገር ግን እግዚአብሄር ለጊዜው የዮሴፍን ቤተሰብ ለእግዚአብሄር ጀርባቸውን ከሰጡት ከከነአናውያን መጥፎ ተፅዕኖ እያራቀ ነበር። ቢሆንም ግን እግዚአብሄር ቃል እንደገባው የእስራኤል ሕዝብ ወደ ከንአን ተመልሷል። | በቀደመው ጥናት ወንድሞቹ ሀጢያታቸውን እንዲናዘዙ ለመርዳት ዮሴፍ እንዴት የጥበብ እርምጃ እንደወሰደ ተምረናል። ይቅር እንዲላቸው እና በእውነት እንዲታረቁና የተቋረጠው ወዳጅነታቸው እንዲቀጥል ለዮሴፍ መንገዱ አሁን ክፍት ነበር። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. ቤቱን ለቆ ወደ አዲስና ሩቅ ምድር እንዲሄድ እግዚአብሄር ለያዕቆብ ነገረው እና እንደሚንከባከበው አረጋገጠለት። ***(46፡ 2-3)***<br>2. መላው ቤተሰብ ንብረቱን ሁሉ ይዞ ወደ ግብፅ ሄደ። ***(46፡ 5-7)***<br>3. የያዕቆብ ቤተሰቦች ጌሴም ደረሱ እና በዮሴፍና በያዕቆብ መሀል በእንባ የተሞላ አንድነት ሆነ። ***(46፡ 29)***<br>4. ከያዕቆብ ሞት በኋላ ዮሴፍ እንዳይበቀላቸው ወንድሞቹ ፈሩ ነገር ግን የሚያስገርመው ነገር እነሱን ይቅር ማለት ብቻ ሳይሆን እነሱንና ቤተሰቦቻቸውን ለመንከባከብ ሀሳብ አቀረበላቸው። ***(50፡ 15-21)***<br><br>***ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።***<br>***ትምህርት 4ን አጠናቁ።***<br>***አሳዩ፡ ስዕል - ዮሴፍ ከያዕቆብ ጋር ዳግም ተገናኘ።*** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. ወንድሞቹ በከነአን ወዳለው ወደ አባታቸው ያዕቆብ ከመመለሳቸው በፊት ይሁዳ በግብፅ ለመቆየትና በቢኒያም ቦታ ባሪያ ሆኖ ለማገልገል ሀሳብ አቀረበ። ያዕቆብን ለብዙ አመታት የልብ ስብራት በመዳረግ ዮሴፍን ለባርነት ከሸጡበት ጊዜ ይሄ ትልቅ ለውጥ ነበር። የእግዚአብሄር ጸጋ በልቡ ውስጥ አሁን በስራ ላይ ነበር። ***(44፡ 33)***<br>2. ዮሴፍ እራሱን ገለጠላቸውና እግዚአብሄር ለመልካም እንደለወጠው ነገራቸው። ***(45፡ 4-5)***<br>3. ዮሴፍ አለቀሰ፣ ቢኒያምን አቀፈውና ወንድሞቹን ሁሉ ሳማቸው። ***(45፡ 14)***<br>4. የዮሴፍ ወንድሞች አባታቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ወደ ግብፅ እንዲያመጡ እና እሱ እንደሚያዘጋጅላቸው ፈርኦን ነገራቸው። ***(45፡ 17-19)***<br>5. ዮሴፍ በሕይወት እንዳለ ወንድሞቹ ለያዕቆብ ነገሩትና ሁሉንም ወደ ግብፅ ለማምጣት የተላከላቸውን ሰረገላዎች ሲያይ ዮሴፍ በሕይወት እንዳለና በድጋሚ እንደሚያገኘው ያዕቆብ አወቀ! ***(45፡ 25-28)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 4ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብፅ ተመለሱ። እና ዮሴፍ ከያዕቆብ ጋር ዳግም ተገናኘ።** |
| ክለሳ | የተጠየቁት ጥያቄዎች በዚህ ትምህርት 4 ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች መልስ እንዲሞሉ እንዲያግዛቸው ተማሪዎቹን በጥቃቄ ጠይቋቸው። | ስለዮሴፍ በዚህ ታሪክ ውስጥ ያለው'መልካም ዜና' ከጌታ ኢየሱስ 'መልካም ዜና' ጋር ተመሳሳይ ወደመሆኑ የተማሪዎቹን ትኩረት ሳቡ፡<br>1. ዮሴፍ በሕይወት እንደነበረው፣ ኢየሱስም አሁን ሕያው ነው፤<br>2. ዮሴፍ በግብፅ ገዢ እንደነበረው ጌታ ኢየሱስም የነገስታት ንጉስና የጌቶች ጌታ ነው፤<br>3. ዮሴፍ ለቤተሰቡ እንዳዘጋጀው ጌታ ኢየሱስም ለመዳን የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ አዘጋጅቷል፤ እና<br>4. ዮሴፍ ቤተሰቡን ወደ ግብፅ እንዳመጣ ጌታ ኢየሱስም ለመዳን ወደ እርሱ እንድንመጣና ለዘለአለም ወደ ገነት ሊወስደን ይፈልጋል። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. ዮሴፍ ወደፊት ለእሱ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ብዙ ጊዜ ያስብ እንደነበር እኛም ምን ሊፈጠር እንደሚችል ሁሌም ላናውቅ እንችላለን። ነገር ግን እንደ ክርስቲያኖች እግዚአብሄር ታማኝነታችንን እንደሚያከብር እርግጠኞች መሆን እንችላለን።<br>2. እግዚአብሄር የዚህን አለም ክፉ ሀሳቦችንና ነገስታቶችን ሽሮ ያሰበውን ውጤት ማምጣት ይችላል። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. የእርሱ ከሆንን በቀራንዮ መስቀል ላይ ሀጢያታችንን ለማስወገድና ለገነት ብቁ ሊያደርገን የሰራውን ስራ በማየት እርሱን በሚያስደስተው መንገድ መኖር አለብን።<br>2. እግዚአብሄር ከዮሴፍ ጋር ነበር እና እንደተጠቀመው ንባብ ይህ በተጨማሪም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ፣ ከመወገሩ በፊት በእስጢፋኖስ ተገልጿል። ***(ሐዋ. ሥራ 7፡12-15)*** |

| | **ለ8 - ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 1 - የወንጌሉ ጸሃፊዎች**<br>**ርዕስ - ማቴዎስ** | **ለ8 - ደረጃ 4**<br>**ጥናት 1 - ከፊት ያለው መንገድ**<br>**ርዕስ - ክርስቲያኖች በአንድነት** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ *ማቴዎስ 9፡ 9-13፤ እና 27፡ 37-42***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡ *ማቴዎስ 16፡ 16***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. ኢየሱስ አይሁዳዊ፣ ቀራጭ የሆነውን ማቴዎስን ሲጠራው በፍጥነት ምላሽ ሰጠና ኢየሱስን ተከተለ።<br>2. ቢሆንም እንኳን አብዛኞቹ አይሁዶች ኢየሱስን አልተቀበሉትም ነበር በውጤቱም ተሰቀለ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ *ሐዋ. ሥራ 2፡ 41-44፣ ሐዋ. ሥራ 4፡ 32-35***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡ *ሐዋ. ሥራ 2፡ 42***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. ህዝቡ ክርስቲያን ሲሆኑ በእምነታቸው እድገትን በመፈለግ በአንድነት በሕብረት ውስጥ ጊዜን የማሳለፍን አስፈላጊነት አስተዋሉ።<br>2. በሚቻለው መንገድ ሁሉ እርስ በእርስ ለመረዳዳት ይተጉና እንዲሁም አንዱ የሌላው ይጋራ ነበር። |
| መግቢያ | ማቴዎስ ቀረጥ ሰብሳቢ እንደነበር ለተማሪዎች አስረዱ። እነዚህ ሰዎች አጭበርባሪ በመሆናቸው፣ከሰዎች በሚሰበስቡት ከፍ ባለ ቀረጥ ምክንያትና በዚያ ጊዜ የአይሁድ የበላይ የነበረውን የሮማን መንግስት ፍላጎቶችን ስለሚያገለግሉ በአይሁድ ዘንድ የተጠሉ ነበሩ። | ጴጥሮስ ከኢየሱስ ደቀመዝሙር መሀል አንዱ እንደነበርና በስቅለቱ ጊዜ ኢየሱስን እንደካደው ለተማሪዎች አስረዱ። ቢሆንም ግን ኢየሱስ ይቅር ብሎት አሁን በድፍረት ለሰዎች ስለኢየሱስ እየተናገረ ነው። ጥፋቶቹ ይቅር መባል እስካይችል ድረስ በጣም መጥፎ አልነበሩም እና አሁን በኃይል እግዚአብሄር ሊጠቀመው ይችላል። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. ማቴዎስ ለአዳኙ ጥሪ በፍጥነት ምለሽ ሰጠ።<br>2. ማቴዎስ በቶሎ የጌታ ኢየሱስ ደቀመዝሙር ለመሆን ሀቀኝነት የጎደለውን ስራውን ትቷል። ከአስራሁለቱ አንዱ ደቀመዝሙር ነበር። ***(9፡ 9)***<br>3. የማቴዎስን ወንጌል ለመፃፍ ክብር አገኘ እና ኢየሱስ ለረዥም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው አይሁዶች መሲሁ ብለው የሚጠሩት ንጉስ እንደሆነ አሳየ።<br>4. ስለጌታ ኢየሱስ መምጣት የማቴዎስን ዘገባ በአጭሩ አስረዱ እና አብዛኞቹ ስለጌታ ኢየሱስ የተነገሩ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ወደዚህ ምድር ሲመጣ መፈፀማቸውን ማቴዎስ እንዴት እንዳስረዳ አጽንኦት ስጡ። ***(ማቴዎስ 1 እና 2)***<br>5. ማቴዎስ የኢየሱስን የትውልድ ሀረግ፣ የአደባባይ አገልግሎቱን ጽፏል እና በመከራው፣ ሞቱ፣ ቀብሩና ትንሳኤው ይዘጋል - የመዳናችን መሰረት ‘ወንጌል’ ተብሎ በሚጠራው በእሱ መጽሐፍ ውስጥ ተጽፏል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ማቴዎስ ኢየሱስን እንዲከተል ተጠራ።** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. ጴጥሮስ የኢየሱስ አንዱ ደቀመዝሙር ለሀጢያታቸው ንስሀ መግባትና ሕያው የሆነውን ክርስቶስ ማመን እንዳለባቸው በማስረዳት ለብዙዎች መልካሙን ዜና ሰበከ። ብዙዎች ክርስቲያን ሆኑና ለመዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ታመኑ - በቤተክርስቲያን ውስጥ በነበሩት በ120ዎቹ ላይ 3000 ተጨመሩ! በጣም ብዙ ሰዎች በዚህ ፍጥነት ክርስቲያን ሲሆኑ ማየት እንዴት የሚያስደንቅ ነገር እንደነበር ከተማሪዎች ጋር አስቡ። ***(2፡ 38-41)***<br>2. አዲሶቹ ክርስቲያኖች በሕብረት ውስጥ በአንድ ላይ መስራት ጀመሩ - ቤተክርስቲያን እየተመሰረተ ነበር። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አንድ ሆኑ፣ የሀዋርያቶቹን ትምህርት ይሰማሉ እና በሕብረት የኢየሱስን ሞት በማሰብና በፀሎት በአንድ ላይ ይሰበሰባሉ። እንዴት የእግዚአብሄርን ቃል እንዲማሩ፣ እንዲፀልዩ እና በእምነታቸው እንዲያድጉ ከሚረዷቸው ሰዎች ጋር መሆን እንደነበረባቸው ለተማሪዎች አስረዱ።<br>3. ክርስቶያኖች ሁሉ በአንድ ላይ ይሰበሰቡና እርስ በእርስ ይካፈሉ ነበር። ይህ ማለት ሁሉንም ነገር ያካፍሉ ነበር ማለት አይደለም ነገር ግን እንደ ቤተሰብ ለተቸገሩት ያካፍሉ ነበር። በክርስቶስ ወንድማማች እና እሕትማማች የመሆንን አስፈላጊነት እና ይህ ማለት ደግሞ በክርስቶስ እርስ በእርስ መካፈልና መዋደድ እንደሆነ ተረድተው ነበር። ***(ሐዋ. ሥራ 2፡ 42-47)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - የበአለ ሀምሳ ቀን** |
| ክለሳ | ተማሪዎቹን በትምህርት 1 ላይ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚረዷቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ከልሱ። | ጥንድ ሆናችሁ አሁን ክርስቲያኖች እንደሕብረት የሚያድጉበትን እና በእምነታቸው የሚጠነከሩበትን ተግባራዊ መንገዶችን ዝርዝር አዘጋጁ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. በፍጥነት ምላሽ መስጠትና ሕይወታችንን ለጌታ ኢየሱስ መስጠትን እንድናስብ?<br>2. ኢየሱስ የአይሁዶች ንጉስ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የነገስታት ንጉስና የጌቶችም ጌታ መሆኑን እና የእኛ እምነትና አገልግሎት የተገባው መሆኑን እንድናደንቅ?<br>3. ጌታ ኢየሱስ እራሱን ማዳን እንዳላስፈለገውና እንደ እኛ አይነት ሀጢያተኞችን ለማዳን በመስቀል ላይ መቆየቱ አስፈላጊ እንደነበር እንድንረዳ? ቀጥሎ ያለውን ለተማሪዎች ጥቀሱ፡ *‘እራሱን ማዳን አልቻለም፣ እሱ በመስቀል ላይ መሞት ነበረበት፣ ወይም ምሕረት ወደ ጠፉ ሀጢያተኞች መምጣት አይችልም፤ አዎ፣ የክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ ደም መፍሰስ አለበት፣ ሀጢያተኞት ከሀጢያታቸው ነፃ ይወጡ ዘንድ።’ - አልበርት ሚድሌን* | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. እኛ ክርስቲያኖች ከሆንን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በሕብረት እና እርስ በእርስ በመማማር ጊዜ ማሳለፉችንን እያረጋገጥን ነው? የእግዚአብሄርን ቃል ካላጠናንና በአንድነት ካልፀለይን አናድግም።<br>2. በክርስቶስ እንደ እሕትማማቾች እና ወንድማማቾች በተቻለው መንገድ ሁሉ እርስ በእርስ ለመረዳዳት ስላለብን ሀላፊነትም ማሰብ አለብን። የእግዚአብሄር ቤተሰብ በተሻለ ሁኔታ የሚሰራው የቤተሰቡ አካላት አንድ ላይ ሲሰሩ ነው።<br>3. ኢየሱስን ለማገልገል የሚያግዳችሁ በጣም ብዙ ስሕተቶችን የሰራችሁ ይመስላችኋል? ጴጥሮስ ኢየሱስን ክዶታል፣ ሆኖም በሺህ ለሚቆጠሩ ሰዎች መልካሙን ዜና እንዲያደርስ እየተጠቀመበት ነበር - እግዚአብሄርም በእናንተ ሕይወት ተመሳሳይ ነገርን ሊያደርግ ይችላል! |

| | ለ8 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 - የወንጌሉ ጸሃፊዎች<br>ርዕስ - ማርቆስ | ለ8 - ደረጃ 4<br>ጥናት 2 - ከፊት ያለው መንገድ<br>ርዕስ - የክርስቲያን ጥምቀት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ሐዋ. ሥራ 12፡ 5-12፤ ማርቆስ 1፡ 29-42***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ማርቆስ 10፡ 45***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. ማርቆስ በወንጌሉ ኢየሱስ 'ፍፁም አገልጋይ' ስለመሆኑ ያተኩራል እና ከተናገረው ይልቅ ስለሰራው ነው የፃፈው።<br>2. ጌታ ኢየሱስ እንዲያገለግሉት ሌሎችን እንዴት እንደሚመርጥ ማርቆስ ያሳያል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ማቴዎስ 28፡ 16-20፣ ሐዋ. ሥራ 8፡ 34-39፣ 18፡ 8***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሐዋ. ሥራ 2፡ 41***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. ጥምቀት ለክርስቶስ የመታዘዝ ተግባር ነው።<br>2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሰዎች ክርስቲያን ሆነዋል እና በእምነታቸው መሰረት ይጠመቁ ነበር።<br>3. ጥምቀት ሰዎች ክርስቶስን እንደሚከተሉ ለሕዝብ ማሳያ ነው። |
| መግቢያ | ከሰማይ ወደ ምድር የመጣው ለመገልገል ሳይሆን ለማገልገል እና በቀራንዮ መስቀል ላይ ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት እንደሆነ በማርቆስ ወንጌል ላይ ስለ ጌታ ኢየሱስ ታሪክ አለ። (እንደ ቁልፍ ጥቅሱ) በምድር ላይ እያለ ጌታ ኢየሱስ ለእግዚአብሄር ፍቃድ ፍፁም ታዛዥ ነበር እና በእግዚአብሄር መንፈስ ኃይል ነበር ተአምራቶችን ያደረገው። ማርቆስ፣ ጸሃፊው፣ በጥሩ ጀመረ፣ ለተወሰነ ጊዜ ከአገልግሎት ራቀ፣ ነገር ግን በመጨረሻ ጌታን ለማገልገል መመለሱን ***(2 ጢሞቴዎስ 4፡ 11)*** ማየት ያስደንቃል ። | የጥምቀት ፕሮግራም ተካፍለው ወይም ተጠምቀው የሚያውቁ ከሆነ ተማሪዎችን ጠይቁ። ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ጠይቋቸው ፤ እንዴት ነበር? ምን ተፈጠረ? ምንን ይወክላል ብለው ነው ያሰቡት? |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. ማርቆስ በእየሩሳሌም ያሉ ክርስቲያኖች ያዕቆብን ከገደለው ከሄሮድስ፣ ጴጥሮስ በሰላም እንዲለቀቅ ለመፀለይ የሚጠቀሙበት ቤት ቤተሰብ ነበር። ***(ሐዋ. ሥራ 12፡ 5-12)***<br>2. ማርቆስ ወንጌሉን በማሰራጨት እግዚአብሔርን ማገልገል ይፈልግ ነበር እና በመጀመሪያ የሚሲዮን ጉዞአቸው ከጳውሎስ ጋር ቢሄድም እንኳን ትቷቸው ግን ወደ እየሩሳሌም ተመልሷል። ***(ሐዋ. ሥራ 12፡ 25፣ እና 13፡ 13)***<br>3. ጳውሎስ የማርቆስን መመለስ በአገልግሎት ውስጥ እንደ እንከን አይቶታል እና በሁለተኛው የሚሲዮን ጉዞው ላይ ማርቆስ አብሮት እንዲሄድ አይፈቅድለትም ነበር። ***(ሐዋ. ሥራ 15፡ 37-39)*** ቢሆንም ግን ማርቆስ በድጋሚ ተመለሰና የጳውሎስን እምነት አገኘ እና ጌታ ኢየሱስን ማገልገል ቀጠለ።<br>4. ማርቆስ በአገልግሎቱ ወድቆ ቢያውቅም እንኳን በማርቆስ ወንጌል ላይ ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ እያለ ስላደረገው ነገር በተለይም ስለ ተአምራቶቹ ረዘም ያለ ነገር ጽፏል። የስምኦንን አማች መፈወስ፣ የለምፃሙን መንፃት እና ደቀመዛሙርቱ በገሊላ ባሕር በጀልባ ላይ እያሉ የማዕበሉን መቆም አጠቃሎ ጽፏል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ጴጥሮስ በተአምር ከእስር ቤት ወጣ።** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. ኢየሱስ ከምድር ከመሄዱ በፊት ለደቀመዛሙርቱ ታላቁን ተልእኮ ሰጣቸው። የዚህን ጊዜ ነበር ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱና ደቀመዝሙር እንዲያደርጉና በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ የነገራቸው። ይህን ሲያደርጉ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን ኢየሱስ ቃል ገብቶላቸዋል። ይህንንም እንዲያደርጉ ስልጣንም ሰጥቷቸዋል። ***(ማቴዎስ 28፡ 18-20)***<br>2. ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ሰዎችን እንዲያጠምቁ ነግሯቸዋል። ጥምቀት፣ ለኃጢአት በመሞታቸው እና ለአዲስ ሕይወት በመነሳታቸው አማኞችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ ያደርጋቸዋል። ክርስቲያን ሲሆኑ አዲስ ሕይወት አላቸው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም ምክንያት የቀድሞ ህይወታቸውን ትተው እንደ አዲስ ይጀምራሉ። ጥምቀት ይህንን ለሁሉም ፊት ለፊት ያሳያል። ***(ሮሜ 6፡ 3-7)***<br>3. ጥምቀት በተጨማሪም ለክርስቶስ መገዛትን፣ በእግዚአብሔር መንገድ ለመኖር መፍቀድን እና ከእግዚአብሔር የቃልኪዳን ህዝብ ጋር መጠራትን ያሳያል።<br>4. ***በሐዋርያት ሥራ 8*** ያለው ታሪክ ውስጥ ፊሊጶስ ለኢትዮጲያዊው ጃንደረባ የኢየሱስ ክርስቶስን መልካም ዜና ይነግረዋ። እሱም ክርስቲያን ሆነ እና ወዲያውኑ ተጠመቀ።<br>5. ***በሐዋርያት ሥራ 18፡ 8*** ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መርቷል። ጥምቀት ልክ ከእምነታቸው ቀጥሎ እንደሚመጣ ይታያል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ የሚሆን ስዕል የለም።** |
| ክለሳ | ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠቀም ትምህርቱን ከልሱ፡<br>1. ማርቆስ በሙሉ ወንጌሉ ጌታ ኢየሱስን እንዴት ነው የሚያቀርበው?<br>2. ማርቆስ ከምን አይነት ቤተሰብ ነው የመጣው? ለምን?<br>3. ማርቆስ በህይወቱ ምን ማድረግ ነበር የሚፈልገው?<br>4. ማርቆስ በመጀመሪያው የሚሲዮን ጉዞ ጳውሎስን ቢያሳዝነውም፣ በድጋሚ ወደ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ተመልሶ እንደነበር እንዴት እናውቃለን?<br>5. ኢየሱስ በምድር ላይ እያለ ያደረጋቸውን አንዳንድ የአገልግሎት ተግባራት ጥቀሱ። | ታላቁን ተልእኮ አጥኑ ***(ማቴዎስ 28፡ 16-20)***<br>1. ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች እንዴት ማዘዝ ይችላል? ***(ቁጥር 18)***<br>2. ደቀመዛሙርቱ የተሰጣቸው አራት ትዕዛዞች ምን ምን ነበሩ?<br>3. ደቀመዝሙር መሆን ምን ማለት ነው? ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው?<br>4. ትዕዛዛቱን ከፈፀሙ ኢየሱስ ምን ሊያደርግላቸው ቃል ገባላቸው? |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስን ለማገልገል ማድረግ የምንችለውን ነገር ጥቀሱ።<br>2. ከዚህ በፊት ባይሳካልንም እንኳን በአገልግሎት መቀጠል?<br>3. በመከራና በሕይወት ማዕበል ውስጥ ኢየሱስን ማመን? | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. ህይወታችሁን ለኢየሱስ ሰጥታችኋል እና በአዲሱ ህይወታችሁ ለእርሱ ለመኖር እየጣራችሁ ነው?<br>2. ቃሉን በመታዘዝ ተጠምቃችኋል? ካልሆነ፣ ለምን? |

| | ለ8 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 - የወንጌሉ ጸሃፊዎች<br>ርዕስ - ሉቃስ | ለ8 - ደረጃ 4<br>ጥናት 3 - ከፊት ያለው መንገድ<br>ርዕስ - የጌታ እራት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል: *ሉቃስ 1፡ 1-4፤ ሉቃስ 4፡ 1-12***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ሉቃስ 19፡ 10***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ከመሆኑም በተጨማሪ 'ፍጹም ሰው' እንደነበር ሉቃስ አጽንኦት ይሰጣል።<br>2. ፈተናዎቹ ጌታ ኢየሱስ ኃጢአት ማድረግ እንዳልቻለ ያረጋግጣሉ እና ቅዱስና ኃጢአት የሌለበት ሰው ስለነበር የኃጢአተኞች አዳኝ መሆን ይችላል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል: *ሉቃስ 22፡ 14-20፤ 1ቆሮንቶስ 11፡ 23-31***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *1ቆሮንቶስ 11፡ 26***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ኢየሱስ በልዩ መንገድ እንድናስታውሰው አዞናል።<br>2. ይህንን ማስታወሻ እንደ ትልቅ ቁም ነገር ማየት አለብን። |
| *መግቢያ* | ሉቃስ እና የሐዋርያት ሥራ የተጻፉት ለቴዎፍሎስ ቢሆኑም እንኳን ስለእርሱ ግን ጥቂት ነው የምናውቀው። 'የከበርህ' ***(ሉቃስ 1፡ 3)*** የሚለው መጠሪያው የመንግስት ሀላፊ እንደነበር ያሳያል። ስሙ 'የእግዚአብሔር ወዳጅ' ማለት ነው። ምናልባት በሮማ ግዛት ውስጥ ሀላፊነት የለው ስራ ያለው ክርስቲያን ሊሆን ይችላል። በአፍ ቃል በሚተላለፍበት ጊዜ ስህተት እንዳይፈጠር ሉቃስ የኢየሱስን ሕይወት የተጻፈ ዘገባ ሰጠው። | አሁን አብሯቸው የሌለን ሰው የሚያስታውሱበትን መንገዶች ተማሪዎቹን ጠይቁ፤ ምናልባት በፎቶግራፍ ወይም በልዩ ትዝታዎች። ከደቀመዛሙርቱ ጋር በማይሆንበት ጊዜ እርሱን እንዲያስታውሱበት ኢየሱስ ለየት ያለ መንገድ ትቶላቸዋል። |
| *ማጠናቀቅ* | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. የሐዋርያው ጳውሎስ የቅርብ ወዳጅ የነበረው ሉቃስ አህዛብ ክርስቲያን ሀኪም ነበር።<br>2. ሉቃስ ኢየሱስ ሲወለድ 'መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ' ***(ሉቃስ 2፡ 11)*** ብሎታል። እርሱ ስጋ የሆነው እግዚአብሔር ነው።<br>3. በእድገቱ ሙሉ በሙሉ ፍጹም እንደነበር ***(ሉቃስ 2፡ 52)*** ሉቃስ ጽፏል። የጌታ በጥበብ ማደግ ስለአእምሮአዊ እድገቱ ይናገራል፤ በቁመት ማደጉ ስለአካላዊ እድገቱ ይናገራል፤ 'በእግዚአብሔር ፊት' ማደጉ ስለመንፈሳዊ እድገቱ ይናገራል እና 'በሰዎች ፊት' ማደጉ ስለማህበራዊ እድገቱ ይናገራል።<br>4. የኢየሱስን ፈተና በአጭሩ አስረዱ ***(ሉቃስ 4፡ 1-13)*** እና ይህ እንዴት ፍጹም እንደነበረና ለፈተና እጅ እንደማይሰጥ እንደሚያሳይ አሳዩ።<br>5. ***በሉቃስ 23*** የጌታን ሞት እና ስለእርሱ ጲላጦስ፤ አንዱ ወንበዴና መቶአለቃው የሰጡትን ሁሉም የጌታ ኢየሱስን ፍፅምና ያሳዩበትን አስደናቂ አስተያየቶች እናገኛለን። ***(ሉቃስ 23፡ 14፤ 41 እና 47)*** *ኢየሱስ ከኃጢአት ነፃ መሆኑ አስፈላጊ እንደነበር፤ ካልሆነ ግን ለኃጢአታችን መሞት እንደማይችል አስረዱ። አሁን ይህ ፍጹም ሰው በገነት ነው እና ኃጢአተኞችን ማዳን ይፈልጋል። የእርሱ የሆኑትን እና እንደአዳኝና ጌታ ያመኑትንም እየጠበቀ ነው።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: - ኢየሱስ በምድረበዳ ተፈተነ ስዕል** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ደቀመዛሙርቱ እና ኢየሱስ አብረው በነበሩበት በመጨረሻው ምሽት ኢየሱስ እንጀራና ጽዋን ወስዶ አመሰገነ። እንጀራው ለእነርሱ የሚቆረሰው ስጋው እና ጽዋው ለእነርሱ የሚፈሰው ደሙ እንደሆነ ነገራቸው። ከዚያም እርሱን ለማስታወስ እንጀራውን እዲበሉና ጽዋውን እንዲጠጡ ነገራቸው። ***(ሉቃስ 22፡ 14-20)***<br>2. በቅርቡ የሚሆነውን የሚያውቀው ኢየሱስ ብቻ ስለነበር ደቀመዛሙርቱ ሙሉ በሙሉ አልተረዱትም። ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ ይህንን ትዕዛዝ ያስታውሱ ነበር።<br>3. ይህ ለክርስቲያኖች እንጀራና ጽዋን በመውሰድ ስለጌታ ኢየሱስ ሞትና ስቃይ የሚያስቡበትና የሚያሰላስሉበት ልዩ መንገድ ነው። ***(1 ቆሮንቶስ 11፡ 23-26)***<br>4. ፋሲካ ከግብፅ ባርነት ነፃ የመውጣት በዓል እንደሆነው፤ እንጀራውንና ጽዋውን መውሰድም በክርስቶስ ከኃጢአት ነፃ የመውጣታችን በዓል ነው።<br>5. እንጀራውንና ጽዋውን እርሱ እስከሚመጣ ድረስ ብቻ እንዲወስዱ ጌታ ኢየሱስ ተናግሯል። ይህ የኢየሱስ ሕይወትና ሞት መታሰቢያ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ቃል የተገባውን የእግዚብሄርን መንግስትም ማስታወሻ ነው!<br>6. ራሱ ኢየሱስ ለህዝቡ ኃጢአት የተሰዋ እውነተኛው የፋሲካ በግ ሊሆን ስለነበር ይህንን የፋሲካ ራት ከደቀመዛሙርቱ ጋር ለማሳለፍ ነበር የፈለገው። ስጋውንና ደሙን ለደቀመዛሙርቱ መስጠቱን ያሳያል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - የመጨረሻው እራት** |
| *ክለሳ* | ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠቀም ትምህርቱን ከልሱ:<br>1. የሉቃስ ወንጌል ጭብጥ ምንድነው?<br>2. የሉቃስ ስራ ምን ነበር?<br>3. ለምን ነበር ለቴዎፍሎስ የጻፈው?<br>4. በውልደቱ ጊዜ ለኢየሱስ የተሰጡት ስሞች ትርጉም ምንድነው 'መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ'?<br>5. ሉቃስ ለምንድነው ፈተናዎቹን የጻፈው?<br>6. ***ሉቃስ 23፡ 14፤ 41 እና 47ን*** ተመልከቱ እና ስለ 'ፍጹሙ ሰው' እነዚህ ሰዎች ምን እንዳሉ ተወያዩ። | በ ***1 ቆሮንቶስ 11፡ 27-31*** ላይ እነዚህን ምልክቶች እንደ ማስታወሻ ከመውሰዳችን በፊት ራሳችንን መመርመር እንዳለብን ይናገራል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ የምታስቡትን ተወያዩ። |
| *ከሕይወት ጋር ማዛመድ* | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ጌታ ኢየሱስን እንዴ ነው የምታዩት - እንደ 'ፍጹም ሰው' ወይስ እንደ ማንኛውም ሰው?<br>2. ይህንን ፍጹም ሰው እንደ አዳኛችሁ አምናችሁታል? ካመናችሁት፤ ለሌሎች ስለእርሱ እየተናገራችሁ ነው? | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. እኛ እንደ ክርስቲያን እንጀራውንና ጽዋውን ወስደን ምን እንደሚወክሉ በቁም ነገር እናስባለን?<br>2. በ"አዲስ ኪዳን" በካህናትና በመስዋዕት በኩል ማለፍ እንደማይጠበቅብን ነገር ግን በኢየሱስ ምክንያት ቀጥታ ወደ እግዚአብሔር መግባት መቻላችንን እናደንቃለን? |

| | **ለ8 - ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 4 - የወንጌሉ ጸሃፊዎች**<br>**ርዕስ - ዮሐንስ** | **ለ8 - ደረጃ 4**<br>**ጥናት 4 - ከፊት ያለው መንገድ**<br>**ርዕስ - እንደ ክርስቲያን ማደግ** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዮሀንስ 20፡ 26-31***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሀንስ 20፡ 31***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ኢየሱስ 'የእግዚአብሔር ልጅ' እንደሆነ ዮሐንስ አጽንኦት ሰጥቶታል፡፡<br>2. ጌታ ኢየሱስ 'እኔ ነኝ' የሚለውን አገላለፅ ብዙ ጊዜ ተጠቅሞታል እና እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን እራሱን 'እኔ ነኝ' ብሎ ስለጠራ ይህንን በማድረጉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን እኩልነት እያሳየ ነበር፡፡ ***(ዘጸአት 3፡ 14-15)*** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***1ጴጥሮስ 2፡ 1-3፣ 2ጴጥሮስ 3፡ 18፣ ሐዋ. ሥራ 17፡ 10-12***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***1ጴጥሮስ 2፡ 2***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ክርስቲያኖች በእምነታቸው በየቀኑ እንዲያድጉ ያስፈልጋል፡፡<br>2. ስለእግዚአብሔር ጸጋና እውቀት ለሁላችንም ሁሌም የምንማረው ነገር አለ፡፡ |
| መግቢያ | ዮሐንስ ወንጌሉን የሚጀምረው ኢየሱስን "ቃል" ብሎ በመጥራት ነው፡፡ ቃላት እራሳችንን ለሌሎች የምናስረዳባቸው ወይም የምንገልፅባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ ከ2000 አመታት በፊት ከድንግል ማርያም በቤተልሔም ሲወለድ፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ሲሆን እግዚአብሔር ለዚህ አለም እራሱን ሙሉ በሙሉ በልጁ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ገልጦታል፡፡ እርሱ ለእኛ በመሞት እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወደን አሳይቶናል ስለዚህም እርሱ እግዚአብሔር ስለእኛ ያለውን ሀሳብ ማሳያ ነው፡፡ | ነገሮች እንዴት እንደሚያድጉ በቡድን ተወያዩ ለምሳሌ:- እንስሳት፣ ሕፃናት፣ እፅዋት፣ ዛፎች፡፡ ለማደግ ምን ያስፈልጋቸዋል? የሚያስፈልጋቸውን ካላገኙ ምን ይፈጠራል? |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ዮሐንስ ኢየሱስን 'ቃል' ብሎ ጠርቶታል፡፡ ***(ዮሐንስ 1፡ 1)***<br>2. ዮሐንስ እራሱን 'ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር' ብሎ ጠርቷል፡፡ ***(ዮሐንስ 20፡ 2)***<br>3. በዮሐንስ ወንጌል 'እኔ ነኝ' የሚለው የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው እና ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ባህሪያት በሰባት የተለያዩ መንገዶች ጠቅሶታል:<br>የሕይወት እንጀራ ***(ዮሐንስ 6፡ 35፣ 41፣ 48፣ 51)***<br>የዓለም ብርሃን ***(ዮሐንስ 8፡ 12፣ 9፡ 5)***<br>በሩ ***(ዮሐንስ 10፡ 7፣ 9)***<br>መልካም እረኛ ***(ዮሐንስ 10፡ 11፣ 14)***<br>ትንሣኤና ሕይወት ***(ዮሐንስ 11፡ 25-26)***<br>መንገድና እውነት ሕይወትም ***(ዮሐንስ 14፡ 6)***<br>የወይን ግንድ ***(ዮሐንስ 15፡ 1፣ 5)***<br>4. ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው በጌታ ኢየሱስ እንድናምንና ዘላለማዊ ሕይወት እንዲኖረን ነው፡፡ ***(የሐንስ 20፡ 30-31)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ፡፡**<br>**ትምህርት 4ን ጨርሱ፡፡**<br>**አሳዩ: የሚሆን ስዕል የለም፡፡** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እንደ ክርስቲያን ልንኖርበት የሚገባ መንገድ አለ፡፡ በባህሪያችንና በስራችን የክርስቶስን ባህሪይ ማንፀባረቅ አለብን፡፡ እርሱን ለማክበር ከፈለግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለብን እንድናውቅ የሚረዱን ብዙ ጥቅሶች አሉ፡፡<br>2. በ ***1 ጴጥሮስ 2፡ 1*** አታላይ፣ ግብዝና ቅንዓተኛ ወይም ሐሜተኛ መሆን እንደሌለብን ይነግረናል፡፡<br>3. ***1 ጴጥሮስ*** አዲስ ክርስቲያን አዲስ እንደተወለደ ህፃን እንደሆነ ይናገራል፡፡ ለማደግ ወተት መጠጣት አለባቸው፡፡ ይህ ወተት የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ይህ እድገት መቼም አያቆምም እና ህፃኑ እያደገ ሲሄድም ምግብ ይፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ በክርስቲያን ህይወት ውስጥ ለማደግ እንዲረዳቸው ምግብ (መጽሐፍ ቅዱስ) የማያስፈልጋቸው ምንም አይነት ጊዜ የለም፡፡<br>4. ***2 ጴጥሮስ 3፡ 18*** በጌታችን ጸጋና እውቀት እንድናድግ ያስተምረናል፡፡ *ጸጋና እውቀት ምን እንደሆኑና በእነሱ እንዴት እንደምናድግ ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ፡፡*<br>5. ጳውሎስና ሲላስ በቤርያ ወንጌል ሲሰብኩ ስለሚሉት ነገር ሰዎቹ በጣም ተደንቀውና ጓጉተው ነበር፡፡ በ ***ሐዋርያት ሥራ 17*** የተከፈተ ልብ እንደነበራቸው፣ በጉጉት ይሰሙ እንደነበር እና መጽሐፍትን በየቀኑ ይመረምሩ እንደነበር ይናገራል፡፡ ስለእግዚአብሔር የበለጠ ለመማር ምን አይነት ፍላጎት ነበራቸው!<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ፡፡**<br>**ጥናት 4ን አጠናቁ፡፡**<br>**አሳዩ: የሚሆን ስዕል የለም፡፡** |
| ክለሳ | ከላይ የተዘረዘሩትን ሰባቱንም 'እኔ ነኝ' ባህርያቶች ውሰዱና እያንዳንዱ እንዴት ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንደሚያሳይ ተወያዩ፡፡ | ጳውሎስ እና ሲላስ ያናገሯቸው ***(የሐዋርያት ሥራ 17፡ 10-12)*** በቤርያ የነበሩት ሰዎች ለመማር ጉጉት ነበራቸውና ጳውሎስና ሲላስ እውነት እየተናገሩ እንደነበር ለማወቅ በየቀኑ መጽሐፍትን ይመረምሩ ነበር፡፡ ሰባኪው ወይንም መሪው ስላለ ብቻ አንድን ነገር ትክክል ነው ብለን እንዳናስብ መጠንቀቅ አለብን፡፡ ለራሳችን ከመጽሐፍ ቅዱስ መልሶችን ለማግኘት መፈለግ አለብን፡፡ |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስን የሚያምኑ ከሆነ ተማሪዎች እንዲናገሩ ጠይቋቸው፡፡<br>2. ከሆኑ እምነታቸውን በእርሱ ላይ ጥለው የዘላለም ሕይወት አግኝተዋል? ***(ዮሐንስ 1፡ 12-13፣ 5፡ 24)***<br>3. የዘላለም ሕይወት ካገኘን ወደ መንግስተ ሰማያት እየተጓዝን ነው እና ለህይወታችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ቀን በቀን ማንበብ አለብን፡፡ በተጨማሪም ቀን በቀን መጸለይ እና ለእኛ ደግ ስለመሆኑ ጌታ ኢየሱስን ማመስገንና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያነበብነውን በተግባር እንድናውል ኃይል እንዲሰጠን መጠየቅ አለብን፡፡ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. በእያንዳንዱ ቀን ለማደግ እንተጋለን? እምነታችን እንዲጠነክር እናነባለን፣ እንጸልያለን እና ስለእግዚአብሔር የበለጠ ለማወቅ እንፈልጋለን? የምናድገው የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት እና በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ብቻ ነው፡፡<br>2. በቤርያ ከነበሩት ሰዎች ጋር እንዴት ነው የምንነፃፀረው? የሚያስተምሩንን ሰዎች ከልባችን እናዳምጣለን? መልስ ለማግኘት በየቀኑ መጽሐፍትን እንመረምራለን?<br>3. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እንዴት እርግጠኛ መሆን እንደምንችል ተወያዩ፡፡ |

| | **ለ9 - ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 1 - ሙሴ**<br>**ርዕስ - በቅርጫት ውስጥ ያለው ህፃን** | **ለ9 - ደረጃ 4**<br>**ጥናት 1 - ሙሴ**<br>**ርዕስ - ልዑሉ** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘፀአት 1፡ 6-14 እና 22፤ 2፡ 1-10***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዕብራውያን 11፡ 23***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እስራኤላውያን በግብፅ ውስጥ በቁጥርም በኃይልም በጣም ጨምረው ነበር እና ፈርዖን በጦርነት ጊዜ አደጋ ያደርሱብኛል ብሎ አሰበ ስለዚህ ሁሉም ወንድ ሕፃናት እንዲገደሉ አዘዘ።<br>2. እግዚአብሔር ሙሴን ተጠቅሞ ፈርዖንን ሊጥልና እስራኤላውያንን ከባርነት ነፃ ሊያወጣ ነበር ስለዚህም ሙሴን በሕፃንነቱ አባይ ወንዝ ውስጥ ከመስመጥ አዳነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘፀአት 1፡ 5-22፤ 2፡ 1-25***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዕብራውያን 11፡ 23***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እስራኤላውያን በግብፅ ውስጥ በኃይልም በቁጥርም ጨምረው ነበር እና ፈርዖን በጦርነት ጊዜ አደጋ ያደርሱብኛል ብሎ አሰበ ስለዚህ ሁሉም ወንድ ሕፃናት እንዲገደሉ አዘዘ።<br>2. እግዚአብሔር ለሙሴ ህይወት እቅድ ነበረው - የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ምድር ነፃ ሊያወጣ ነበር። |
| መግቢያ | ትምህርት ለ7ን እና ለ8ን ከልሱና ዮሴፍና ወንድሞቹ ወደ ግብፅ ከመጡ ከ300 አመታት በኋላ እስራኤላውያን በቁጥር ጨምረው እንደነበር ለተማሪዎቹ አስረዱ። ባሪያ ያደረጋቸው አዲስ ፈርዖን ስልጣን ላይ ነበር። እስከዚያ ድረስ በሙሴ መወለድ እና መጠበቅ ውስጥ እግዚአብሔር ለእነርሱ ዕቅዱን እየፈፀመ ነበር። ወደ ከነዓን ምድር የሚመራቸው ሙሴ ነበር። | ጥናት ለ7ን እና ለ8ን ከልሱ። ዮሴፍ ሲሞት የእስራኤል ልጆች ትልቅና ሰፊ ቤተሰብ ነበሩ። ቢሆንም ግን ትልቅ ህዝብ ሆኑ፣ ይህ ባሪያ ያደረጋቸውን አዲሱን ፈርዖን አሳሰበው። ቢሆንም ግን እግዚአብሔር አይረሳቸውም እና ለእስራኤል ህዝብ ያለውን ዕቅድ ይፈጽማል። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ፈርዖን ወደ ስልጣን መጣ እና የእስራኤላውያን ብልፅግና ***(1፡ 7)*** ወደ መከራ ተቀየረ ***(1፡ 8-11)*** ነገር ግን እግዚአብሔር አይኖቹ በእነርሱ ላይ ነበሩ እና ጠበቃቸው። ***(1፡ 12)***<br>2. ቁጥራቸው ከእንግዲህ እንዳይጨምር ለመጣርና ለማቆም ሁሉም አዲስ የሚወለዱ ወንድ ሕፃናት እንዲገደሉ ፈርዖን ትዕዛዝ አወጣ። ***(1፡ 15-20)***<br>3. ሙሴ የተወለደው ከእንበረም እና ከዮካብድ ነው እና ለሶስት ወራት ከተንከባከቡት በኋላ በአባይ ወንዝ ዳር ባስቀመጡት በትንሽዬ ሳጥን ውስጥ ከተቱት። ***(2፡ 1-3)***<br>4. እግዚአብሔር የሙሴን ህይወት ጠበቀ እናም ይህንን ለማድረግ እህቱን ማርያምን፣ እናቱን እና የፈርዖንን ሴት ልጅ ተጠቀመ። ***(2፡ 4-9)***<br>5. ሙሴ 'የፈርዖን የሴት ልጅ ልጅ' ***(ሐዋ. ሥራ 7፡ 22)*** በመሆኑ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ትምህርት አግኝቷል በተጨማሪም የግብፅ ዙፋን ወራሽ ነበር።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ሕፃን ሙሴ (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እስራኤላውያን መንግስቱ ላይ አደጋ ይፈጥራሉ ብሎ ፈርዖን ፈራ ስለዚህ እድገታቸውን ለማቆም በመጣር ባሪያ አደረጋቸው። ***(1፡ 8-11)***<br>2. እስራኤላውያን የበለጠ እየጠነከሩ እየጠነከሩ ሄዱ ስለዚህ ፈርኦን ሁሉንም አዲስ የሚወለዱ ወንድ ሕፃናትን እንዲገድሉ አዋላጆቹን አዘዛቸው ነገር ግን ተዕዛዙን በመቃረን አዋለጆቹ ህይወታቸውን አተረፉ። ***(1፡ 15-20)***<br>3. ሙሴ ሲወለድ ትንሽ ጀልባ ተሰራና እናቱ በዚያ ውስጥ በአባይ ወንዝ ዳር አኖረችው። ***(2፡ 1-3)***<br>4. የፈርዖን ሴት ልጅ ሙሴን አዳነችው እና በመጨረሻም እናቱ አሳዳጊው ሆነች። ***(2፡ 4-9)***<br>5. ሙሴ ያደገው በቤተ መንግሥት ውስጥ ነበር። ሲያድግ እስራኤላውያን ባሪያዎችን በመርዳት ህይሉን ለማሳየት መሞከር ጀመረ።<br>6. ባሪያ ሲመታ የነበረውን ግብፃዊ ገደለ እናም ወደ ምድያም ምድር መሰደድ ነበረበት። ***(2፡ 11-15)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ሕፃን ሙሴ (I) እና ሙሴ የግብፅ ልዑል (I)** |
| ክለሳ | ስለ:<br>(i) የሙሴ መወለድ ዳራ<br>(ii) የእርሱ መጠበቅ<br>(iii) የእርሱ እንክብካቤ<br>(iv) የእርሱ ትምህርት<br>(v) በግብፅ ውስጥ ሊያገኘው ስለነበረው ሹመት<br>የተማሩትን በጥቂት አረፍተ ነገሮች እንዲያጠቃልሉ ተማሪዎችን ጠይቁ። | በጥናት 1 ከነበሩት ጋር የሚመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ከልሱ። አዋላጆቹና የሙሴ ወላጆች እንዴት የምድሩን ህግ እንዳልታዘዙ አስቡ። ክርስቲያኖች የምድሩን ህግ መታዘዝ ይኖርባቸው ይሆን በሚለው ላይ እና ይህንን ማድረግ ሊከብድ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ካሉ የቡድን ውይይት አድርጉ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>ለህይወቱ ትልቅ እቅድ ስለነበረው፣ እግዚአብሔር የልጁን (ሙሴ) ህይወት እንደተቆጣጠረውና እንደመራው ሁሉ ለመዳን በልጁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነታችንን ፣ ስናደርግ የእኛንም ህይወት ይቆጣጠራል እናም ይመራል። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. የሙሴ ወላጆችና አዋላጆቹ ትክክል ለሆነው ነገር ቆሙ ምክንያቱም ሁኔታው ተስፋ የሌለው ቢመስልም እንኳን በእግዚአብሔር ይታመኑና ይፈሩት ነበር። በከባድ ጊዜ ለእርሱ ታማኝ ሆነን እንቀጥላለን?<br>2. የሙሴ ኃጢአት ወዲያውኑ ነበር የታወቀበት። 'ትናንሽ ኃጢያቶችን' ሰርተን እናመልጣለን ብለን ልናስብ እንችላለን ነገር ግን ሁሌም ይታወቃል፣ በዚያ በሚሆን ሰው፣ ወይም ከሁሉም በላይ ደግሞ እግዚአብሔር ሁሉንም ያያል። |

| | ለ9 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 - ሙሴ<br>ርዕስ - ትልቁ ስህተቱ | ለ9 - ደረጃ 4<br>ጥናት 2 - ሙሴ<br>ርዕስ - እረኛው |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 2፡ 11-22***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘኍልቁ 32፡ 23***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ሙሴ ህዝቡን መርዳት መጀመር ይፈልጋል።<br>2. ኃጢአታችንን ከሌሎች ለመደበቅ ብንሞክርም እንኳን ከጌታ ኢየሱስ ግን መደበቅ አንችልም።<br>3. ለኃጢአታችን ንስሀ ስንገባና በታማኝነት በጌታ ኢየሱስ ፊት ስንናዘዝ ይቅር ይለናል። (ተማሪዎችን ***1 ዮሐንስ 1:9ን*** አመልክቷቸው) | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 3፡ 1-16፤ 4፡ 1-17***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሐዋ. ሥራ 7፡ 35***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እግዚአብሔር ለሙሴ ተገለጠና ተመልሶ ሄዶ ህዝቡን ነፃ እንዲያወጣ ነገረው።<br>2. እንዲሰራ በጠራው ነገር ውስጥ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደሚሆን ቃል ገባ። |
| መግቢያ | በትምህርት 1 መጨረሻ ሙሴ እንዴት 'የፈርኦን የሴት ልጅ ልጅ' እንደሆነና ቤተ መንግስት ውስጥ እንዳደገ ተማሪዎቹን አስታውሱ። በዚህ ትምህርት እርሱ አሁን አድሜው አርባ አመት ነው ***(ሐዋ. ሥራ 7፡ 23)*** እና የእስራኤል ልጆች በግብፅ እያሉ የሚደርስባቸው ነገር በጣም አሳስቦት ነበር። ግብፃዊውን የገደለው ***(ዘጸአት 2፡ 14)*** ከሀሳቡ የተነሳ ነው ነገር ግን የግድያ ኃጢአት በመፈፀሙ ስህተት ነበር። እግዚአብሔር ህዝቡን ነፃ ለማውጣት ሙሴን ሊጠቀመው ነበር ነገር ግን የእግዚአብሔርን ስራ ለመስራት ዝግጁ ከመሆኑ በፊት ተጨማሪ ሌላ አርባ አመት መጠበቅ ነበረበት! | ***ዘጸአት 3፡ 1*** ላይ ያለው ኮሬብ ተራራ፣ ሲና ተራራ እንደሆነ እና በሙሴ ህይወት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ቦታ መሆኑን ለተማሪዎቹ አስረዱ። ***በዘጸአት 3፡ 12*** እግዚአብሔር ለሙሴ: 'በዚህ ተራራ ላይ ለእግዚአብሔር ትገዛላችሁ' አለው። እግዚአብሔር በዚህ ተራራ ላይ ነበር ሙሴን ያናገረውና 'አስርቱን ትዕዛዛት' የሰጠው። ***(19፡ 1-20)*** |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ሙሴ ለእስራኤላውያኑ ችግር በጣም ሀዘኔታ ተሰምቶት ነበር ነገር ግን ፈጥኖ ግብፃውያኑን በመግደሉ እግዚአብሔር ተቆጣ። ስለሁኔታው ወደ እግዚአብሔር መፀለይና ምሪቱን መፈለግ ነበረበት።<br>2. ሙሴ በራሱ እጅ እስራኤላውያንን ነፃ አወጣለው ብሎ አስቦ ነበር ነገር ግን ይህ ገና የእግዚአብሔር እቅድ አልነበረም።<br>3. ኃጢአቱ ሲታወቅ ወደ ምድያም ምድር ሸሸ። ***(2፡ 15)***<br>4. በምድያም ባለ የውሀ ምንጭ አጠገብ የወደፊት ሚስቱን ሲፓራን አገኘ ***(2፡ 21)*** እና ሁለት ወንድ ልጆች ወለዱ። አንዱ ልጅ ጌርሳም ይባላል፣ 'መጻተኛ' ማለት ነው። ይህ ስም በምድያም ምድር እያለ የሙሴን የብቸኝነት ስሜት ገልጿል። አልዓዛር የሚባል ሌላም ልጅ ነበረው፣ 'እግዚአብሔር ረዳቴ ነው' ማለት ነው። ሙሴ ግብፃዊውን በመግደሉ ምክንያት ሊገድለው ከሚፈልገው ከፈርዖን ስላዳነው እግዚአብሔርን አመሰገነ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ የግብፅ ልዑል (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ሙሴ ከግብፅ ሸሽቷል እና አሁን በምድያማውያን መካከል እየኖረ ነበር።<br>2. እግዚአብሔር ከሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ ሙሴን አናገረው እና ሙሴ በአክብሮት ጫማውን አወለቀ። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ለማውጣት ወደ ፈርዖን እንዲሄድ እንደሚፈልግ ሲነግረው፤ ሙሴ ለስራው ብቁ እንዳልሆነ ገለፀ። ***(3፡ 10-11)***<br>3. ግብፃውያን ብዙ አማልክት በነበራቸው ጊዜ ሙሴ ለእስራኤላውያን ይህን እንዲናገር እግዚአብሔር ነግሮታል: 'ያለና የሚኖር ወደ እናንተ ላከኝ' ***(3፡ 14)*** -ብቸኛው እውነተኛና የማይለወጥ እግዚአብሔር!<br>4. ሀይሉን ለሙሴ ለማሳየትና እግዚአብሔር በትክክል ማን እንደሆነ እንዲያውቁ ይህንን ኃይል ሙሴ ለህዝቡ እንዴት ማሳየት እንደሚችል ለማሳየት እግዚአብሔር የሙሴን በትር ተጠቀመ እና ወደ እባብ ቀየረው።<br>5. በመጨረሻም እግዚአብሔር አሮን ለሙሴ እንዲናገርለት ፈቀደ እና ሙሴ እግዚአብሔር እንደነገረው ለአሮን ምን ማለት እንዳለበት ይነግረዋል። ***(ዘጸአት 4፡ 16)***<br>6. ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ነፃ ስለማውጣት ለፈርዖን ለመንገር ወደ ግብፅ ሄደ። ይህ ምናልባት በህይወቱ ውስጥ ትልቁ ፈተና ሊሆን ይችላል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ እና የሚቃጠለው ቁጥቋጦ (I)** |
| ክለሳ | ***ሐዋ. ሥራ 7፡ 23-29ን*** በማንበብ ይህን ትምህርት ከልሱ እና ትምህርቱን ለማጠናቀቅ እንዲረዳቸው በትምህርት 2 ከተጠየቁት ጋር የሚገናኙ ጥያቄዎችን ተማሪዎችን ጠይቁ። | የእስራኤልን ህዝብ ነፃ ለማውጣት እግዚአብሔር ወደ ግብፅ ሲልከው እንዴት ሲያስብ እንደነበር በማሳየት የሙሴን ምስል ከተወሰኑ የንግግር ሳጥኖች ጋር ሳሉ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ለእርሱ ባለን አገልግሎት እና በራሳችን ሀሳብ ሳይሆን በእርሱ መንገድ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ጌታ ኢየሱስ እንዲመራን የመጠየቅን አስፈላጊነት።<br>2. ኃጢአታችንን ያለመሸፈን ነገር ግን ለጌታ ኢየሱስ የመናዘዝን አስፈላጊነት። እግዚአብሔር ሁሉንም እንደሚያውቅ፤ ምንም ነገር በሚስጥር እንደማይደረግ ተማሪዎችን አስታውሱ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ለሙሴ የተገለጠው እግዚአብሔር ዛሬ በልባችንና በህይወታችን መኖር የሚችለው ራሱ እግዚአብሔር ነው። እርሱ በህይወታቸው ይኖርና ህይወታቸውን ይቆጣጠር እንደሆነ ተማሪዎቹን ጠይቁ።<br>2. እንደክርስቶስ ተከታዮች የሆነ ነገር እንድናደርግ እግዚአብሔር ከጠራን፤ ልክ አሮን ሙሴን ወክሎ እንደተናገረው እርሱ ስራውን እንድንሰራ ይረዳናል። |

| | ለ9 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 - ሙሴ<br>ርዕስ - የሚቃጠለው ቁጥቋጦ | ለ9 - ደረጃ 4<br>ጥናት 3 - ሙሴ<br>ርዕስ - መሪው |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 2፡ 23-25፤ 3፡ 1-10***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘጸአት 15፡ 11***<br><br>***እየተማርን ያለነው:***<br>1. እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆች በአዲሱ የግብፅ ንጉስ እንደባሪያ ተደርገው እየኖሩ እንደሆነ ያውቃል ነገር ግን ወደ ከነዓን ምድር መልሶ ሊያመጣቸው ነበር።<br>2. እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ አውጥቶ ወደ ከነዓን እንዲመራ ሙሴን ጠራው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 7፡ 1-25***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ምሳሌ 29፡ 1***<br><br>***እየተማርን ያለነው:***<br>1. የእግዚአብሔር ኃይል ከማንኛውም የሰው ወይም የተደራጀ ኃይል ይበልጣል - 'ሁሉን ማድረግ የሚችል ሀያል' ነው- እርሱ ሁሉን ቻይ ነው።<br>2. አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚጠሩት በችግር ውስጥ ሲሆኑ ብቻ ነው እና ነገሮች በጥሩ ሲሄዱ እርሱ በህይወታቸው ላይ ያለውን ስልጣን ይረሳሉ። |
| ***መግቢያ*** | አሁን ያለውን ሁኔታ ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ፤ ሙሴ ግብፅን ለቋል እና አሁን በምድያም ውስጥ አዲስ ህይወትን ጀምሯል። በተለይም ፈርዖን ሊገድለው ስለሚፈልግ ወደ ግብፅ የመመለስ ምንም አይነት ሀሳብ የለውም። እስራኤላውያን አሁንም በግብፅ ውስጥ በጣም እየተሰቃዩና ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር እየጮሁ ነው። እግዚአብሔር ልመናቸውን በሙሴ በኩል መመለስ ይጀምራል። | ሙሴ በግብፅ ምን ሊገጥመው እንደሚችል ባለማወቁ በዚህ ሰአት ምን ተሰምቶት ሊሆን እንደሚችል ከተማሪዎቹ ጋር አስቡ። ስለሆነ ነገር ስንጨነቅ አንዳንዴ ምን እየተፈጠረ እንዳለ ወይም ለምን እየተፈጠረ እንዳለ እና ማን እየረዳን እንደሆነ ማረጋገጫ ሊሰጠን ይገባል። ***በዘጸአት 7፡ 1-5*** እግዚአብሔር ለሙሴ ይህንን አድርጓል። |
| ***ማጠናቀቅ*** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>***ተወያዩና አስረዱ:***<br>1. እግዚአብሔር ስለእስራኤል ልጆች ሁኔታ የሚያውቀው ነገር - አየ፣ ሰማ እና ሀዘናቸውን ያውቃል። ***(2፡ 23-25)***<br>2. እግዚአብሔር ጩኸታቸውን ሰማ እና በሰና ተራራ በሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ እራሱን ለሙሴ ገለጠ፤ ማን እንደሆነና ቅድስናውን።<br>3. እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች ስላለው ጥንቃቄ ***(ቁጥር 7)***፣ ከፈርዖን እንዴት እንደሚያድናቸው ***(ቁጥር 8)*** እና እነርሱን ከግብፅ ለማውጣት ሙሴን እንደሚጠቀመው ***(ቁጥር 10)*** ለሙሴ ነገረው።<br>4. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 'የተቀደሰ' ለሚለው ቃል የመጀመሪያው ማጣቀሻ የሚገኘው ***በዘጸአት 3፡ 5*** ላይ እንደሆነ እና ጫማውን በማውለቁ ሙሴ የቆመበት ቦታ 'የተቀደሰ' ለመሆኑ እውቅና መስጠቱን ተማሪዎቹን አስታውሱ። የእኛ እግዚአብሔር ሁሌም በአምልኮት እና በአክብሮት ሊታይ ይገባል።<br>5. ሙሴ የሚቃጠለው ቁጥቋጦ ጋር ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘቱ ስለእግዚአብሔር ቅድስና እና ኃይል የሆነ ነገር ይማራል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴና የሚቃጠለው ቁጥቋጦ (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>***ተወያዩና አስረዱ:***<br>1. እግዚአብሔር ሙሴን ሊደመጥ የሚገባው ሀያል ሰው አደረገው ('እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሀለው' ***(7፡ 1)*** - ነገር ግን ፈርዖን ለእርሱ እጅ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነም።<br>2. ሙሴ እና አሮን ጌታ እንዳዘዛቸው አደረጉ እና አሮን በፈርዖን ፊት በትሩን ሲጥለው እባብ ሆነ። የፈርዖን አስማተኞችም በትራቸውን ሲጥሉ እባብ ሆነ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል በስራ ላይ በማሳየት የአሮን በትር የእነርሱን በትር ዋጠቻቸው። ***(7፡ 8-12)***<br>3. ሙሴ እና አሮን በትራቸውን በአባይ ወንዝ ላይ ዘረጉ እና ወደ ደም ተቀየረ። አሳዎቹ ሞቱ፣ ውሀው ለመጠጥነት፣ ለእርሻ፣ ለመታጠብም አሳ ለማጥመድም መዋል አልቻለም ነበር። ***(7፡ 20-21)***<br>4. ፈርዖን ሙሴ ህዝቡን እንዲለቅ ያቀረበውን ጥያቄ ተቃወመ።<br>5. ፈርዖን እንዲሰማና እስራኤላውያንን እንዲለቅ ለማድረግ እግዚአብሔር የላካቸውን ተጨማሪ መቅሰፍቶች ለማየት ***ከምዕራፍ 8-10*** አንብቡ። ነገር ግን ልቡ ደንድኖ ነበር እና አሁንም አልተቀበለም። ቢሆንም ፈርዖን ለመስማማት እንቢ ማለቱ የጌታ እቅድ ሁሌም ፍፃሜ ላይ እንደሚደርስ አረጋግጧል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴና መቅሰፍቶቹ ክፍል 1 (I)** |
| ***ክለሳ*** | ተማሪዎቹን ወደ ***ሐዋ. ሥራ 7፡ 30-35*** በማመልከት ትምህርቱን ከልሱ።እስጢፋኖስ ስለሙሴ ህይወት እንዴት እንደተናገረ እና በተጨማሪም የሚቃጠለውን ቁጥቋጦ ሁኔታ መጥቀሱን ተማሪዎቹን አሳዩ። | ቁልፍ ጥቅሱን ተመልከቱና ከዚህ ጥናት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ከክፍሉ ጋር ተወያዩ። |
| ***ከሕይወት ጋር ማዛመድ*** | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ መሆኑን ማስታወስ እና የሚገባውን ክብርና አምልኮ መስጠት አለብን። አሁን ብዙ ሰዎች እንደሚያደርጉት በፍፁም ስሙን በከንቱ ማንሳት የለብንም።<br>2. እግዚአብሔር ቅዱስ ቢሆንም እንኳን ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለኃጢአተኞች እንዲሞት ልኮታል እና ኃጢአታችንን ሁሉ እና አድርገን ሊሆን የሚችለውን አለማክበራችንን እና አለማምለካችንን ጭምር ይቅር ይላል። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. የወንዙ ወደ ደም መቀየር ተአምራዊ ክስተት ነበር ነገር ግን ጌታ ኢየሱስንና በመስቀል ላይ የሰራውን ስራ ስናምን እግዚአብሔር በህይወታችን ውስጥ የበለጠ ተአምራዊ ነገር ማድረግ ይችላል።<br>2. ***መዝሙር 105፡ 23-29*** ተመልከቱና እግዚአብሔር እንዴት ሁሉንም ነገር እየተቆጣጠረ እንዳለ አስቡ። በአሁኑ አለም የዚህን እንድምታ አስቡ። |

| | ለ9 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 - ሙሴ<br>ርዕስ - የእግዚአብሔርን መልዕክት ማድረስ | ለ9 - ደረጃ 4<br>ጥናት 4 - ሙሴ<br>ርዕስ - ነፃ አውጪው |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ዘጸአት 5፡ 1-9፤ 22-23፤ 6፡ 1-9***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ዕብራውያን 10፡ 31***<br><br>***እየተማርን ያለነው፡***<br>1. ሙሴና አሮን የእስራኤልን ልጆች እንዲለቅ ለመጠየቅ ወደ ፈርዖን ቀረቡ ነገር ግን ፈርዖን ጥያቄያቸውን አልተቀበለም።<br>2. እንዲለቃቸው ስለሚያስገድደው፣ ፈርዖን የእስራኤልን ልጆች እንደሚለቅ ጌታ ለሙሴ አረጋገጠለት። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ዘጸአት 11፡ 1-10፤ 12፡ 1-13 እና 21-42***<br>**ቁልፍ ጥቅሶች፡** ***የሐንስ 1፡ 29፤ 1 ቆሮንቶስ 5፡7***<br><br>***እየተማርን ያለነው፡***<br>1. ግብፃውያን ስላልታዘዙ እግዚአብሔር ፍርዱን አሳይቷቸዋል ነገር ግን እስራኤላውያን ስለታዘዙ ምህረቱን አሳይቷቸዋል።<br>2. የፋሲካው በግ በመስቀል ላይ ሞቶ የኃጢያታችንን ቅጣት ወደወሰደው ወደ ጌታ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ይጠቁማል። |
| *መግቢያ* | እግዚአብሔር ወደ ግብፅ እንዲመለስ ሙሴን ቢያዘውም እንኳን ሙሴ ግን ወደፊት ስለሚጥመው ነገር ፈርቶ እንደነበር ለተማሪዎቹ አስረዱ። እግዚአብሔር አብሮት እንደሚሆን ቃል ገባለት ነገር ግን ሙሴ ፈርዖን በድጋሚ ሲያየው እንዴት ሊሆን እንደሚችል ምንም አላወቀም ነበር። | የግብፅ ሀያል ህዝብ ለአብርሃምና ለእስራኤል ህዝብ ቃሉን ከመጠበቅ እግዚአብሔርን ሊያግደው አልቻለም። ይህ የመጨረሻው መቅሰፍት በግብፅ ውስጥ በባርነት መጨረሻ እና በቀይ ባህር ውስጥ ወደ ምድረበዳ እስራኤላውያንን በመምራት ጅማሬ ነው የመጣው።<br>እስራኤላውያን የሙሴን ቃል መታዘዝ ነበረባቸው ከዚያም ከእግዚአብሔር ፍርድ ይድናሉ። |
| *ማጠናቀቅ* | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>***ተወያዩና አስረዱ፡***<br>1. የእስራኤልን ልጆች እንዲለቅ ሲጠየቅ፣ ፈርዖን በሙሴና በአሮን የመጣለትን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለማድረግ እንቢተኛ ሆነ። ***(5፡ 4)***<br>2. ፈርዖን ጡብ ለመስራት የሚያስፈልገውን ገለባም እንዲሰበስቡ በማድረግ የእስራኤል ልጆች ላይ የስራ ጫና ጨመረባቸው። ***(5፡ 6-7)***<br>3. ሙሴ ስለጉዳዩ ጌታን አናገረው እናም እርሱ የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ነፃ እንደሚያወጣ አረጋገጠለት። ***(5፡ 22-23 እና 6፡ 1)***<br>4. ***በዘጸአት 6፡ 6-8 ጌታ 7*** ጊዜ 'አደርጋለው' ብሏል እና ***በዘጸአት 6፡ 2*** 'እኔ እግዚአብሔር ነኝ' ብሏል። ሙሴና አሮን በሀይሉ እና በገባው ቃል እንዲታመኑ ፈልጎ ነበር። ብዙም ሳይቆይ እግዚአብሔር በተጨማሪም በግብፅ ምድር በሚልካቸው 10 ቅጣቶች (መቅሰፍቶች) ፈርዖን የእርሱን ኃይል እንደሚያይ ተናገረ።<br>5. ሙሴ ይህንን ለእስራኤል ህዝብ አስተላለፈ ነገር ግን ለማመን በባርነታቸውና በመከራቸው በጣም ተስፋ ቆርጠው እና ተሰብረው ነበር። ***(6፡ 9)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 4ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ እና አሮን ወደ ፈርዖን ሄዱ (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>***ተወያዩና አስረዱ፡***<br>1. በተከሰቱት ዘጠኝ መቅሰፍቶች ውስጥ እንደታየው የእግዚአብሔርን ተአምራዊ ኃይል ችላ ማለቱን ከቀጠለ እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ ሙሴና አሮን ፈርዖንን አስጠንቅቀውታል። ***(መዝሙር 105፡ 26-36ን*** ተመልከቱ) የመጨረሻው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። ***(11፡ 4-6)***<br>2. ፋሲካ ተጀመረ እና እስራኤላውያን ነውር የሌለበትን ጠቦት ደም ወስደው የቤታቸው በር ሁለቱ መቃንና ጉበኑ ላይ እንዲረጩት ታዘዙ።<br>3. እንዴት መስዋዕትና በቤት ውስጥ ለሚሞተው የበኩር ልጅ ምትክ እንደሆነ፤ የጠቦቱን ጥቅም አስረዱ። የበኩር ልጅ እንዳይሞት እንስሳው መሞት ነበረበት። ***(12፡ 1-7)***<br>4. በመጨረሻም እኩለ ሌሊት ላይ ሞት መጣ እና ሁሉም የግብፃውያን የበኩር ልጅ ሞተ ነገር ግን በበሩ መቃኖች ላይ ደሙ ስለተረጨ የእስራኤል ልጆች ታለፉ። ***(12፡ 29-30)***<br>5. ፈርዖን በመጨረሻም የእስራኤልን ህዝብ ለመልቀቅ ተስማማ። አሁን በግብፅ ውስጥ ከ430 አመታት በኋላ የእስራኤላውያን ዘጸአት ጀመረ። ***በዘፍጥረት 15፡ 13-14*** ያለው እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ተፈጸመ!<br><br>**ቁልፍ ጥቅሶቹንና እንዴት ከዚህ ጥናት ጋር እንደሚገናኙ አስረዱ። ተማሪዎቹ እንዲያውቋቸው አበረታቱ።**<br>**ጥናት 4ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ እና መቅሰፍቶቹ ክፍል 2 (I)** |
| ክለሳ | እግዚአብሔር ለሙሴ አስቀድሞ የነገረውን ነገር እና ፈርዖን ወዲያውኑ እንቢ ሲል አሁንም ሙሴ ለእግዚአብሔር እንዴት ምላሽ እንደሰጠ አስቡ። እየሆነ ስላለው ነገር እስራኤላውያን ሙሴና አሮንን ተመልከተው ሲወቅሷቸው፣ ሙሴ ደግሞ በምላሹ ወደ እግዚአብሔር ተመልክቶ ወቀሰው። እግዚአብሔር ስለአላማውና ስለገባው ቃል በድጋሚ ለእነርሱ ለማስረዳት እንዴት ያለ ታጋሽና ምህረት የተሞላ ነው፤ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ"። | ፋሲካው፣ በእስራኤላውያን መንደር የንፁህ ደም መስዋዕት መሆን ምንን እንደሚወክል እንዲያስቡ ተማሪዎቹን አበረታቱ። ለመጪው ታላቅ መስዋዕት እንዴት ምልክት እንደሆነም አስቡ። (በእኛ መንደር የጌታ ኢየሱስ ንፁህ የደም መስዋዕት - እርሱ የእግዚአብሔር በግ ነበር።) |
| *ከሕይወት ጋር ማዛመድ* | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኑን እንድንረዳ ይፈልጋል።<br>2. እግዚአብሔር እርሱን አለመታዘዝ በጣም ከባድ ነገር መሆኑን እንድንረዳ ይፈልጋል።<br>3. እግዚአብሔር በከባድ ጊዜያት እንኳን ሁሌም ልንታመነው እንደምንችል እንድንረዳ ይፈልጋል። እርሱ እንደማይተወን ነገር ግን ሁሌም ለእኛ እቅድ እንዳለው ማስታወስ አለብን። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. ከኃጢአታችን ነፃ እንድንወጣ የተከፈለንን ትልቅ ዋጋ እንገነዘባለን? ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ይህንን ዋጋ ከፍሎ እንዳዳነን?<br>2. የእኛን ኃጢአት ስለወሰደ እና ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖረን ስላደረገ እርሱን እናመሰግነዋለን? ማድረግ ያለብን ነገር ቢኖር እርሱን ማመን እና የዘላለም ህይወት ስጦታን መቀበል ነው። |

| | ለ10 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 - ሙሴ<br>ርዕስ - የፋሲካው በግ | ለ10 - ደረጃ 4<br>ጥናት 1 - ሙሴ<br>ርዕስ - በቀይ ባህር ውስጥ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 12፡ 1-14፣ 29-36 እና 50-51***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘጸአት 12፡ 13***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው በግብፃውያን ላይ ፍርዱን አሳይቷል እና ደግሞ በመታዘዛቸው ለእስራኤላውያን ምህረቱን አሳይቷል።<br>2. ኢየሱስ የመጨረሻው መስዋዕትና ቤዛችን ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 13፡ 17-22፣ 14፡ 1-31***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘጸአት 14፡ 13***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ነበር።<br>2. እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ጥበቃ እና እርዳታ ተጠራጠሩ።<br>3. እግዚአብሔር ከግብፃውያን ለማዳን ለህዝቡ ሀይሉንና ፍቅሩን በድጋሚ አሳይቷል። |
| መግቢያ | ስለምናከብራቸው አንዳንድ በአላቶችና ምን እንደሚወክሉ እንዲያስቡ ተማሪዎችን ጠይቁ ለምሳሌ:- ገና፣ ፋሲካ። በአላት እግዚአብሔር ስላደረገልን ነገሮች ጠቃሚ ማስታወሻዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ አስረዱ። በአይሁድ እምነት ውስጥ ስለሚከበር በአል (ስለፋሲካ) ሰምተው የሚያውቁ ከሆነ ጠይቋቸው። በዛሬው ታሪክ ስለፋሲካ እንማራለን። | ከዚህ በፊት ሄደው ወደማያውቁበት ቦታ ረዥም መንገድ እየሄዱ እንደሆነ በአዕምሮአቸው እንዲስሉ ተማሪዎቹን ጠይቁ። መንገዱን የሚያሳያቸው የሆነ ነገር (ካርታ) ወይም የሆነ ሰው ያስፈልጋቸዋል። እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ለሚያደርጉት ረዥም ጉዞ ይህ ነበር የሚያስፈልጋቸው። እግዚአብሔር በጉዞአቸው በልዩ መንገድ መራቸው። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ስላለፉት መቅሰፍቶች ከተማሪዎች ጋር ከልሱ እና ይህ የመጨረሻው ከሁሉም በላይ እጅግ መጥፎ እና በጣም አስደንጋጭ እንደነበር አስረዱ። እግዚአብሔር ከፈርዖን የበለጠ ሀያል መሆኑን ሊያሳይ ነበር።<br>2. እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን ምን ማድረግ እንዳለባቸው በጣም ዝርዝር የሆኑ መመሪያዎችን ሰጣቸው። ***(ቁጥር 1-14)***<br>3. እስራኤላውያን ከሞት ለመዳን ምንም እንከን የሌለበት ጠቦት ማረድና ደሙን በበሩ መቃን ላይ ማድረግ ነበረባቸው።<br>4. እንዴት መስዋዕትና በቤት ውስጥ ለሚሞተው የበኩር ልጅ ምትክ እንደሆነ፣ የጠቦቱን ጥቅም አስረዱ።<br>5. ፋሲካ እንስሳ የሰዉትን ሰዎች ቤት ጌታ "ያለፈበትን" ምሽት በማስመልከት የሚከበር የአይሁድ በአል እንደሆነ አስረዱ። በራቸው ላይ ደም ያልነበረበት የእያንዳንዱ ቤተሰብ የበኩር ልጅ ተገደለ።<br>6. የቤዛነትን ትርጉም አስረዱ፤ ከምርኮ መልሶ መግዛት/ማዳን። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለኃጢአተኛ የእንስሳ መስዋዕትን ይቀበል ነበር። ኢየሱስ ሲመጣ ፍጹም የሆነውን ህይወቱን በኃጢአታችን ቦታ ተካው። እርሱ አዳኛችን ነው - ከኃጢአት ኃይል አድኖን ወደ እግዚአብሔር መልሶ አምጥቶናል። የኢየሱስ መስዋዕት የእንስሳን መስዋዕት አላስፈላጊ አድርጎታል።<br>7. ፈርዖን በመጨረሻም የእስራኤልን ህዝብ ለመልቀቅ ወሰነ - ጌታ ለእነርሱ የገባውን ቃል ጠብቋል! ***(12፡ 31-32)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ እና መቅሰፍቶቹ ክፍል 2 (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ወደዚያ መራቸው። በቀን በደመና አምድ እና በምሽት በእሳት አምድ መራቸው። ከዚያም እየመራቸውና እየረዳቸው ከእነርሱ ጋር እንደሆነ ያውቁ ነበር። ***(13፡ 21-22)*** *አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንደሆነ ለማወቅ እንደዚህ አይነት የሚታየ ምልክት እንደሚፈልጉ ከተማሪዎቹ ጋር ተወያዩ። ነገር ግን አሁን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው እና በመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈስ ቅዱስ በኩል መርቶናል - በእርሱ ኢያመንን ከሆነ።*<br>2. እስራኤላውያን ከግብፅ ነፃ በመውጣታቸው እየተሰማቸው ስለነበረው እፎይታ አስቡ። ሆኖም የፈርዖን የጦር ሰራዊት እነርሱን ለመመለስ እየተከተላቸው እንደሆነ ሲሰሙ ይህ እፎይታ እንዴት ወደ ፍርሀት ተቀይሮ እንደነበር አስቡ። ***(14፡ 10)***<br>3. እስራኤላውያን መጨነቅ፣ ለዚህ እግዚአብሔርን መክሰስ እና መናደድ ጀመሩ። ነገር ግን ሙሴ እንዲረጋጉ ነገራቸው። እግዚአብሔር ለእነርሱ ይዋጋል። ሙሴ እግዚአብሔርን መታመን እየተማረ ነበር። ***(14፡ 13)***<br>4. እግዚአብሔር ለህዝቡ መሄዳቸውን እንዲቀጥሉ ነገራቸው እና በቀይ ባህር ውስጥ ማምለጫ አዘጋጀላቸው። ከዚያም እግዚአብሔር የግብፃውያን የጦር ሰራዊት እንዲሰምጥ አደረገ። ለህዝቡ የመዳኛ መንገድ ከፈተ። እግዚአብሔር ባህሩን በመክፈል ይህንን ተአምራት ሊያደርግ የቻለው ሀይሉን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ለህዝቡ ያለውንም ፍቅር ለማሳየት ነው። ***(14፡ 21-22)***<br>5. እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በመፍራት ውስጥ ነበሩ እና በዚያ ቀን በእርሱና በሙሴ አመኑ። ***(14፡ 31)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ፡ ቀይ ህርን መሻገር (I)** |
| ክለሳ | ከብዙ የባርነት እና ወደ እግዚአብሔር የማልቀስ አመታት በኋላ፣ ከብዙ መቅሰፍቶች እና ፈርኦን እግዚአብሔርን ለመስማት ፍቃደኛ ካለመሆኑ በኋላ የእስራኤል ህዝብ በመጨረሻም ነፃ ሆነ! ግብፅን ሲለቁ ምን ተሰምቷቸው ሊሆን እንደሚችል በቡድን ተወያዩ። | ትምህርቱን ለመከለስ በዛሬው ጥናት ላይ ተማሪዎቹን ፈትኑ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ከኃጢአታችን ነፃ እንድንወጣ የተከፈለንን ትልቅ ዋጋ እንገነዘባለን? ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ይህንን ዋጋ ከፍሎ እንዳዳነን?<br>2. የእኛን ኃጢአት ስለወሰደ እና ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖረን ስላደረገ እርሱን እናመሰግነዋለን? ማድረግ ያለብን ነገር ቢኖር እርሱን ማመን እና የዘላለም ህይወት ስጦታን መቀበል ነው። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ነገሮች በእኛ መንገድ ወይም እኛ በጠበቅነው መንገድ በማይሄዱበት ጊዜ እንዴት ነው ምላሽ የምንሰጠው? እግዚአብሔርን እንከስሳለን እና በእርሱ እንናደዳለን? ወይስ እኛ በጠበቅነው መንገድ ባይሆንም እንኳን ካመንነው እግዚአብሔር እንደሚረዳን በመተማመን እነዚህን ችግሮች እንጋፈጣለን?<br>2. ከዚህ ጥናት እግዚአብሔር የማይቻል ነገር አምላክ እንደሆነ አስቡ። |

| | ለ10 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 - ሙሴ<br>ርዕስ - ቀይ ባህር | ለ10 - ደረጃ 4<br>ጥናት 2 - ሙሴ<br>ርዕስ - በሲና ተራራ ላይ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 13፡ 20-22፣ 14፡ 5-15፣ 19-31***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘጸአት 14፡ 14***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እግዚአብሔር የተመረጠ ህዝቡን ከግብፅ አዳነ።<br>2. እስራኤላውያን እግዚአብሔርንና ለእነርሱ ያለውን ሀሳብ መጠራጠር ጀመሩ።<br>3. እግዚአብሔር እየመራቸውና እየጠበቃቸው ከእነርሱ ጋር ነበር። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 19፡ 1-13፣ 16-25፣ 20፡ 1-21***<br>**ቁልፍ ጥቅሶች:** ***ዘጸአት 19፡ 5 እና 20፡ 20***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እግዚአብሔር ቅዱስ እና ኃያል ነው።<br>2. እስራኤላውያን ለያደርጉ ያልቻሉትን እግዚአብሔርን በቀላሉ የማግኘት መብት አለን።<br>3. እግዚአብሔር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ለእስራኤላውያን ትዕዛዝ ሰጣቸው። |
| *መግቢያ* | እስራኤላውያን 430 አመታትን በባርነት በግብፅ ውስጥ ካሳለፉ በኋላ አሁን ነፃ ሲሆኑ ምን ተሰምቷቸው ሊሆን እንደሚችል አስቡ። በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ምን አስበው ሊሆን ይችላል ብለው እንደሚያስቡ ተማሪዎቹን ጠይቁ። | በቀን ተቀን ሁኔታዎች ስለምንጠቀማቸው ህግና መመሪያዎች አስቡ ለምሳሌ:- የሆነን እቃ የመጠቀም መመሪያ፣ የሆነን ምግብ የመስራት መመሪያ። እነዚህ መመሪያዎች የተቀመጡት እኛን ለመርዳት ነው። ሙሴ ለእስራኤል ህዝብ ከእግዚአብሔር ከተቀበለው ትዕዛዝ ጋር ተመሳሳይ ነው። በህይወታቸው እንዲመሯቸው ለእነርሱ ጥቅም ነበር የተቀመጡት። |
| *ማጠናቀቅ* | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. በመጨረሻም እስራኤላውያን ነፃ ሆነዋል እና ከግብፅ ወደ ተስፋይቱ ምድር እየተጓዙ ነበር! ከባርነት ነፃ በመውጣታቸው እንዴት ተደስተው ሊሆን እንደሚችል አስቡ።<br>2. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በቀን በደመና አምድ እና በምሽት በእሳት አምድ መራቸው። ***(13፡ 21-22)*** ይህ እርሱ ሁሌም ከእነርሱ ጋር እንደነበርና እየመራቸው እንደነበር አሳያቸው። *ብዙ ጊዜ ዛሬ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዳለ የሚታዩ ምልክቶችን ለማየት እንመኛለን። ነገር ግን ሊመራን እና በመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈስ ቅዱስ በኩል ሊረዳን ይችላል።*<br>3. የፈርዖን የጦር ሰራዊት እስራኤላውያንን ማሳደድ ሲጀምሩ፣ እስራኤላውያን ፈሩና እግዚአብሔር እየጠበቃቸው እንዳልሆነ አማረሩ። እርሱን አላመኑትም ነበር። ***(14፡ 10)*** ከዚህ በፊት እግዚአብሔር እንዴት እንደረዳቸውና እስከዚህ ድረስ እንዳመጣቸው ሙሉ በሙሉ ረስተዋል። *በህይወታችን ነገሮች በትክክል ሳይሄዱ ሲቀሩ ብዙ ጊዜ እንደዚህ አይነት ምላሽ ሊኖረን አረንደሚችል አስረዱ።*<br>4. እግዚአብሔር እንደሚዋጋላቸው ህዝቡን በማስታወስ ሙሴ ተረጋግቶና በሁኔታ ውስጥ አዎንታዊ አመለካከት ይዞ ቀጠለ። ***(14፡ 14)***<br>5. እስራኤላውያን እንዲያልፉና ወደ ማዶ ከተሻገሩ በኋላ የግብፅን ሰራዊት በባህር ውስጥ እንዲጠፉ ቀይ ባህርን በመክፈል እግዚአብሔር ታላቅ ሀይሉን አሳየ። ***(14፡ 21-22፣ 26-28)***<br>6. እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ፈሩትና እርሱን አመኑ እና ሙሴንም እንደመሪ አመኑት። ***(14፡ 31)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ፡ ቀይ ባህርን መሻገር (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እግዚአብሔር እስራኤውያንን ከግብፅ ካወጣ ሁለት ወር ሆኖታል። እርሱ አሁን ለሚመጣው ነገር ያዘጋጃቸዋል።<br>2. እግዚአብሔር ለህዝቡ እንዴት የተመረጠ ህዝብ እንደሆኑ እና እንዴት የተመረጠ ርስት እንደሚሆኑለት እንዲነግራቸው ለሙሴ ነገረው። ***(19፡ 5-6)*** እራሳቸውን እንዲቀድሱ ነገራቸው። *መቀደስ ምን ማለት እንደሆነ አስረዱ - መለየት፣ እግዚአብሔርን እንዲያገኙ እነርሱን በስጋና በመንፈስ ዝግጁ ማድረግ።*<br>3. የተቀደሰ ስለነበር እስራኤላውያን ተራራውን እንኳን መንካት አልቻሉም። የእግዚአብሔር ኃይል እና ቅድስና በጣም ኃያል ከመሆኑ የተነሳ ህዝቡ ወደ እርሱ መቅረብ አልቻሉም ነበር። ***(19፡ 10-13)*** *ጌታ ኢየሱስ በሰራው ስራ ሁሉ ምክንያት አሁን ይህን ቅዱስ፣ ኃያል እግዚአብሔር በነፃነት መቅረብ መቻላችን እንዴት ድንቅ እንደሆነ አስቡ።*<br>4. እግዚአብሔር ሙሴ ብቻ እንዲቀርበው ፈቀደ እና አስርቱን ትዕዛዛት ሰጠው። (20፡ 1-17) እነዚህ ህጎች የእስራኤል ህዝብ ለእግዚአብሔር እና እርስ በእርስ ያለውን ሀላፊነት ይናገራሉ። የተሰጡት እስራኤልን ወደ ተግባራዊ የቅድስና ህይወት ለማምራት፣ የእግዚአብሔርን ማንነት እንዲያዩ እና ህይወታቸውን እንዴት መኖር እንዳለባቸው ለማሳየት እቅድ ነበር።<br>5. ህዝቡ እራሳቸው ፈርተውና ወደ ተራራው ለመውጣት ፍቃደኛ አልነበሩም ስለዚህ ሙሴ በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል እንደ መካከለኛ ሆነ። አንድ ከሙሴ የሚበልጥ፣ ኢየሱስ፣ በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ብቸኛው መካከለኛ ሆነ። ***(1 ጢሞቴዎስ 2፡ 5)***<br>6. ሙሴ እንዳይፈሩ ነገር ግን እግዚአብሔርን መፍራት ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን ነገራቸው። የእነርሱ ፍርሀት መሸበር ነበር። ሙሴ ይህንን፣ እምነትና መታዘዝን በሚያመጣው እና ከኃጢአት በሚጠብቃቸው በእግዚአብሔር ፍርሀት መተካት ፈልጎ ነበር። (20፡ 20)<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ በሲና ተራራ (I)** |
| ክለሳ | እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ሲመራ፣ እስራኤላውያን ግብፃውያን እያሳደዷቸው እንደሆነ ሲያዩ እና ከዚያም እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳናቸው የሚያሳይ የዚህን ታሪክ ተከታታይ ክፍል ከምስል ጋር ስሩ። | አስርቱን ትዕዛዛት እንዲናገሩ እና እያንዳንዱን እንዲያብራሩ ተማሪዎቹን በመጠየቅ ትምህርቱን ከልሱ። አስርቱ ትዕዛዛት በራሳችን ህይወት እንዴት ተግባራዊ መሆን ይችላሉ? |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>በህይወታችን መጥፎ ነገሮች ሲፈጠሩ እግዚአብሔርን ወቅሰን እርሱ ስለማይደርስልን ወይም እኛን ለመርዳት ፍቃደኛ ስላልሆነ ነው እንላለን? ወይስ እኛም እንደ ሙሴ እርሱ እንደረዳንና ካመንነው ብቻ መርዳቱን እንደሚቀጥል እና እንደሚዋጋልን እናምናለን? | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>እስራኤላውያን ምን ያህል እንደፈሩ እና እንዴት የእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ለመግባት ብቁ እንዳልሆኑ ካሰብን፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት ወደ እግዚአብሔር መገኘት በነፃነት መግባት የመቻልን እድል በእውነት እንገነዘባለን? በእግዚአብሔር እይታ የተቀደሰን እንድንሆን ኃጢአታችንን ወደራሱ ስለወሰደ ልናመሰግነው ይገባል። |

| | ለ10 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 - ሙሴ<br>ርዕስ - ከባዱ ጉዞ | ለ10 - ደረጃ 4<br>ጥናት 3 - ሙሴ<br>ርዕስ - ከእሳት መውጣት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 17፡ 1-16***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***1 ጴጥሮስ 5፡ 7***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እስራኤላውያን እግዚአብሔርን መጠራጠራቸውን ቀጠሉ።<br>2. እግዚአብሔር መቼም አይጥላቸውም እናም ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸውን መስጠቱንና መዋጋቱን ቀጠለ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 32፡ 1-35***<br>**ቁልፍ ጥቅሶች:** ***ዘጸአት 32፡ 26 እና 33***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. የእስራኤል ህዝብ ብዙም ሳይቆዩ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ረሱ።<br>2. እግዚአብሔር ለተከተሉት ምህረትን አሳየ እና ያልተከተሉትን ቀጣ። |
| መግቢያ | እስራኤላውያን ምን ያህል እንደተጓዙ እና እግዚአብሔር እንዴት የሚያስፈልጋቸውን እንዳዘጋጀላቸው ተመልከቱ፤ በግብፅ ውስጥ መቅሰፍቶቹ፤ የቀይ ባህር መከፈል። በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ስለ እግዚአብሔር ምን እንደተሰማቸው ተማሪዎቹ እንዲያስቡ ጠይቋቸው። | ስህተት እንደሆነ የሚያውቁትን ነገር ያደረጉበትን ጊዜ እንዲያስቡ ተማሪዎችን ጠይቁ። እኛ ብዙ ጊዜ ለምን አዎ እንደምንልና በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ብዙኃኑን እንደምንከተል አስቡ። በዚህ ታሪክ እንደ አሮን መሆን እንደሌለብን ነገር ግን እንደ ሙሴ መሆንና የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል እንዳለብን እንማራለን። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እስራኤላውያን የጌታን ትዕዛዝ በመከተል በድጋሚ እየተጓዙ ነበር። ነገር ግን በመንገዳቸው ላይ የሚጠጡበት ምንም አይነት ቦታ አልነበረም። ስለዚህ በድጋሚ ማጉረምረም ጀመሩ። ***(17፡ 2-3)*** ወደ እግዚአብሔር ከመጸለይ እና እርሱን ከማመን ይልቅ ለሙሴ ቅሬታ ማቅረብ ጀመሩ።<br>2. ቢያጉረመርሙም እንኳን እግዚአብሔር በቸርነት ሰራ እና ከአለት ውሀን ሰጣቸው - እርሱ አይጥላቸውም እና ተአምራት ያደርጋል! ***(17፡ 5-6)***<br>3. *አማሌቃውያን ስለተዋጓቸው መከራቸው አላለቀም ነበር!* ***(17፡ 8)*** *እነዚህ ቡድኖች ለደስታ ብለው የሚገድሉ ክፉ፣ አደገኛ ሰዎች እንደሆኑ ነበር የሚታወቁት። እስራኤላውያን ግብፅንና ችግሩን ሁሉ ትተው ከወጡ በኋላ አሁን በአማሌቃውያን መገደልን ሲጋፈጡ ምን ተሰምቷቸው ሊሆን እንደሚችል አስቡ።*<br>4. ነገር ግን እግዚአብሔር ረዳቸው። ሙሴ በኮረብታ ራስ ላይ ቆመ እና የእግዚአብሔርን በትር ከራሱ በላይ ያዘው። ከራሱ በላይ በሆነ ጊዜ እያሸነፉ ነበር ነገር ግን ከራሱ በታች ሲሆን እየተሸነፉ ነበር! ብዙም ሳይቆይ የሙሴ እጆች ደከሙ ስለዚህ አሮን እነ ሖር እጆቹን ከራሱ በላይ አድርጎ እንዲቆይ ረዱት። ***(17፡ 11-13)***<br>5. በዚያን ቀን እስራኤላውያን ውጊያውን አሸነፉ - ይህን ጠላት እንዲያሸንፉ በመርዳት እግዚአብሔር በግልፅ ከእነርሱ ጋር ነበር። ይህ በተጨማሪም እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ በሙሴ በኩል እንደሚመራ አሳይቷል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ፡ በምድረበዳ ውስጥ ምግብ እና ውሀ፣ ውጊያ ከአማሌቃውያን ጋር (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. የእስራኤል ህዝብ ሙሴ ከሲና ተራራ እስኪወርድ በመጠበቅ ትዕግስት አጡ። ችግሮችን በገዛ እጃቸው ወስደው የራሳቸውን አማልክት መስራት *ፈለጉ። የእግዚአብሔርን መሪነት እነርሱ ሊቆጣጠሩት በሚችሉት በውሸት ጣኦት ተኩት። ይህ እንዴት የመጀመሪያዎቹን ሁለት ትዕዛዛት እንደሚጥስ አስቡ።* ***(32፡ 1-4)***<br>2. እግዚአብሔር ምን እየተፈጠረ እንደሆነ ሲያይ ካለመታዘዛቸው የተነሳ ሁሉንም ህዝብ ሊያጠፋ ነበር ***(32፡ 10)*** ነገር ግን ሙሴ ይህን እንዳያደርግ እግዚአብሔርን ለመነ። እዚህ ጋር እግዚአብሔር ምህረትን አሳየ። ***(32፡ 11-14)*** *የምህረትን ትርጉም አስረዱ (ከሚገባን ቅጣት መዳን)።*<br>3. ሙሴ ከተራራው ወረደ እና በህዝቡ በጣም ከመናደዱ የተነሳ የእግዚአብሔርን ህግ እንደተላለፉ ሊያሳያቸው በፊታቸው ጽላቶቹን ሰበራቸው። ***(32፡ 19)*** ሆኖም እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ የበለጠ ተቆጣ።<br>4. የእስራኤልን ህዝብ ወደስህተት ስለመራ ሙሴ በአሮን ላይ አዝኖ ነበር። የእስራኤል ህዝብ እያደረጉ ያሉት ነገር ስህተት እንደሆነ ማወቅ ነበረበት ነገር ግን ቅሬታቸውን ሰምቶ ለማምለክ ይህን የወርቅ ጥጃ እንዲሰሩ አዝዛቸው። ***(32፡ 21-22)***<br>5. ሙሴ “ማነው የእግዚአብሔር ወገን?” ብሎ እስራኤላውያንን ጠየቀ። ምላሽ ያልሰጠ እና እግዚአብሔርን ያልተከተለ ሁሉ በዚያን ቀን ተገደለ። ***(32፡ 26-29)*** *ከሌላው ታማኝነት ሁሉ በላይ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ እና የወርቁ ጥጃ (I)** |
| ክለሳ | ቁልፍ ጥቅሱን አጥኑ እና እንዴት በተግባር ማዋል እንደሚችሉ ከቡድኑ ጋር ተወያዩ። | ***1 ዮሐንስ 5፡ 21ን*** ተመልከቱ እና በልባችን ውስጥ ምን አይነት “ጣዖታት” የእግዚአብሔርን ቦታ ሊወስዱ እንደሚችሉ አስቡ። እግዚአብሔርን የመከተልና የመታዘዝን አስፈላጊነት የሚያጎላ የግድግዳ ፖስተር ለመስራት ይህንን ጥቅስ እና እነዚህን “ጣዖታት” ተጠቀሙ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. በከባድ ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔር ሊረዳን እንደሚችል አንዳንድ ጊዜ እንረሳለን? ውጊያችንን እንድንዋጋ እንዲረዳን እና በሁሉም ከባድ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲረዳን ወደ እርሱ መዞር እንዳለብን ማስታወስ አለብን።<br>2. አሮንና ሖር እንዴት ሙሴን እጁን ከራሱ በላይ አድርጎ እንዲቆይ እንደረዱት አስቡ - አበረታተውት እና ደግፈውት ነበር። እኛ አሁን ሌሎችን በመርዳት እንዴት እንደዚህ መሆን እንችላለን? | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ስለዚህ ብዙ ጊዜ ስህተት ልንሰራና እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ዘወር ልንል እንችላለን። ነገር ግን በመጠየቅ ብቻ ከእግዚአብሔር ይቅርታን መቀበል እንችላለን።<br>2. አሮን ትክክል እንደሆነ ለሚያውቀው ነገር አልቆመም። በህይወታችን ውስጥ ይህንን አድርገን ብዙኃኑን የተከተልንበትን ጊዜያት ልናስታውስ እንችላለን? እንድንታዘዘው እና ፈተናዎች በመንገዳችን ሲመጡ እጅ እንዳንሰጥ እግዚአብሔር እንዲረዳን ጸልዩ። |

| | ለ10 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 - ሙሴ<br>ርዕስ - የናሱ እባብ | ለ10 - ደረጃ 4<br>ጥናት 4 - ሙሴ<br>ርዕስ - በምድረበዳ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘኍልቁ 21፡ 4-9፣ ዮሐንስ 3፡ 1-2 እና 14-16***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 3፡ 14***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እስራኤላውያን በድጋሚ በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ።<br>2. እግዚአብሔር እነርሱን መቅጣት ነበረበት - ነገር ግን ከቅጣታቸው የሚያመልጡበትን መንገድ አዘጋጀላቸው።<br>3. ይህ ወደፊት ኢየሱስ ለኃጢአታችን በመስቀል ላይ ሲሰቀል የሚያሳይ ስዕል ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘኍልቁ 21፡ 1-9***<br>**ቁልፍ ጥቅሶች:** ***ዮሐንስ 3፡ 14 እና 15***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እስራኤላውያን እግዚአብሔር እስከዚህ ድረስ እንዴት እንደተንከባከባቸውና የሚያስፈልጋቸውን እንዳዘጋጀላቸው በጣም በፍጥነት ረሱ።<br>2. ኃጢአት እያደረጉ እንደሆነና እያመኑት እንዳልሆነ እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ ማሳየት ነበረበት።<br>3. እግዚአብሔር ከቅጣታቸው የማምለጫ መንገድ አዘጋጀላቸው። |
| መግቢያ | የሆነ ነገር ወይም ከሆነ ሰው የተገባላቸውን ቃል ሲጠብቁ ትዕግስት ያጡበትን ጊዜ እንዲያስቡ ተማሪዎችን ጠይቁ። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለእስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር ቃል እንደገባላቸው ነገር ግን እዚያ ለመድረስ ትዕግስት እያጡ እንደሆነ አስረዱ። | ረዥም ጉዞ ስለመጓዝ አስቡ። ብዙ ጊዜ ሰዎች በጉዞው ሊሰለቹና ትዕግስት ሊያጡ ይችላሉ በተለይ ህፃናት። አንዳንዴ በአንድ ጊዜ እዚያ መድረስ ይፈልጋሉ። እስራኤላውያን እግዚአብሔር ስለነገራቸው የተስፋይቱ ምድር ስለመድረስ እንደዚህ ነበር የተሰማቸው። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እስራኤላውያን አሁን ለ40 አመት ያክል በምድረበዳ ላይ ነበሩ እና እየተናደዱ ነበር።በድጋሚ በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረም ጀመሩ - “በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብፅ ለምን አወጣችሁን?!” ***(ዘኍልቁ 21፡ 4)***<br>2. ስለዚህ በእርሱ ባለማመናቸው እግዚአብሔር ተቆጣ። መርዛማ እባቦችን በመካከላቸው ላከ እና ብዙዎች ሞቱ። ነገር ግን ሙሴ ህዝቡን ወክሎ ለይቅርታ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። ***(21፡ 7)***<br>3. እግዚአብሔር ሙሴ በእንጨት ላይ የናስ እባብ እንዲሰራ አደረገው እና ይህን እባብ ያየ ሁሉ ይድን ነበር። የናሱ እባብ እስራኤላውያን እንዲድኑ አስቻላቸው። እሱን በመመልከት ይህ ፍርድ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ እና እግዚአብሔር ብቻ ከዚህ ሊያድናቸው እንደሚችል እውቅና እየሰጡ ነበር። ***(21፡ 9)***<br>4. እስራኤላውያን ይህን ገና አላወቁም ነበር ነገር ግን ይህ እንጨቱ ላይ ያለው እባብ ከዚህ የበለጠ ትርጉም ነበረው። ኢየሱስ ***በዮሐንስ 3*** ላይ እስራኤላውያን ይህን እባብ በማየት እንደዳኑት ሁሉ ዛሬም እንዲሁ በመስቀል ላይ የኢየሱስን ሞት በማየት ከኃጢአታችን መዳን እንደምንችል ይናገራል። እስራኤላውያንን ያዳናቸው እባቡ አልነበረም ነገር ግን ሊያድናቸው የሚችለው እምነታቸው ነበር።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 4ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ሙሴ እና የናሱ እባብ (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እስራኤላውያን በምድረበዳ ላይ ለ40 አመታት ያክል ሲቅበዘበዙ ነበር እናም ትዕግስት ማጣት ጀመሩ። እግዚአብሔር የተስፋይቱን ምድር ቃል ገብቶላቸዋል አሁን ግን ምንም አይታይም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ምን ያህል እንዳመጣቸው ከማስታወስ ይልቅ ስለችግራቸው በእግዚአብሔር ላይ አማረሩ እና አጉረመረሙ። ***(ዘኍልቁ 21፡ 4-6)***<br>2. ከዚህ በፊት ብዙ አይነት የአደጋ ሁኔታዎች ውስጥ ነበሩ ነገር ግን እምነት ባይኖራቸውም እና ማማረራቸውን ቢቀጥሉም እንኳን እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን አዘጋጅቶላቸዋል እናም ከጎናቸው ነበር።<br>3. ነገር ግን እግዚአብሔር በቅቶት ነበር እናም ሰዎቹን የነደፏቸውን መርዛማ እባቦችን ላከ እና ብዙዎች ሞቱ። ***(21፡ 6)***<br>4. ብዙም ሳይቆይ ህዝቡ ኃጢአታቸውን አስተዋሉ እና እግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲጠይቅ ሙሴን ጠየቁት። ***(21፡ 7)***<br>5. ስለዚህ እግዚአብሔር የናሱ እባብ በእንጨት ላይ እንዲሰቀል አዘዘ እና ያዩተም ይኖራሉ። ይህን እባብ በመመልከት ይህ ፍርድ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ እና እግዚአብሔር ብቻ ሊወስድላቸውና ሊያድናቸው እንደሚችል እውቅና ሰጡ። ***(21፡ 9)***<br>6. የእስራኤል ህዝብ አላስተዋሉትም እንጂ ይህ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ የሚያሳይ ምልክት ነው። እባቡን ያዩ ከህመማቸው ነፃ ወጥተው ነበር እናም አልሞቱም። በተመሳሳይ መንገድ በመስቀል ላይ ወዳለው ኢየሱስ የሚመለከቱ እና የሚያምኑት አይሞቱም ነገር ግን የዘላለም ህይወት ይኖራቸዋል። (ቁልፍ ጥቅሶቹን ተመልከቱ)<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 4ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ሙሴ እና የናሱ እባብ (I)** |
| ክለሳ | በጣም ታዋቂ የሆነውን ጥቅስ ***ዮሐንስ 3፡ 16ን*** እንዲመለከቱ እና የዘላለም ህይወትን ምንነት እንዲያስቡ ተማሪዎቹን ጠይቁ። ብዙ ሰዎች የምድራዊ ህይወታቸውን ስለማይወዱት የዘላለም ህይወትን ሀሳብ አይወዱትም። ነገር ግን ኢየሱስ የሚሰጠው የዘላለም ህይወት በሽታ፣ ሞት፣ ክፋት ወይም ኃጢአት የለበትም! ክርስቶስን አውቀን ስንከተለው ለምድራዊ ህይወት ያለንን እይታ ይቀይረዋል። | በትናንሽ ቡድኖች ***መዝሙር 78፡ 10-38ን*** ተመልከቱና አጥኑ እና እግዚአብሔር ለህዝቡ ያደረገውን አስደናቂ ነገሮች በሙሉ እና ለእነዚህም የሰጡትን ምላሾች ዘርዝሩ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>እስራኤላውያን እያመኑት ስላልነበረ፣ ትዕዛዙን ስላላከበሩ እና ያደረገላቸውን ነገር ሁሉ ስለረሱ በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ። የምናጉረመርምባቸው ነገሮች ብዙ ጊዜ እንዴት ከራሳችን ድርጊትና አመለካከት የመጡ እንደሆኑ አስቡ። ማጉረምረማችንን ማስወገድ አለብን እና ህይወታችንን እንዲያዝ መፍቀድ የለብንም። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>እስካሁን ባያሳፍራቸውም እንኳን እስራኤላውያን አሁን ስላሉበት ሁኔታ በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ። በጣም ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ስለሚሰጠን ብዙ በረከቶችና በእርሱ ካመንን እንዴት እንደሚንከባከበን ልንረሳና እንደዚህ ልንሆን እንችላለን። እግዚአብሔርን ማየት እና በእርሱ ማመን እንችል ዘንድ ነገሩ እኛ በምናስበው መንገድ ላይሆን ይችላል እና ብዙ ጊዜም በህይወታችን “መርዛማ እባቦች” ለገጥሙን ይችላሉ። |

| | ለ11 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 - ሙሴ<br>ርዕስ - እግዚአብሔርን መገናኘት | ለ11 - ደረጃ 4<br>ጥናት 1 - ህጉ<br>ርዕስ - "አንድ እግዚአብሔር" |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 19፡ 1-14***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***1 ጴጥሮስ 1፡ 16***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እግዚአብሔር ቅዱስና ፍጹም ነው።<br>2. ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት መታዘዝ በጣም አስፈላጊ ነው።<br>3. የእግዚአብሔር ትዕዛዛት የህዝቡን ኃጢያተኝነት ገልጦ ያሳያል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 19፡ 16-25፣ እና 20፡ 1-7፣***<br>***ማቴዎስ 22፡ 34-40***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማቴዎስ 22፡ 37***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ ነው።<br>2. እግዚአብሔር ኃያል አምላክ ነው።<br>3. እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው።<br>4. እግዚአብሔር አፍቃሪ አምላክ ነው። |
| መግቢያ | ወደ ሰርግ ቦታ ሊሄዱ ከሆነ ምን እንደሚያደርጉ እንዲያስቡ ተማሪዎችን ጠይቁ ለምሳሌ:- ልብሳቸውን ማጠብ፣ ገላቸውን መታጠብ እና በጣም ንፁህ መሆናቸውን እና ለዚህ ትልቅ ቀን ጥሩ ልብስ መልበሳቸውን ማረጋገጥ! እርሱ ፍጹምና ኃጢአት የሌለበት ስለሆነና የእስራኤል ህዝብ ደግሞ በጣም ብዙ ጊዜ ኃጢአትን ስላደረጉ የእስራኤል ህዝብ እግዚአብሔርን ለመገናኘት እንዴት ይህን ማድረግ እንደነበረባቸው አስረዱ። | በዚህ ጥናት እግዚአብሔር ከእርሱ ውጪ ሌላ አማልክት ወይም ጣዖታት እንዳይኖራቸው የእስራኤልን ህዝብ እንዴት እንዳዘዘ እናያለን። በእኛና በእግዚአብሔር መሀል ምንም አይነት ነገር ቢመጣ ጣዖት ነው። ዛሬ ባለው ማህበረሰብ ውስጥ የጣዖታትን ወይም የአማልክትን ምሳሌዎች አስቡ እና እንዴት የእግዚአብሔርን ቦታ ሊወስዱ እንደሚችሉ ከተማሪዎቹ ጋር ተወያዩ። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እግዚአብሔርን ለመገናኘት ወደ ተራራው መውጣት የቻለው ሙሴ ብቻ ነበር። የእግዚአብሔር መገኘት በጣም ኃያልና ቅዱስ ስለነበር የእስራኤል ህዝብ ወደ እርሱ መውጣት አልቻሉም።<br>2. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ለማዳን ምክንያት ነበረው እና አሁን ነገራቸው። እርሱ እንዲታዘዙትና እንዲከተሉት ይፈልጋል። እግዚአብሔር እስራኤል ቅዱስ ህዝቡ፣ የእርሱ የተመረጡ ልዩ ህዝቦች እንዲሆኑት ፈልጓል። ***(ቁጥር 5-6)***<br>3. የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ሲሰሙ ህዝቡ እግዚአብሔር ያለውን ነገር ሁሉ እንደሚያደርጉ ምላሽ ሰጡ። ***(ቁጥር 8)***<br>4. እግዚአብሔር ለአምልኮ የእስራኤልን ህዝብ እንዲቀድስ ለሙሴ ነገረው። ***(ቁጥር 10)*** ይህ እግዚአብሔርን እንዲገናኙ እነርሱን ለማዘጋጀት የተደረገ ነበር። እግዚአብሔርን ለመገናኘት መታጠብና ልባቸውንና አእምሯቸውን ማዘጋጀት ነበረባቸው። እራሳቸውን በአካል ማንፃታቸው እግዚአብሔርን ለማምለክ በልባቸውም ለመንጻት እንዴት እንደረዳቸው ለተማሪዎቹ አስረዱ።<br>5. እግዚአብሔርን ለማግኘት ለምን መዘጋጀት እንደነበረባቸው ለማየት ቁልፍ ጥቅሱን ተመልከቱ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል- ሙሴ በሲና ተራራ (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እስራኤላውያን ወደ ሲና ተራራ መጥተዋል እና ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት እየነጹና ለመሄድ እየተዘጋጁ ነበር። እግዚአብሔር በጣም ቅዱስ ከመሆኑ የተነሳ የሚቻላቸውን ያክል ውጪያቸውን ለማንፃት መሞከር ነበረባቸው። ***(19፡ 14)***<br>2. እግዚአብሔር በእሳት አምሳል ከሰማይ ወረደ - የእስራኤል ህዝብ ከኃይሉ በታች በፍርሀት ተንቀጠቀጡ። ***(19፡ 16-18)***<br>3. እግዚአብሔር ከእርሱ ውጪ ሌላ አማልክት እንዳይኖራቸው ለህዝቡ ተናገረ። ***(20፡ 3)*** በተጨማሪም ሌሎች አማልክትንና ጣዖታትን፣ የእርሱን ቦታ ሊወስዱ የሚችሉ ማንኛውንም ነገሮች እንዳያመልኩ ነገራቸው። እርሱ ስለእኛ ፍቅር የሚቀና አምላክ ነው እና ለሚወዱትና ትእዛዛቱን ለሚጠብቁ የዘላለማዊ ፍቅርን ተስፋ ሰጥቷል። ***(20፡ 5-6)***<br>4. እግዚአብሔር ቀናተኛ ነኝ ሲል ኃጢአት እንደሆነው እንደ ሰዎች ቅንዓት አይደለም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ሁሌም እውነተኛ ፍቅርንና አሳቢነትን ያሳያል።<br>5. በተጨማሪም የጌታን ስም በከንቱ መጥራት የለባቸውም ነበር። ስሙን የምንጠቀምበት መንገድ ስለ እርሱ ምን እንደምናስብ ያሳያል። ቅዱስ ስሙን በመጥፎ ንግግር ወይም በመቃላ ሳይሆን በአክብሮትና በአምልኮ ልንጠቀመው ይገባል።<br>6. ኢየሱስ በምድር ላይ እያለ የህግ አዋቂዎች ሊፈትኑት ሞክረው ነበር። ***ማቴዎስ 22፡ 34-40*** እንዲመለከቱ ተማሪዎቹን ጠይቁ። ኢየሱስ ከተናገረው አንፃር ታላቁ ትዕዛዝ ምንድን ነው?<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል- ሙሴ በሲና ተራራ (I)** |
| ክለሳ | ሲና ተራራ እንዴት የተቀደሰ ስፍራ እንደሆነ ከተማሪዎቹ ጋር አስቡ። እዚህ በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ ሙሴን አናገረው ***(ዘጸአት 3፡ 1-12)*** ። ለህይወቱ ፈርቶ በሸሸበት ጊዜ እግዚአብሔር በተጨማሪም ኤሊያስን ቀስ ባለ ድምፅ አናገረው። ***(1 ነገሥት 19፡ 1-13)*** | ቁልፍ ጥቅሱን አጥኑና ይህ ጥቅስ የዛሬውን ጥናት እንዴት እንደሚያጠቃልል ከቡድኑ ጋር ተወያዩ። ጥናት 1ን ለማጠናቀቅ የሚረዷቸውን ጥያቄዎች ጠይቁ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. እግዚአብሔር በጣም ቅዱስና ፍጹም ነው እና እኛ በጣም ኃጢያተኞችና የቆሸሸን ስለሆንን ወደ እርሱ መምጣት የምንችልበት መንገድ የስፈልገናል።<br>2. ለዚህ ነው እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ለእኛ እንዲሞት ወደ ምድር የላከው፣ ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ግንኙነት እንዲኖረን። በጌታ ኢየሱስ ባለን እምነት እግዚአብሔር እንደ ንጹህና ቅዱስ አድርጎ ይመለከተናል! | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. በህይወታቸው ውስጥ የእግዚአብሔርን ቦታ የሚወስድ ወይም ለእነርሱ ከእግዚአብሔር በላይ አስፈላጊ የሆነ ምንምነገር ካለ ተማሪዎቹ እዲያስቡ ጠይቋቸው? አስፈላጊነቱን በድጋሚ ሊያስቡ ይገባል።<br>2. አንዳንዴ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ እና እንደመቃላ የሚጠቀሙት እንደሆን አስቡ? ይህ እግዚአብሔርን በጣም ያሳዝነዋል። ተማሪዎቹ ስሙን እንዴት እንደሚጠቀሙ በጥንቃቄ እንዲያስቡ አድርጉ። |

| | ለ11 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 - ሙሴ<br>ርዕስ - እግዚአብሔርን ማወቅ | ለ11 - ደረጃ 4<br>ጥናት 2 - ህጉ<br>ርዕስ - "የእግዚአብሔር መንገድ" |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ዘጸአት 20፡ 1-12***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ማቴዎስ 22፡ 37***<br><br>***እየተማርን ያለነው፡***<br>1. እግዚአብሔር አንድ እውነተኛ አምላክ ነው።<br>2. የእግዚአብሔር ስም ልዩ ነው እና ክብር ሊሰጠው ይገባል።<br>3. እሑድ እንደ ልዩ የእረፍት ቀን መወሰድ አለበት።<br>4. እናትና አባታችንን ማክበር አስፈላጊ ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ዘጸአት 20፡ 8-11፤ ሉቃስ 13፡ 10-17***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ዘጸአት 20፡ 8***<br><br>***እየተማርን ያለነው፡***<br>1. እግዚአብሔር ሰንበትን ቅዱስ አድርገን እንድንጠብቅ ይፈልጋል።<br>2. ህጎችን ማክበር ሰዎችን ከመውደድ ሊያግደን አይገባም። |
| *መግቢያ* | ህጎች ጥሩ ነገር ስለሆኑበት ስለቀን ተቀን ሁኔታዎች አስቡ ለምሳሌ፡- ጨዋታ በመጫወት ውስጥ፣ ወላጆች ልጆች ትኩስ ነገር እንዳይነኩ ሲያስቆሙ፣ የትራፊክ መብራት ምልክቶች፣ የመኝታ ሰአት፣ ትምህርት ቤት መሄድ ወዘተ። የእርሱ ቅዱስ ህዝብ ሊያደርጋቸው እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ እንዴት ትዕዛዛትን እንደሰጠ - አስርቱን ትዕዛዛት፤ ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ። እግዚአብሔር እንደሚፈልገው እንዲኖሩ የእግዚአብሔር መመሪያ ያስፈልጋቸው ነበር። | ህጎች ጥሩ ነገር ስለሆኑበት ስለቀን ተቀን ሁኔታዎች አስቡ ለምሳሌ፡- ጨዋታ በመጫወት ውስጥ፣ ወላጆች ልጆች ትኩስ ነገር እንዳይነኩ ሲያስቆሙ፣ የትራፊክ መብራት ምልክቶች፣ የመኝታ ሰአት፣ ትምህርት ቤት መሄድ ወ.ዘ.ተ። የእርሱ ቅዱስ ህዝብ ሊያደርጋቸው እና በእርሱ ጥበቃ ስር ለመኖር ከሁሉ የተሻለውን መንገድ ሊያሳያቸው እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ እንዴት አስር ትዕዛዛትን እንደሰጠ ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ። |
| *ማጠናቀቅ* | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>***ተወያዩና አስረዱ፡***<br>1. እግዚአብሔር የሰጠው የመጀመሪያው ትዕዛዝ ***(ቁጥር 1-3)*** ከእርሱ በቀር ሌሎች ምንም አይነት አማልክት ወይም ጣዖታት እንዳይኖሯቸው ነበር። ጣዖት በህይወታችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ቦታ የሚወስድ ማንኛውም ነገር ነው። ይህ ለእግዚአብሔር እጅግ አስፈላጊ ነበር፤ ለዚህ ነው የመጀመሪያው ትዕዛዝ የሆነው። ኢየሱስ እራሱ ***በማቴዎስ 4፡ 10*** ይህንን አረጋግጧል።<br>2. ሁለተኛው ትዕዛዝ ***(ቁጥር 4)*** ሌሎች ምንም አይነት ጣዖታትን እንዳይሰሩ ነበር። ይህ ቀላል ሊመስል ይችላል ነገር ግን የእስራኤል ህዝብ ብዙ ጣዖታትና አማልክት ከነበረበት ስፍራ ከግብፅ ገና መውጣታቸው ነው። ኢየሱስ ***በሉቃስ 16፡13*** ላይ ለዚህ ትዕዛዝ አጽንኦት ሰጥቷል።<br>3. ሦስተኛው ትእዛዝ ***(ቁጥር 7)*** የጌታ የአምላካችንን ስም በከንቱ አለመጠቀም ነበር። የእግዚአብሔር ስም ልዩ ነው እና ያለአግባብ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም። ስሙን የምንጠቀምበት መንገድ ስለእርሱ ምን አይነት ስሜት እንዳለን ያሳየናል። ስሙን በመጥፎ ንግግር እና በመቃላ ውስጥ ሳይሆን በአክብሮት እና በአምልኮ ውስጥ ልንጠቀመው ይገባል።<br>4. አራተኛው ትእዛዝ ***(ቁጥር 8-11)*** በሳምንት ውስጥ ካሉት ከሌሎች ስድስት ቀናት በተለየ መንገድ ሰንበትን ቅዱስ ቀን አድርገው እንዲጠብቁ ነበር። እግዚአብሔር ሰማይን እና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጠረ እና በሰንበት አረፈ፤ እኛም የእርሱን ምሳሌ መከተል አለብን። እግዚአብሔር የምናርፍበት ቀን እንዲኖረን እና እርሱንና ፍጥረቱን እንድናስብ ይፈልጋል።<br>5. አምስተኛው ትእዛዝ ***(ቁጥር 12)*** እናትና አባታቸውን እንዲያከብሩ ነበር። ማክበር ምን ማለት እንደሆነ እና ወላጆቻችንን እንዴት ማክበር እንደምንችል ተወያዩ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል- ሙሴ በሲና ተራራ (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>***ተወያዩና አስረዱ፡***<br>1. ለእስራኤላውያን ከተሰጠው ከአስርቱ ትእዛዛት አንዱ ለእግዚአብሔር የተሰጠ የሰንበትን ቀን መጠበቅ እና መቀደስ ነበር። ***(ዘጸአት 20፡ 8-11)***<br>2. እግዚአብሔር እራሱ ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጠረ እና በሰባተኛው ቀን አረፈ። እኛም ይህን እንድናደርግ እና በሳምንት ውስጥ ከሌሎቹ የተለየ ለማረፍና እርሱንና ፍጥረቱን ለማሰብ የተሰጠ አንድ ቀን እንዲኖረን ይነግረናል።<br>3. እግዚአብሔር መና እንዲሰበስቡ በተሰጣቸው ትዕዛዝ ውስጥ ይህንን ስርአት መመስረት ጀምሮ ነበር። ***(ዘጸአት 16፡ 22-26)***<br>4. ኢየሱስ በምድር ላይ እያለ ለዚህ ትእዛዝ ባለው "አይታ" ሰዎች ደስተኛ አልነበሩም። በሰንበት ቀን ሰዎችን ሲፈውስ ይህንን ትእዛዝ ባለማክበሩ ከሰውት ነበር። ይህ ብዙ ኢጋጥሚዎች ላይ ተፈጥሮ ነበር። አንዱ ***በሉቃስ 13፡ 10-17*** ውስጥ ይገኛል።<br>5. ኢየሱስ ግብዝነታቸውን አሳየ። እራሳቸው በእሑድ ቀን እንስሶቻቸውን ይንከባከባሉ ሆኖም ግን ኢየሱስ ሰውን መንከባከብ አይችልም? በህጉ እጅግ በመጠመዳቸው እና ህጉን በጣም አጥብቀው ከመጠበቃቸው የተነሳ የእግዚአብሔር ፍቃድ ለህይወታቸው በትክክል ምን እንደነበር ረስተው ነበር።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል- ሙሴ በሲና ተራራ (I)** |
| ክለሳ | ***ማቴዎስ 22፡ 37-40ን*** ተመልከቱና እነዚህ ጥቅሶች አስርቱን ትዕዛዛት እንዴት እንደሚያጠቃልሉ አብራሩ። ተማሪዎችን ትምህርት 2ን እንዲያጠናቅቁ የሚረዷቸውን ጥያቄዎች ጠይቁ። | በሁለት ወገን ከፈሉና ሰንበትን ቅዱስ አድርጎ ስለመጠበቅ የቡድን ክርክር አድርጉ፤"ለመደገፍ" እና "ለመቃወም"። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | ***ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:***<br>1. ሌሎች አማልክትንና ጣዖታትን ከእግዚአብሔር ፊት እናደርጋን? ሌሎች ነገሮች ለምሳሌ፡- ስፖርት፣ ቲቪ፣ ስራ፣ ወዘተ. የእግአብሔርን ቦታ እንደማይወስዱ ማረጋገጥ አለብን።<br>2. እንምላለን ወይም የእግዚአብሔርን ስም በተሳሳተ መንገድ እንጠቀማለን? የእግዚአብሔርን ስም ልዩ እና ቅዱስ በሆነ መንገድ ለመጠቀም መጠንቀቅ አለብን።<br>3. እሑዳችንን ከሌሎቹ በተለየ መንገድ እንደ ልዩ ቀን እንጠብቃለን?<br>4. እናትና አባታችንን እናከብራለን? | ***ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:***<br>1. ማናችንም ሁሉንም ትእዛዛት መጠበቅ አንችልም። ኃጢአተኞች ነን እና በራሳችን የእግዚአብሔርን ደረጃ መድረስ አንችልም። ***(ሮሜ 3፡ 23)***<br>2. እነዚህን ትእዛዛት ለመጠበቅ በመሞከር ብቻ እግዚአብሔርን ማስደሰት አንችልም።<br>3. ከእግዚአብሔር ጋር እንድንታረቅ እና የኃጢአታችንን ቅጣት ለመውሰድ ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ። ወደ ህይወታችን ከተቀበልነው ህይወታችንን መኖር እንዳለብን እንድንኖር እንዲረዳን መንፈስ ቅዱስን ይሰጠናል። |

| | ለ11 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 - ሙሴ<br>ርዕስ - እግዚአብሔርን መታዘዝ | ለ11 - ደረጃ 4<br>ጥናት 3 - ህጉ<br>ርዕስ - “መጀመሪያ እግዚአብሔር” |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 20፡ 13-21፤ ማቴዎስ 19፡ 16-30***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማቴዎስ 19፡ 21***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. እግዚአብሔር እነዚህን ትእዛዛቶች የሰጠው እንዲከበሩ ነው።<br>2. እነዚህን ትእዛዞች በማክበር የዘላለም ህይወት ይኖረናል ማለት አይደለም።<br>3. አንዳንድ ጊዜ በህይወታችን ሌሎች ነገሮችን ከእግዚአብሔር በፊት ልናስቀምጥ እንችላለን። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ዘጸአት 20፡ 12-21፣ ማርቆስ 10፡ 17-31***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማቴዎስ 6፡ 24***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. ትእዛዛትና ህግጋት አስፈላጊ ናቸው እና ሊከበሩ ይገባል።<br>2. ትእዛዛትና ህግጋት ብቻ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትን ወይም የዘላለም ሕይወትን አያስገኙም።<br>3. ሌሎች ጣዖታትን በቀላሉ በእግዚአብሔር ቦታ ልናስቀምጥ እንችላለን። |
| መግቢያ | በትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት ህጎችን ለማክበር እንደምንሞክር ነገር ግን አንዳንዴ እረስተን ህጎቹን እንደምንተላለፍ አስቡ። ምሳሌዎችን ስጡ። ይህ የሆነው ሰዎች እና ኃጢአተኞች ስለሆንን እና እንደ እግዚአብሔር ፍጹም መሆን ስለማንችል እንደሆነ አስረዱ። | በትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት ህጎችን ለማክበር እንደምንሞክር ነገር ግን አንዳንዴ እረስተን ህጎቹን እንደምንተላለፍ አስቡ። ምሳሌዎችን ስጡ። ይህ የሆነው ሰዎች እና ኃጢአተኞች ስለሆንን እና እንደ እግዚአብሔር ፍጹም መሆን ስለማንችል እንደሆነ አስረዱ። በምንሰራው ነገር ወደ መንግስተ ሰማይ መንገድ ማግኘት አንችልም። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ስድስተኛው ትእዛዝ አለመግደል ነበር። የኢየሱስን የመግደልን አዲስ ትርጉም ለማየት ***ማቴዎስ 5፡ 21-22ን*** ተመልከቱ። ይህ አሁን ለሰዎች ያለን አመለካከት ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድር አስቡ።<br>2. ሰባተኛው ትእዛዝ አለማመንዝር ነው።<br>3. ስምንተኛው ትእዛዝ አለመስረቅ ነበር። በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ይህን በድጋሚ ተርጉሞ የሆነ ሰው ቲሸርታችሁን ከሰረቀ ኮታችሁንም ጨምሩለት ብሏል! ***(ማቴዎስ 5፡ 40)***<br>4. ዘጠነኛው ትእዛዝ በባልንጀራ ላይ በሐሰት አለመመስከር ነው። ይህ የሆነ ሰው ስለሰራው ነገር መዋሸት ወይም የታሪኩን የሆነ ክፍል አውጥቶ መናገር ማለት እንደሆነ ለተማሪዎቹ አስረዱ። *በዚህ ጉዳይ ላይ ኢየሱስ ምን እንዳለ ለማየት **ማቴዎስ 12፡ 36ን** ተመልከቱ።*<br>5. አስረኛው ትእዛዝ አለመመኘት ወይም ሌሎች ባላቸው ነገር አለመቅናት ነበር። መመኘት አዘጋጃችን እንደመሆኑ በእግዚአብሔር ለይ እምነት ማጣትን ያሳያል።<br>6. ***ማቴዎስ 19፡ 16-30ን*** ከተማሪዎቹ ጋር አንብቡ። እነዚህን ሁሉ ትእዛዛት መጠበቅ ማለት የዘላለምን ህይወት መውረስ ማለት እንዳልሆነ ኢየሱስ እንዴት እንዳሳየ ተወያዩ። ድነት ጥሩ ስራ በመስራት ብቻ አይመጣም ነገር ግን እግዚአብሔርን መውደድ እና በጌታ ኢየሱስ በማመን ሁሉንም ለመተው ፍቃደኛ መሆን የስፈልጋል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ባለጠጋው ሰውዬ ኢየሱስን ጠየቀው (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ የህጉ ፍጻሜ ሆኗል እና አንዳንዱን ትእዛዝ አሻሽሏል፡<br>2. አምስተኛው ትእዛዝ - እናትና አባትህን አክብር - ***ማቴዎስ 10፡ 37*** ኢየሱስ በዚህ ላይ ያለውን አዲስ ምልከታ ያሳየናል።<br>3. ስድስተኛው ትእዛዝ - አትግደል። የኢየሱስን የመግደልን ትርጉም ለማየት ***ማቴዎስ 5፡ 21-22ን*** ተመልከቱ። *ይህ አሁን ለሰዎች ያለን አመለካከት ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድር አስቡ።*<br>4. ሰባተኛው ትእዛዝ - አታመንዝር። ***ማቴዎስ 5፡ 28*** የኢየሱስን ማብራሪያ ያሳየናል።<br>5. ስምንተኛው ትእዛዝ - አትስረቅ። ኢየሱስ ይህንንም እንደገና ተርጉሟል። ***(ማቴዎስ 5፡ 40)***<br>6. ዘጠነኛው ትእዛዝ - በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር። ይህ የሆነ ሰው ስለሰራው ነገር መዋሸት ወይም የታሪኩን የሆነ ክፍል አውጥቶ መናገር ማለት እንደሆነ ለተማሪዎቹ አስረዱ። *በዚህ ጉዳይ ላይ ኢየሱስ ምን እንዳለ ለማየት **ማቴዎስ 12፡ 36ን** ተመልከቱ።*<br>7. **ማርቆስ 10፡ 17-31ን** አንብቡ። ኢየሱስ ድነት ጥሩ ስራን በመስራት ብቻ እንደማይመጣ ነገር ግን እግዚአብሔርን መውደድ፣ ቁሳዊ ሀብትን ለመተው ፈቃደኛ መሆን እና ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ላይ እምነት ሊኖር እንደሚገባ እንዴት እንዳሳየ ተወያዩ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ባለጠጋው ሰውዬ ኢየሱስን ጠየቀው (I)** |
| ክለሳ | በትንሽ ቡድኖች በመሆን በህይወታችን ውስጥ እግዚአብሔርን መጀመሪያ ከማድረግ የሚይዙን ከእግዚአብሔር በላይ አስፈላጊ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነገሮች አስቡ። እርሱን በህይወታችን ውስጥ አንደኛ እንድናደርገው እነዚህን ነገሮች የምናወርድበትን (ማስወገድ አይደለም) ተግባራዊ መንገዶች አብራሩ። | ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ ለውጥ አምጪ ነበር። የኢየሱስ ልደት፣ ህይወት እና ሞት የህግን አስፈላጊነት እንዴት እንደቀየረ ተወያዩ ለምሳሌ:- መልካም ስራዎች እና ትእዛዛትን ማክበር በቂ እንዳልሆነ አስተምሯል። ህጉ ከዚያ በኋላ እንዳያስፈልገን እና ይቅር መባል እንችል ዘንድ ኢየሱስ ለመሞት መጣ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ጥሩ ከሆንን እና ወላጆቻችንን፣ አስተማሪዎቻችንን ወዘተ ካከበርን እግዚአብሔር ይደሰትብናል እና የዘላለም ህይወት ይኖረናል ብለን እናስባለን? ***ኤፌሶን 2፡ 8-9ን*** ተመልከቱ።<br>2. ለእግዚአብሔር ነገሮችን መተው ስለማንፈልግ እንደ ወጣቱ ባለጠጋ ሰው እኛም ተመሳሳይ ስህተት ሰርተን አዝነን እንኼዳለን? | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. እንደ ወጣቱ ባለጠጋ ሰው በቂ እንደሆንን እና ሁሉንም ትእዛዛት እንደምንጠብቅ የምናስብ ነን? ትእዛዛትን መጠበቅ ጥሩ ነው ነገር ግን የዘላለምን ህይወት ወይንም ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትን አይሰጠንም።<br>2. በምንሰራው ነገር ሳይሆን ኢየሱስን በማመን የዘላለምን ህይወት እንቀበላለን። ጌታ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር የምንደርስበት ብቸኛው መንገድ ነው። ***(ዮሐንስ 14፡ 6)*** |

| | ለ11 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 - ሙሴ<br>ርዕስ - እግዚአብሔርን ማሳዘን | ለ11 - ደረጃ 4<br>ጥናት 4 - ህጉ<br>ርዕስ - “የእግዚአብሔር ቃል” |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ዘጸአት 32፡ 1-26***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ዘጸአት 32፡ 26***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. የእስራኤል ህዝብ እግዚአብሔርን ወደ አለመታዘዝ ተመለሱ።<br>2. እግዚአብሔር ለተከተሉት ምህረትን አሳየ እና ያልተከተሉትን ደግሞ ቀጣ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ማርቆስ 7፡ 1-23***<br>**ቁልፍ ጥቅሶች፡** ***1 ጢሞቴዎስ 1፡ 15፣ ሮሜ 5፡ 8***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. ፈሪሳውያን ግብዞች ነበሩ።<br>2. ልምድ (ባህል) ከእግዚአብሔር ቃል የበለጠ አስፈላጊ መሆን የለበትም።<br>3. ኢየሱስ ተከታዮቹን በልባቸው ንፅህና ፈተናቸው። |
| *መግቢያ* | የሆነ ነገር እንዳያደርጉ ስለተጠየቁበት ነገር ግን እንደዚያም ሆኖ ስላደረጉበት ጊዜ እንዲያስቡ ተማሪዎችን ጠይቁ። እዚህ ጋር የተፈጠረው ይህ እንደሆነ እና የእስራኤል ህዝብ እግዚአብሔርን ረስተው የውሸት አማልክትን ወደማምለክ እንደተመለሱ አስረዱ። | ስላሉን ልምዶች (ባህሎች) አስቡ፣ ምናልባት በቤተሰባችን ወይንም በቸርች ውስጥ። ከእነዚህ አንዳንዶቹ ጥሩ እና አንዳንዶቹ ደግሞ መጥፎ ሊሆኑ ይችላሉ። ጥሩ ልምዶች በእግዚአብሔርን ቃል ላይ ብርሃንን ያበራሉ እና እንድናገለግለው እና እንድንታዘዘው ያነሳሱናል። ነገር ግን መቼም ቢሆን ከእግዚአብሔር ቃል የበለጠ አስፈላጊ መሆን የለባቸውም። |
| *ማጠናቀቅ* | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. የእስራኤል ህዝብ ሙሴ ከሲና ተራራ ተመልሶ እስኪ.ወርድ በመጠበቅ ትእግስት አጡ። ስለዚህ ለማምለክ የውሸት አማልክትን ሰሩ። ***(32፡ 1-4)*** መስራት እና እራሳቸው መቆጣጠር የሚችሉትን የራሳቸውን ጣዖት መስራት ፈለጉ። የመጀመሪያዎቹን ሁለት ትእዛዛት ረስተው ነበር። ***(ዘጸአት 20፡1-5)***<br>2. ባለመታዘዛቸውና በኃጢአታቸው ምክንያት ህዝቡን ሁሉ ለማጥፋት እግዚአብሔር ዝግጁ ነበር ***(32፡ 10)*** ነገር ግን ሙሴ እግዚአብሔር ይህን እንዳያደርግ ተማፀነ። እዚህ ጋር እግዚአብሔር ሁሉንም ባለማጥፋት ፍቅሩን እና ምህረቱን አሳየ። *የምህረትን ትርጉም አስረዱ (ከሚገባን ቅጣት መዳን)።*<br>3. ጌታን ለመከተል ፍቃደኛ ለሆኑት እግዚአብሔር ምህረትን አሳየ ***(32፡ 26)*** ለሌሎቹ ግን ባለመታዘዛቸው ተገደሉ።<br>4. የእስራኤልን ህዝብ ወደ ስህተት በመምራቱ ሙሴ በአሮን አዝኖ ነበር። የእስራኤል ህዝብ እያደረጉት የነበረው ስህተት እንደሆነ ማወቅ ነበረበት ነገር ግን ቅሬታቸውን ሰምቶ ለማምለክ ይህንን የወርቅ ጥጃ እንዲሰሩ ረዳቸው። ***(32፡ 22-24)*** *አንዳንድ ጊዜ ትክክል እንዳልሆኑ የምናውቃቸውን ነገሮች ሁሉም ሰው እያደረገው ስለሆነ ብቻ እናደርጋለን?*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 4ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሙሴ እና የወርቁ ጥጃ (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. ኢየሱስ ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ሙሴና የእስራኤል ህዝብ የተሰጣቸው ህግጋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነበር። ሆኖም ከእግዚአብሔር ሳይሆን በልምድ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያሳዩ ብዙ ተጨማሪ ህግና ትእዛዛት ተጨምረው ነበር።<br>2. ፈሪሳውያን በጣም ፈራጅ ስለነበሩ ኢየሱስን ለመመርመር መጡ። የእግዚአብሔርን ህግ እየጣሱ ነው በማለት የኢየሱስን ደቀመዛሙርት ስላደረጉት ነገር ወቀሷቸው። ***(ማርቆስ 7፡ 5)***<br>3. ፈሪሳውያን ግብዝ ሰዎች ነበሩ፡ ሁሉም እንዲያያቸው ድርጊታቸው ከእግዚአብሔር ከራቀው ከልባቸው የመነጨ ሳይሆን ውጫዊ ነበር። ቅዱስ ሆነው መታየት ስለሚፈልጉ እና ክብራቸውን ለመጨመር ትክክለኛ ላልሆነ ምክንያት ነበር የሚያመልኩት።<br>4. ኢየሱስ ፈሪሳውያንን እራሳቸው በፈጠሩት በራሳቸው ህግ ምክንያት የእግዚአብሔርን ሕግ ባለማክበራቸው ከሰሳቸው ለምሳሌ፡- ለእናትና ለአባታቸው ማሰብ ማቆማቸው። እግዚአብሔርን ከማክበር ይልቅ ቅዱስ ሆኖ ለመታየት ሕጎችን እና ልማዶችን በመጠበቃቸው ገሰጻቸው።<br>5. ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የንጹህ ልብን አስፈላጊነት እና ንጹህ ልብ እንዲኖረን ካልተጋን እንዴት ክፉ፣ ኃጢአተኛ ባህሪ ከህይወታችን ሊወጣ እንደሚችል አስተማረ። ***(ማርቆስ 13፡ 17-19)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 4ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ የሚሆን ስዕል የለም** |
| ክለሳ | ትምህርቱን ለመከለስ እንዲያስችል እና እንዲያጠናቅቁት እንዲረዳቸው በዛሬው ታሪክ ላይ ተማሪዎቹን ፈትኑ። | ***ማርቆስ 7፡ 21-22ን*** እንዲመለከቱ እና ይህን ***ከፊልጵስዩስ 4፡ 8*** ጋር እንዲያስተያዩ ተማሪዎችን ጠይቁ። በህይወታችን ውስጥ የትኞቹ ባህሪያቶች ሊኖሩን ይገባል እና እንዴት ይህን ልናደርግ እንችላለን? |
| *ከሕይወት ጋር ማዛመድ* | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. ኃጢያት ቢያደርጉም እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ምሕረትን እንዳሳየው ለሰራነው ስሕተት ይቅርታን ከጠየቅን ለእኛም ምሕረትን ሊያሳየን ይችላል።<br>2. እግዚአብሔር አፍቃሪ አምላክ ነው እና በኃጢአታችን ምክንያት ሊቀጣን አይፈልግም። ለዚያ ነው የሚገባንን ቅጣት እንዳንወስድ ልጁን ለእኛ ሲል እንዲሞት የላከው። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. የልባችንን ሁኔታ እና የውስጥ ፍላጎታችንን ሳናስተውል ለመፍረድ እና ሰዎችን ለመክሰስ መፍጠን የለብንም።<br>2. እንደ ፈሪሳውያን በራሳችን ህግና ልማዶች መያዝ እና እንደምንኖርባቸው ብቸኛ መንገዶች ማየት የለብንም። ይህ እግዚአብሔርን ከማክበር እና ከመውደድ ሊያስቆመን ይችላል። በጥርጣሬ ውስጥ ከሆንን ስለራሳችን ባህሪ እንዲያሳየን ወደ ጌታ ኢየሱስ መመልከት አለብን። |

| | **ለ12 - ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 1 - የክርስቶስ ልደት ደስታ!**<br>**ርዕስ - የእግዚአብሔር ተስፋዎች** | **ለ12 - ደረጃ 4**<br>**ጥናት 1 - የክርስቶስ ልደት ደስታ!**<br>**ርዕስ - ወንድ ልጅ ተወልዷል** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል: *ኢሳይያስ 9፡ 1-7፤ ሚክያስ 5፡ 2***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ኢሳይያስ 9፡ 6***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. የኢየሱስ መወለድ ኢየሱስ ከመወለዱ ከብዙ መቶ አመታት በፊት ተተንብዮ ነበር።<br>2. ብዙ ሰዎች የኢየሱስን መወለድ በጉጉት እየጠበቁ ነበር።<br>3. ኢየሱስ ለረዥም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው መሢሕ፣ የአለም ብርሃን ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል: *ሉቃስ 1፡ 26-38፤ ሉቃስ 2፡ 1-7***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ሉቃስ 1፡ 35***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. የኢየሱስ መወለድ ከብዙ መቶ አመታት በፊት የተጻፉትን ትንቢቶች ፈጽሟል።<br>2. ማርያምና ዮሴፍ እግዚአብሔር ለአለም ባለው እቅድ አካል አድርጎ እንዲጠቀማቸው ፍቃደኛ ነበሩ።<br>3. የኢየሱስ መወለድ በቤቴልሔም ውስጥ አልታወቀም ነበር ማለት ይቻላል። |
| *መግቢያ* | እርጉዝ የነበረ ሰው የሚያውቁ ከሆነ ተማሪዎችን ጠይቁ። ለወላጆች ልጁ እስኪወለድ በመጠበቅ 9 ወር ምን ያህል ረዥም ሊመስላቸው እንደሚችል አስረዷቸው። ነቢያቶች ለእስራኤል ህዝብ ስለ ኢየሱስ መምጣት ተናግረዋል ነገር ግን ከመወለዱ በፊት ለብዙ መቶ አመታት መጠበቅ ነበረባቸው። | እንዴት እቅዶችን ልናቅድ እንደምንችል ከተማሪዎቹ ጋር ተወያዩ ለምሳሌ፡- ለበአላት፣ ለልደት ዝግጅቶች፣ ለሰርጎች፣ ጓደኞቻችንን ለመጠየቅ። እነዚህ እቅዶች በተሳሳተ መንገድ ሲሄዱ ወይም እኛ እንዲሆን ባሰብነው መንገድ ሳይሄዱ ሲቀሩ እንዴት ልንሆን እንደምንችል አስቡ። ማርያም ዮሴፍን ለማግባት እቅድ እንደነበራት ነገር ግን እግዚአብሔር ለእርሷና ለዮሴፍ ከዚህ የበለጠ እቅድ እንደነበረው ተወያዩ። |
| *ማጠናቀቅ* | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ከመጀመሩ በፊት የእግር ኳስ ጨዋታ ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ወይም ከ40 አመታት በኋላ ምን እያደረግን ሊሆን እንደሚችል እንደማናውቅ ከተማሪዎቹ ጋር ተወያዩ። ያንን መገመት አንችልም። ሆኖም አሳይያስ እና ሚክያስ ነገሮቹ ከመሆናቸው ከብዙ መቶ አመታት በፊት የኢየሱስን ወደ ምድር መምጣት ተንብየዋል።<br>2. ነብዩ ኢሳይያስ እንዴት በጨለማ ያሉ ሰዎች በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ላሉት እንኳን ሳይቀር የሚያበራ ታላቅ ብርሃን እንደሚያዩ ይናገራል። ይህ ታላቅ ብርሃን ማን እንደሆነ ለማየት ***ዮሐንስ 8፡ 12ን*** እንዲመለከቱ ተማሪዎችን ጠይቁ።<br>3. በኢሳይያስ ውስጥ ያሉት እነዚህ ትንቢቶች ከብዙ መቶ አመታት በኋላ እንዴት እንደተፈጸሙ ለማየት ***ማቴዎስ 4፡ 14-16ን*** እንዲመለከቱ ተማሪዎቹን ጠይቁ።<br>4. የእግዚአብሔር አለምን የማዳን ታላቅ እቅድ እንዴት አስደናቂ እንደነበር እና አይሁዶች ይህ እቅድ እንዲፈጸም እንዴት ለብዙ መቶ አመታት እንደጠበቁ ከተማሪዎቹ ጋር ተወያዩ። ብዙዎቹ እርሱ ሲወለድ ለማየት በህይወት አልነበሩም። እንደአዳኛችን በራሳችን እርሱን እንድናውቀው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የኢየሱስ ሙሉ የህይወት ታሪክ መኖሩ እንዴት አስደናቂ እንደሆነ አስቡ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ስለኢየሱስ መወለድ የሚናገሩ ትንቢቶች** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. እግዚአብሔር ልጅ እንደምትወልድ ለማርያም እንዲነግራት መልአኩን ገብርኤልን ላከ። ማርያም ድንግል በመሆኗ እና ይህ እንዴት እንደሚሆን ስላልገባት ፈርታለች። ነገር ግን መልአኩ አረጋጋት እና በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን እንዳገኘች ነገራት። ***(ሉቃስ 1፡ 26-34)***<br>2. ምን እየተፈጠረ እንደነበር ማርያም ሙሉ በሙሉ ላይገባት ይችላል ነገር ግን እግዚአብሔርን ማመን እንዳለባት ታውቅ ነበር። ***(1፡ 38)*** ህይወታችንን እስከመጨረሻው ለሚቀይሩ ዜናዎች ምን አይነት ምላሽ ልንሰጥ እንደምንችል ተወያዩ።<br>3. ማርያም የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ማርያምና ዮሴፍ ለመጻፍ ከናዝሬት ወደ ቤተልሔም መጓዝ ነበረባቸው። ይህ ጽሁፈት የታዘዘው በአውግስጦስ ነበር። ***(ሉቃስ 2፡ 1-5)*** አውግስጦስ ነገሩን እየተቆጣጠረ እንደሆነ አስቦ ሊሆን እንደሚችል ነገር ግን በእውነቱ እግዚአብሔር እንደነበር እና ጌታ ኢየሱስ በቤተልሔም እንዲወለድ ይህ የእርሱ የጊዜና የእቅድ አካል እንደነበር ተወያዩ።<br>4. ኢየሱስ በቤተልሔም የተወለደው የሚክያስ ትንቢት እንዲፈጸም ነበር። ***(ሚክያስ 5፡ 2)*** ኢየሱስ ትንቢቶቹን መፈጸሙ ለምን አስፈላጊ እንደነበር አስቡ።<br>5. ኢየሱስ ሲወለድ ማርያም በመጠቅለያ ጠቀለለችው እና በግርግም አስተኛችው። ***(2፡ 7)***<br>6. አይሁዶች ለረዥም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረውን ንጉሳቸውን በንጉሳዊ ቤተሰብ ውስጥ እስኪመጣ እንዴት ሲጠብቁ እንደነበር ሆኖም ኢየሱስ ከእንስሶች ጋር እንደተወለደ ተወያዩ። እግዚአብሔርን መገደብ እና ነገሮች በተወሰነ መንገድ እንዲሆኑ መጠበቅ እንደሌለብን አስረዱ። ይህ እግዚአብሔር ለኢየሱስ የነበረው እቅድ አካል ነበር። ማርያምን እና ዮሴፍን እየመራቸው እና የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ እያዘጋጀላቸው ነበር። ***2 ቆሮንቶስ 8፡ 9ን*** አንብቡ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 1ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል- የኢየሱስ መወለድ** |
| *ክለሳ* | ኢሳይያስ 9፡ 6 እና 7ን ከተማሪዎቹ ጋር አንብቡ እና ኢየሱስን ይገልፃል ብሎ ኢሳይያስ የተነበያቸውን የተዘረዘሩትን ስሞች በጠቅላላ አብራሩ። ጌታ ኢየሱስ በእያንዳንዱ እንዴት ሊጠራ እንደሚችል ከተማሪዎቹ ጋር መርምሩ። | ተማሪዎቹ ማርያምና ዮሴፍን እንደሆኑ እንዲያስቡ ጠይቁ። በዚህ ጥናት ላይ በተፈጠሩት ክስተቶች በበመርኮዝ ከማርያም ወይም ከዮሴፍ እይታ አንጻር ማስታወሻ እንዲጽፉ ጠይቋቸው። |
| *ከሕይወት ጋር ማዛመድ* | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ስለ ብርሃን ባህሪያት እና ኢየሱስ እንዴት የአለም ብርሃን ተብሎ ሊጠራ እንደሚችል እንዲያስቡ ተማሪዎቹን ጠይቁ። ***(ኢሳይያስ 9፡ 2)***<br>2. ኢየሱስን እንደ አለም ብርሃን እንዲመለከቱት ተማሪዎችን አነሳሱ። የገና መብራቶችን ስናይ ምናልባትም ኢየሱስ ከኃጢአታችን ቅጣት ሊያድነን ወደ ምድር የተላከ እውነተኛው ብርሃን እንደሆነ ያስታውሱናል። | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ባንረዳቸውም እንኳን ለህይወታችው የእግዚአብሔርን እቅድ ለመቀበል ተማሪዎች የማርያምን ያክል ዝግጁ መሆናቸውን ግምት ውስጥ አስገቡ።<br>2. ሰዎች ለረዥም ጊዜ ለጠበቁት ለዚህ ኢየሱስ ምን አይነት ምላሽ ነው የምንሰጠው? በገና በአል ጊዜ በግርግም ውስጥ እንደተቀመጠ ህጻን ብቻ ነው የምናየው? ወይስ ቀን በቀን ልትኖሩለት የምትፈልጉት አዳኝ ነው? |

| | ለ12 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 - የክርስቶስ ልደት ደስታ!<br>ርዕስ - የማርያም አስገራሚ ነገር! | ለ12 - ደረጃ 4<br>ጥናት 2 - የክርስቶስ ልደት ደስታ!<br>ርዕስ - ስለ አዳኝ ተነገረ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ሉቃስ 1፡ 26-38***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሉቃስ 1፡ 32***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እቅድ አስፈላጊ አካል እንደነበር በማሳየት ስለ ኢየሱስ የተነገሩት ትንቢቶች ተፈጽመዋል።<br>2. እኛ ልክ እንደ ማርያም እና ዮሴፍ የእራሳችንን እቅድ ልናቅድ እንችላን ነገር ግን ሁሌም ለህይወታችን የእግዚአብሔር እቅድ ነው የሚበልጠው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡** ***ሉቃስ 2፡ 8-20***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሉቃስ 2፡ 11***<br><br>**እየተማርን ያለነው፡**<br>1. በሰማይ ያሉት መላእክት ክርስቶስ ስለሆነው መሲሕ መምጣት ጓጉተው ነበር።<br>2. ከመላእክቶቹ ከሰሙት ነገር በኋላ እረኞቹ ይህንን ህጻን ኢየሱስን ለማግኘት ጓጉተው ነበር።<br>3. እኛም መጓጓት እና የኢየሱስን ልደት ማክበር አለብን። |
| መግቢያ | እንዴት እቅዶችን ልናቅድ እንደምንችል ከተማሪዎቹ ጋር ተወያዩ ለምሳሌ:- ለበአላት፣ ለልደት ዝግጅቶች፣ ለሰርጎች፣ ጓደኞቻችንን ለመጠየቅ። እነዚህ እቅዶች በተሳሳተ መንገድ ሲሄዱ ወይም እኛ እንዲሆን ባሰብነው መንገድ ሳይሄዱ ሲቀሩ እንዴት ልንሆን እንደምንችል አስቡ። ማርያም ዮሴፍን ለማግባት እቅድ እንደነበራት ነገር ግን እግዚአብሔር ለእርሷና ለዮሴፍ ከዚህ የበለጠ እቅድ እንደነበረው ተወያዩ። | በተለምዶ ልጅ ሲወለድ እንዴት እንደሚነገር አስቡ፤ ምናልባትም በወላጆቹ፣ በካርድ ወይም የልጁን ፎቶ በመጠቀም። የሆነ ደስታ እና ሀሴት አለው። ኢየሱስ ተራ ሕፃን እንዳልነበረም ስለዚህም ደግሞ መወለዱ በተለመደ መንገድ እንደማይነገር አስረዱ። የመጣው ወደ ተራ ሰዎች ነበር ስለዚህም መወለዱን ለመስማት መጀመሪያ የሆኑት እረኞቹ እንደነበሩ አስታውሱ። |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. እግዚአብሔር ገና ባታገባም እንኳን ልጅ እንደምትወልድ እንዲነግራት መልአኩ ገብርኤልን ወደ ማርያም ላከው። ***(ቁጥር 31)***<br>2. ማርያም ተጨንቃለች እና ይህ ሁላ እንዴት እንደሚሆን አልገባትም ሆኖም መልአኩ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን እንዳገኘች እና ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ አረጋገጠላት። ***(ቁጥር 34-37)*** *ይህ ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎቹ ጋር ተወያዩ።*<br>3. *ማርያም ከገሊላ የመሆኗን እና ዮሴፍ ከዳዊት የዘር ሀረግ የመሆኑን አስፈላጊ ነጥቦች ግለጹ። ይህ ለምን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ከተማሪዎቹ ጋር ተወያዩ፤ ይህ የሚመጣው መሲሕ ከገሊላ እንደሚመጣ* ***(ኢሳይያስ 9፡ 1)*** *እና የዳዊት ዘር እንደሚሆን* ***(ኢሳይያስ 9፡ 7)*** ነቢያቶቹ ተናግረዋል። እነዚህ እውነታዎች ሁሉንም ትንቢቶች የሚፈጸሙ የትልቁ ስዕል አንድ አካል ናቸው።<br>4. ምን እየተፈጠረ እንደነበር ማርያም ሙሉ በሙሉ ላይገባት ይችላል ነገር ግን እግዚአብሔርን ማመን እንዳለባት ታውቅ ነበር። ***(ቁጥር 38)*** *ህይወታችንን እስከመጨረሻው ለሚቀይሩ ዜናዎች ምን አይነት ምላሽ ልንሰጥ እንደምንችል ተወያዩ።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - የኢየሱስ መወለድ** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ፡**<br>1. ኢየሱስ በተወለደበት ምሽት እረኞች በጎቻቸውን እየጠበቁ በሜዳ ነበሩ። በተለምዶ በምሽት በግ መጠበቅ ረጭ ያለ እንደሆነ እና ለእረኞቹ ምናልባትም አሰልቺ እንደሚሆን ጥቀሱ። ***(ቁጥር 8)***<br>2. ነገር ግን በዚህ ምሽት አስደናቂ ነገር ተፈጠረ! መልአክ ተገለጠላቸውና ሁሉም ደነገጡ! *ምን ተሰምቷቸው ሊሆን እንደሚችል ተማሪዎቹን ጠይቁ።* ***(ቁጥር 9)***<br>3. *መልአኩ ኢየሱስ አዳኝ እንደተወለደ ሊነግራቸው መጥቷል።* ***(ቁጥር 11)***<br>4. ከመልአኩ ጋር ተጨማሪ ብዙ መላእክት ተገለጡ እና የጌታ ኢየሱስን ወደ ምድር መምጣት በማስመልከት ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቀረቡ። *ይህ እይታ በጨለማ ውስጥ ከበጎች ጋር ለነበሩት እረኞች ምን ያህል አስደናቂ ሊሆን እንደሚችል አስረዱ።* ***(ቁጥር 13-14)***<br>5. መላእክቶቹ ከሄዱ በኋላ እረኞቹ ይህን ህፃን እራሳቸው ሄደው ለማየት ፈጠኑ። *በዚህ ጊዜ ምን ተሰምቷቸው ሊሆን እንደሚችል አስቡ፤ ምናልባትም በአይምሮአቸው የፈጠሩት ነገር እንደሆነ ፣ ወይም መልአኩ ስህተት እንደሆነ አሰበዋል።*<br>6. ልክ መልአኩ እንደገለጸው ህፃኑን አገኙት! ***(ቁጥር 16)*** እግዚአብሔርን አከበሩትና አመሰገኑት እና ለሁሉም ስለተወለደው አዳኝ መናገር ጀመሩ። ***(ቁጥር 17 እና 20)***<br>7. እረኞቹ ይህንን ህፃን በማየታቸው ምን ያክል እንደተደሰቱ እና ወዲያውኑ ስለእርሱ ለሰዎች መናገር እንደጀመሩ እና መልካሙን ዜና ለሌሎች ማካፈል እንደፈለጉ አስቡ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 2ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - እረኞች የኢየሱስን መወለድ ሰሙ** |
| ክለሳ | በቁልፍ ጥቅሱ ውስጥ መልአኩ ገብርኤል የተናገራቸውን ተስፋዎች በሙሉ ዘርዝሩ። ስለሚመጣው ንጉስ እና ምን ሊያደርግ እንደመጣ ከዚህ ጥቅስ ምን እንማራለን? እነዚህ ተስፋዎች ስለ ኢየሱስ እንደሆኑ በእውነት እናምናለን? | ይህ የልደት መግለጫ ምን ሊመስል እንደሚችል በአይምሮአችሁ የምትስሉትን ነገር የሚያሳይ ፖስተር ወይም የግድግዳ ስዕል ስሩ። በስዕላችሁ ውስጥ መልአኩ የተናገረውን ነገር (ቁልፍ ጥቅሱን) ጨምሩ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. ባንረዳቸውም እንኳን ለህይወታችን የእግዚአብሔርን እቅዶች ለመቀበል የማርያምን ያክል ዝግጁ ነን?<br>2. ሰዎች ለረዥም ጊዜ ለጠበቁት ለኢየሱስ ምን አይነት ምላሽ እንሰጣለን?<br>3. እቅዶች እኛ በፈለግናቸው መንገድ ባይሆኑም እንኳን ስለ ወደፊታችን ጌታን ለማመን ፍቃደኛ ነን? | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን፡**<br>1. ስለኢየሱስ ታሪክ ለመናገር እኛም እንደ እረኞቹ እንጓጓለን? የእርሱ ልደት እነርሱ ያደረጉትን ያክል አስደናቂ እንደሆነ ታስባላችሁ?<br>2. የክርስቶስን ልደት ለትክክለኛ ምክንያቶች ነው የምናከብረው? ስለ ስጦታዎቹና ዝግጅቱ ብቻ ነው ወይስ አዳኛችን ለመሆን የኢየሱስን ወደ ምድር መምጣት እናስባለን? |

| | ለ12 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 - የክርስቶስ ልደት ደስታ!<br>ርዕስ - የኢየሱስ ልደት | ለ12 - ደረጃ 4<br>ጥናት 3 - የክርስቶስ ልደት ደስታ!<br>ርዕስ - ንጉሡ ነገሥት ሲመለክ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ሉቃስ 2፡ 1-7***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***2 ቆሮንቶስ 8፡ 9***<br><br>***እየተማርን ያለነው:***<br>1. በቤተልሔም ውስጥ የኢየሱስን ልደት አላስተዋሉት ነበር።<br>2. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ በእውነት ሰው ነበር።<br>3. ውልደቱ ከብዙ መቶ አመታት በፊት የተነገሩትን ትንቢቶች ፈጽሟል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ማቴዎ 2፡ 1-12***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማቴዎስ 2፡ 11***<br><br>***እየተማርን ያለነው:***<br>1. ኢየሱስ ሲወለድ አንዳንዶች ተቀበሉት ሌሎች ደግሞ አልተቀበሉትም።<br>2. እግዚአብሔር ኢየሱስን፣ ማርያምን እና ዮሴፍን እየተንከባከባቸው እና እየጠበቃቸው ነበር። |
| *መግቢያ* | ንጉሥ ወይም ንግስት ሰፈራቸውን ሊጎበኙ ቢመጡ ምን አይነት ምላሽ እንደሚሰጡ ከተማሪዎቹ ጋር ተወያዩ፤ ሰዎች በጣም ይደሰቱና ትላልቅ ክብረ በአላቶችን ያደርጋሉ! ነገር ግን ኢየሱስ ሲወለድ ማንም አላወቀም ነበር። አልታወቀም ነበር። ለእርሱ የሚሆን ቦታ እንኳን አልነበረም እና አልጋው በግርግም ነበር። | ልጅ ሲወለድ ምን እንደምናደርግ እንዲያስቡ ተማሪዎቹን ጠይቁ። እንዴት ስጦታ እንደምንገዛ፣ ሄደን ህፃኑን እንደምናይና እንደምንይዘው አስቡ። ይህ አስደሳች የሐሴት ጊዜ እንደሆነ አስረዱ። |
| *ማጠናቀቅ* | ***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ***<br><br>***ተወያዩና አስረዱ:***<br>1. *ማርያም እና ዮሴፍ ለጽህፈት ከናዝሬት ወደ ቤተልሔም መጓዝ ነበረባቸው፣ ለመቆጠርና ለመመዝገብ። ለእርጉዝ ሴት ይህ ረዥም ጉዞ በተለይም በእነዚያ ቀናት ምን ያህል አድካሚ ሊሆን እንደሚችል አስቡ።* ***(ቁጥር 1-4)***<br>2. *ይህ ጽህፈት በአውግስጦስ ነበር የታዘዘው። አውግስጦስ ነገሩን እየተቆጣጠረ እንደሆነ አስቦ ሊሆን እንደሚችል ነገር ግን በእውነቱ እግዚአብሔር እንደነበር እና ጌታ ኢየሱስ በቤተልሔም እንዲወለድ ይህ የእርሱ የጊዜና የእቅድ አካል እንደነበር ተወያዩ።*<br>3. *በዚያ ሳሉ ኢየሱስ ከእንስሶች ጋር በበረት ውስጥ ተወለደ እና በግርግም ውስጥ ተኛ።* ***(ቁጥር 7)***<br>4. *ኢየሱስ በቤተልሔም የተወለደው መሢሕ በቤተልሔም ውስጥ እንደሚወለድ የተነገረው ትንቢት እንዲፈጸም ነው።* ***(ሚክያስ 5፡ 2)*** *ኢየሱስ ትንቢቶቹን መፈጸሙ ለምን በጣም አስፈላጊ እንደነበር አስቡ።*<br>5. *ንጉሥ የሚወለድበት የተለመደ ሁኔታ እንዳልነበረ ነገር ግን ይህ ለጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር እቅድ አካል እንደነበር ተወያዩ። እርሱ ማርያምና ዮሴፍን እየመራቸው እና የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ እያዘጋጀላቸው ነበር።*<br>6. *አይሁዶች ለረዥም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረውን ንጉሳቸውን በንጉሳዊ ቤተሰብ ውስጥ እስኪመጣ እንዴት ሲጠብቁ እንደነበር ሆኖም ኢየሱስ ከእንስሶች ጋር እንደተወለደ ተወያዩ። እግዚአብሔርን መገደብ እና ነገሮች በሆነ መንገድ እንዲሆኑ ብቻ መጠበቅ እንደሌለብን አስረዱ።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - የኢየሱስ መወለድ** | ***የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ***<br><br>***ተወያዩና አስረዱ:***<br>1. *ኢየሱስ ሲወለድ ንጉሥ ሄሮድስ ንጉሥ ነበር።*<br>2. *ሰብአ ሰገል ከምሥራቅ ተጉዘዋል እና አዲስ ንጉሥ እንደሚወለድ የነገራቸውን ኮከብ አይተዋል። ይህ ንጉሥ ማን እንደነበረ ንጉሥ ሄሮድስን ጠየቁት።* ***(ቁጥር 1-2)***<br>3. *ንጉሥ ሄሮድስ ዙፋኑ ላይ የእርሱን ቦታ የሚወስድ ሌላ ንጉሥ ሊኖር እንደሚችል በሰማው ዜና ተረብሾ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት ጌታ ኢየሱስ እንደነበረው በውልደት ትክክለኛ የእስራኤል ንጉሥ ስላልነበረ ነው። ስለሆነም ስለዚህ "ንጉሥ" በጥርጣሬ ተሞልቶ ነበር።* ***(ቁጥር 3)***<br>4. *እርሱም ሄዶ እንዲሰግድለት ሰብአ ሰገል ሄደው ይህን ንጉሥ እንዲያገኙት ነገራቸው። ነገር ግን ሄሮድስ ህፃኑን ለመግደል እያቀደ ነበር።* ***(ቁጥር 7-8)***<br>5. *ሰብአ ሰገል ኮከቡን ተከተሉ እና ህፃኑን በቤቱ ውስጥ አገኙት። እነርሱ ሲመጡ አንድ ወይም ሁለት አመት ቢሆነው ነው። ሲያዩት እጅግ በጣም ተደስተው ነበር! ሰገዱለት እና የወርቅ፣ የእጣን እና የከርቤ ስጦታ ሰጡት።* ***(ቁጥር 10-11)***<br>6. *ኢየሱስን መግደል ስለሚፈልግ ንጉሥ ሄሮድስን ላለማግኘት ሰብአ ሰገል በሌላ መንገድ ወደ ቤት እንዲሄዱ እግዚአብሔር በህልም ተናገራቸው። እግዚአብሔርን ታዘዙ እና ኢየሱስን ለመጠበቅ መንገዳቸውን ቀየሩ።* ***(ቁጥር 12)***<br>7. *ኢየሱስ በተወለደበት ጊዜ ሰብአ ሰገል የሰጡትን ምላሽ ከሄሮድስ ምላሽ ጋር አነፃፅሩት። ኢየሱስን እንደ መሲሕ እና የአለም አዳኝ ነበር የተቀበሉት በአንፃሩ ሄሮድስ ኢየሱስን ያየው ለዙፋኑ ስጋት እንደሆነ ነበር።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 3ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ፡ ስዕል - ሰብአ ሰገሎች ኢየሱስን ጎበኙ** |
| *ክለሳ* | *በትንሽ ቡድኖች በመሆን የኢየሱስን መወለድ ለማወጅ ለቤተልሔም ጋዜጣ የሚሆን ጽሁፍ አዘጋጁ።* | ትምህርቱን ለመከለስ እና ለጥናት 3 እነርሱን ለመርዳት በዛሬው ጥናት ላይ ተማሪዎቹን ፈትኑ። |
| **ከሕይወት ጋር ማዘመድ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. *ሰዎች ስለእርሱ ስላላወቁ ኢየሱስ ሲወለድ አላስተዋሉትም ነበር። አሁን እኛ ስለእርሱ እናውቃለን ነገር ግን እናስተውለዋለን? በገና በአል ጊዜ በግርግም ውስጥ እንደተኛ ህፃን ብቻ ነው የምናየው? ወይስ ቀን በቀን ልንኖርለት የምንፈልገው አዳኝ ነው?*<br>2. *ወደ መስቀል ሄዶ ለኃጢአታችን ለመሞት ኢየሱስ ሰው ሆነ። የዚህን ታላቅነት በእውነት እንረዳለን?* | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. *በታሪኩ ውስጥ እንዳሉት ሰብአ ሰገል ነን? ጌታ ኢየሱስን ለማምለክ እና ለእርሱ ስጦታ ለመስጠት እንፈልገዋለን? ወይስ እኛ በምላሹ ምንም ሳንሰጠው እርሱ ስጦታ እንዲሰጠንና እንዲረዳን እንጠብቃለን?*<br>2. *'ጠቢብ' የሆኑት አሁንም ማግኘት ለሚፈልጉት ነገር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ኢየሱስን ስለማንነቱ ይፈልጉትና ያመልኩታል።* |

| | ለ12 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 - የክርስቶስ ልደት ደስታ!<br>ርዕስ - የመላእክቱ መልዕክት | ለ12 - ደረጃ 4<br>ጥናት 4 - የገና ድንቅ ነገር<br>ርዕስ - ደህንነት! |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ሉቃስ 2፡ 8-20***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 2፡ 11***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. በሰማይ ያሉት መላእክት ስለ ጌታ ኢየሱስ (የእግዚአብሔር ልጅ) መምጣት ጓጉተው ነበር።<br>2. እረኞቹ ከመላእክቶቹ ከሰሙት ነገር በኋላ ሕፃኑን ኢየሱስን ለማግኘት ጓጉተው ነበር።<br>3. እኛም መደሰትና የኢየሱስን ልደት ማክበር አለብን። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:** ***ሉቃስ 2፡ 25-40***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ኢሳይያስ 7፡14***<br><br>**እየተማርን ያለነው:**<br>1. በሕፃኑ ኢየሱስ መምጣት ሰዎች ተደስተው ነበር።<br>2. ለኢየሱስ የተደባለቁ ምላሾች ይኖራሉ። ሰዎች ወይ ሙሉ በሙሉ በደስታ ኢየሱስን ይቀበሉታል ወይንም ሙሉ በሙሉ እሱን አይቀበሉትም።<br>3. ጌታ ኢየሱስ በዓለም ውስጥ ብርሃን እንዲሆን የተላከ የእግዚአብሔር ማዳን ነው። |
| መግቢያ | በተለምዶ ልጅ ሲወለድ እንዴት እንደሚነገር አስቡ፤ ምናልባትም በወላጆቹ፣ በካርድ ወይም የልጁን ፎቶ በመጠቀም። የሆነ ደስታ እና ሀሴት አለው። ኢየሱስ ተራ ሕፃን እንዳልነበረ ስለዚህም ደግሞ መወለዱ በተለመደ መንገድ እንደማይነገር አስረዱ። | ሕፃን ልጅ ሲወለድ ሰዎች እስኪመጣ ለዘጠኝ ወር ሲጠብቁ ስለነበር ብዙ ደስታ አለው። በዚህ ጥናት ውስጥ የምንማራቸው ሰዎች ይህን የተወለደውን ሕፃን ለመገናኘት ሙሉ ህይወታቸውን ሲጠብቁ የነበሩ ሰዎች እንደሆኑ አስረዱ - በመጨረሻም ስለመጣ በጣም ተደስተው መሆን አለበት! |
| ማጠናቀቅ | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ኢየሱስ በተወለደበት ምሽት እረኞች በጎቻቸውን እየጠበቁ በሜዳ ነበሩ። በተለምዶ በምሽት በግ መጠበቅ ረጭ ያለ እንደሆነ እና ምናልባትም አሰልቺ እንደሚሆን ጥቀሱ። ***(ቁጥር 8)***<br>2. ነገር ግን በዚህ ምሽት መልአክ ተገለጠላቸውና ሁሉም ደነገጡ! *ምን ተሰምቷቸው ሊሆን እንደሚችል ተማሪዎቹን ጠይቁ።* ***(ቁጥር 9)***<br>3. መልአኩ ኢየሱስ አዳኙ እንደተወለደ ሊነግራቸው መጥቷል። ***(ቁጥር 11)***<br>4. ከመልአኩ ጋር ተጨማሪ ብዙ መላእክት ተገለጡ እና የጌታ ኢየሱስን ወደ ምድር መምጣት በማስመልከት ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቀረቡ። ***(ቁጥር 13-14)*** ይህ እይታ ለእረኞቹ ምን ያህል አስደናቂ ሊሆን እንደሚችል አስረዱ።<br>5. መላእክቶቹ ከሄዱ በኋላ እረኞቹ ይህን ህፃን እራሳቸው ሄደው ለማየት ፈጠኑ። *በዚህ ጊዜ ምን ተሰምቷቸው ሊሆን እንደሚችል አስቡ፤ ምናልባትም በአይምሮአቸው የፈጠሩት ነገር እንደሆነ ፣ ወይም መልአኩ ስህተት እንደሆነ ሊያስቡ ይችላሉ።*<br>6. ልክ መልአኩ እንደገለጸው ህፃኑን አገኙት! እግዚአብሔርን አከበሩትና አመሰገኑት እና ለሁሉም ስለተወለደው አዳኝ መናገር ጀመሩ። ***(ቁጥር 16-17)***<br>7. እረኞቹ ይህንን ህፃን በማየታቸው ምን ያክል እንደተደሰቱ እና ወዲያውኑ ስለእርሱ ለሰዎች መናገር እንደጀመሩ አስቡ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት 4ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - እረኞች የኢየሱስን መወለድ ሰሙ።** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አቅርቡ**<br><br>**ተወያዩና አስረዱ:**<br>1. ስምዖን በታማኝነት እግዚአብሔርን የሚታዘዝና የሚታመን ሰው ነበር። ***(ቁጥር 25)***<br>2. ከመሞቱ በፊት ለረዥም ጊዜ የተጠበቀውን መሲህ እንደሚያይ መንፈስ ቅዱስ ለስምዖን ቃል ገብቶ ነበር። ***(ቁጥር 26)*** ይህ ይፈፀም አይፈፀም በማሰብ ስምዖን በእርጅና ዘመኑ ምን ተሰምቶት ሊሆን እንደሚችል ተወያዩ።<br>3. አንድ ቀን ማርያም እና ዮሴፍ ከሕፃኑ ኢየሱስ ጋር ሲመጡ ስምዖን በቤተመቅደሱ ውስጥ ነበር።<br>4. ስምዖን እጅግ ተደሰቶ እግዚአብሔርን አከበረ እና ሕፃኑን ባረከው።<br>5. ***በሉቃስ 2፡ 34*** ስምዖን እርሱ ለብዙ ሰዎች ደስታ እንደሚሆን ነገር ግን ብዙዎች እንደሚቃወሙት ተናግሯል። *ስምዖን ይህን ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ መርምሩ።*<br>6. ነብይ ሐናም በተመሳሳይ ጊዜ ቤተመቅደሱ ውስጥ ነበረች። እየጾመች እና እየጸለየች ሁሌም በቤተመቅደሱ ውስጥ ነበረች። ***(ቁጥር 36-37)***<br>7. ሕፃኑን ኢየሱስን ስታየው እግዚአብሔርን አከበረች እና ለሁሉም ሰው ስለእርሱ መናገር ጀመረች። ***(ቁጥር 38)***<br>8. ኢየሱስ ከወላጆቹ ጋር ወደ ቤት ሄደ እና ጥበበኛ በመሆን አደገ እግዚአብሔርም በእርሱ ተደሰተ። *ኢየሱስ በእርሱ እድሜ ካሉት ከሌሎች ሕፃናት እንዴት እንደሚለይ አስረዱ።*<br>9. *ስምዖን እና ሐና ስለልጃቸው በሰጡት ምላሽ ማርያም እና ዮሴፍ ምን ተሰምቷቸው ሊሆን እንደሚችል አስቡ።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አበረታቱ።**<br>**ጥናት 4ን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ስምኦን እና ሐና ሕፃኑ ኢየሱስን ተገናኙት** |
| ክለሳ | ይህ የልደት መግለጫ ምን ሊመስል እንደሚችል በአይምሮአችሁ የምትስሉትን ነገር የሚያሳይ ፖስተር ወይም የግድግዳ ስዕል ስሩ። በስዕላችሁ ውስጥ መልአኩ የተናገረውን ነገር (ቁልፍ ጥቅሱን) ጨምሩ። | ለልጃቸው በተሰጠው በዚህ ሁሉ የደስታ ምላሽ ምክንያት ማርያም እና ዮሴፍ ሀሴት አድርገው መሆን አለበት።<br>ቁልፍ ጥቅሱን አጥኑ እና ጥቅሱ የዛሬውን ጥናት እንዴት እንደሚያጠቃልል ከቡድኑ ጋር ተወያዩ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ስለኢየሱስ ታሪክ ለመናገር እኛም እንደ እረኞቹ እንጓጓለን? የእርሱ ልደት እነርሱ ያደረጉትን ያክል አስደናቂ እንደሆነ ታስባላችሁ?<br>2. የክርስቶስን ልደት ለትክክለኛ ምክንያቶች ነው የምናከብረው? ስለ ስጦታዎቹና ዝግጅቱ ብቻ ነው ወይስ አዳኛችን ለመሆን የኢየሱስን ወደ ምድር መምጣት እናስባለን? | **ትምህርቱ እንዴት ነው የሚያነሳሳን:**<br>1. ስምዖን እና ሐና ታማኝ የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ። እኛ ህይወታችንን ለእግዚአብሔር እንሰጣለን? ወደ እርሱ እንጸልይና መጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን?<br>2. በቁልፍ ጥቅሱ ውስጥ ኢየሱስ "አማኑኤል" ተብሎ እንደሚጠራ ይናገራል ማለትም "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር"። ይህን ካመንን ህይወታችንን እንዴት ነው የምንኖረው? |

# ለመምህራን የእርማት መመሪያ

### ለደረጃ 3 ትምህርቶች

- ተማሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን ሳያነቡ ትምህርቶቹን ማጠናቀቅ አይችሉም። ስለዚህ አንድ ወይንም ከዚያ በላይ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦችን ማድረግ ይጠበቅባቸው ይሆናል።
- ጥያቄዎቹ የተለያዩ ናቸው። እነኝህም cross words እና word grids, እንዲሁም የጎደሉ ቃላትን መሙላት ወዘተ… ናቸው።
- ጥያቄዎቹ የተለያዩ አይነቶች የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትሞችን በማንበብ እንዲመለሱ ታስበው የተዘጋጁ ጥያቄዎች ናቸው።
- የእኛ አላማ ሁሉም ተማሪዎች የትኛውንም አይነት የመጽሐፍ ቅዱስ እትም ተጠቅመው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ መርዳት ነው።
- በየሳምንቱ 20 ነጥቦች ይሰጣቸዋል። በወር ደግሞ ትምህርቶቹ በሙሉ ትክክል ከሆኑ በአጠቃላይ 80 ማርኮች ይሰጣቸዋል።
- ደረጃ 3 - ለአንድ መልስ አንድ ማርክ ብቻ ይሰጠዋል።

### ደረጃ 4 ጥናቶች

- እነኝህ በደረጃ ሶስት ከሚሰጡት ትምህርቶች በትንሹ ጠጠር ይላሉ።
- ተጨማሪ ውስብስብ ጥያቄዎችና መልሶች ያስፈልጋሉ።
- በሳምንት ሀያ ነጥቦች በወር ደግሞ 80 ነጥቦች ይሰጣሉ። ይህም ትምህርቶቹ በሙሉ ትክክል ሲሆኑና ጥያቄዎቹ የተሟላ መልስ ሲኖራቸው ነው።

### የነጥብ አሰጣጥ ፍንጮች

መምህራን በመጀመሪያ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ።

- እያንዳንዱን ትምህርት መገምገምና መልሶቹ ትክክል መሆን አለመሆናቸውን ምልክት ማድረግ።
- በመመሪያው መሰረት ትክክለኛውን ነጥብ መስጠት።
- ነጥብ ስንሰጥ የተለያየ አይነት ቀለም ያላቸውን ብዕሮች /እስክርቢቶዎች/ መጠቀም አለበን። ትክክል ለሆኑ መልሶች የ "✓" ምልክት እናድርግ።
- ትክክል ላልሆኑ መልሶች ትክክለኛ መልሶቻቸውን አስቀምጡ። የፊደላት ግድፈቶች ካሉም እርማት ስጡ። ለፊደላት ግድፈት ነጥብ አይቀነስም።
- በከፊል ትክክል ለሆኑ መልሶች ነጥብ ቀንሱ።
- የወሩን ድምር ነጥብ አስቀምጡ። ይህንንም በጀርባ ገፅ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ ጻፉ።

አንዳንዴ በአግባቡ ለጋስ መሆን ያስፈልጋል። እንዲሁም ተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን ማጠናቀቅ እንዲችሉ ለማበረታታት ማንኛውንም ነገር ማድረግ አስፈላጊ ነው። በየወሩ መጨረሻ መምህራን አንድ የማበረታቻ ቃል ለተማሪዎች ቢፅፉ መልካም ነው። ይህን ለማድረግም በየትምህርቶቹ ቦታ ተዘጋጅቷል። ጥሩ የቀለም ቅብን፣ ንፅሕናን፣ ተማሪው ያስመዘገበውን ነጥብ፣ ተማሪው ምን ያህል እንደተረዳ የሚገልፁ አስተያየቶችን መጻፍ ይቻላል።

አስተያየቶች በተቻለ መጠን የተለያዩ እንዲሆኑ መጣር አለብን። ጥያቄዎች፣ አረፍተ ነገሮች፣ ምልከታዎች፣ ማበረታቻዎች ወዘተ…ይህን ልዩነት ለማሳየት ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ይህ በጥልቅ ማሰብንና የተማሪዎች ፍላጎት መጠበቁን ማረጋገጥ ይጠይቃል። አንድ አረፍተ ነገር ወይንም ደግሞ ጥያቄ በየወሩ የሚደጋገም ከሆነ የሚፈለገውን ግብ ላይመታ ይችላል።

### ደረጃ 3

#### አጠቃላይ አስተያየቶች

"በጣም ጥሩ ስራ! ጥያቄዎቹን በጥንቃቄ እንዳነበብካቸው ያስታውቃል። በተለይም ለመጨረሻው ጥያቄ የሰጠኸው መልስ አስደስቶኛል። ትክክለኛ ቃላትን ተጠቅመሃል።"

"ሃይ ዮናታን! ስለጥረትህ አመሰግንሃለሁ። ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ መሞከርህ ትልቅ ነገር ነው። ያልሰራሃቸውን እኔው አሟልቼልሃለሁ።"

#### መንፈሳዊ አስተያየቶች

"ከእስራኤል ልጆች ጋር ሙሴ አስቸጋሪ ጊዜ ነበረው። ሆኖም እግዚአብሔር ሙሴ በራሱ ለነገሮች መፍትሔ እንዲፈለግ ብቻውን አልተወውም።"

"ዮሴፍ አባቱ እግዚአብሔርን እንዲወድ ያስተማረውን ትምህርት ፈፅሞ አልረሳውም። ከቤተሰቦቹ በጣም ርቆ በነበረበት ጊዜ እንኳን ይህን ፍፁም አልረሳውም።"

"በርጠሎሜዎስ ጌታ ኢየሱስን ለመንካት ቆርጦ ነበር። ማየት ችሏልና ምንም አይቆጨውም። አሁን ለእርሱ ጌታ ኢየሱስ ማለት በጣም ልዩ የሆነ ሰው ነው።"

### ደረጃ 4

#### አጠቃላይ አስተያየቶች

"ሌላ በጣም አስገራሚ ትምህርት! የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮቹን በሚገባ የተረዳሃቸው ይመስላል። እነኝህ ታሪኮች እንዳስደሰቱህም ተስፋ አደርጋለሁ። ትምህርቶችህን በጥንቃቄ ስላጠናሃቸው በጣም አመሰግንሃለሁ። በፍጥነት ልትጨርሳቸው ትችላለህ። ስለዚህ ጥረትህን በሙሉ አደንቃለሁ።"

"ራሔል! በጣም ጥሩ ሙከራ! መልሶችሽን አይቻቸዋለሁ። ታሪኩን ሙሉ በሙሉ የተረዳሽው አይመስለም። ምናልባት እንደገና ማንበብ ይጠበቅብሽ ይሆናል።"

#### መንፈሳዊ መልእክቶች

"ምሳሌዎች አንዳንድ ጊዜ ሰማያዊ ወይንም ጥልቅ ትርጉም በውስጣቸው የያዙ ምድራዊ ታሪኮች ተብለው ይጠራሉ። በጥናት 3 ያለውን ምሳሌ ጥልቅ ትርጉም ምን እንደሆነ ልታስበው ትችላለህ?"

"እስጢፋኖስ በጭካኔ አገዳደል ሞተ። ሆኖም ሞትን አልፈራም። ምክንያቱም አሁንም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በበላይነት እንደሚቆጣጠር ያውቅ ስለነበር ነው። እንዲሁም ቢሞትም እንኳን በሰማይ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንደሚሆን ያውቅ ነበር።"

© የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት 2019 ዓ.ም.

www.besweb.com

በሕግ የተመዘገበ የዩ.ኬ ለጋሽ ድርጅት 1186004

03/2025
AM-Amharic